## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስምንት (8)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን የእይታ ልዩነትና አንድነት በመዘርዘር ተወያዩበት::
2. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን ልዩነት ለማጥበብና አንድነታቹህ ላይ በጋራ አጠናክሮ ለመቀጠል ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
3. የጋራ የሆነ ገንዘብና ንብረት በፍጹም ግልጥነትና ነፃነት እየተጠቀማችሁ ነውን? ካልሆነ ችግሩ ምንድን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የከበሩ ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው::
5. እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ገንዘብን በጋራ እንዴት እንደምታስተዳድሩና እንደምትጠቀሙበት በፍጹም ግልጥነት፣ ነፃነት በተሞላውና የለውጥ እርምጃ ለመውሰድ በተዘጋጀ አቋም ተወያዩ::
6. በእናንተ ቤት ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት አለን? ካለ በምን ምክንያት ተፈጠረ? ግጭቱን ለመፍታትስ ምን እርምጃ መውሰድ አለብን ትላላችሁ?
7. በገንዘብና በንብረት ምክንያት በትዳራችሁ ግጭት እንዳይፈጠር አስቀድሞ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ ከወዲሁ በመመካከር ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ አቅዱ::





# ምዕራፍ ዘጠኝ(9)

# የግብረ ስጋ ግንኙነት

## 1. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ

የግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም ሩካቤ ስጋ ማለት ባለትዳር በሆኑ ጥንዶች መካከል ማለትም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ለጠለቀ ግንኙነት፣ ለስሜት እርካታና ልጅን ለመውለድ የሚደረግ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ግንኙነት ነው:: የግብረ ስጋ ፍላጎትን በማሟላት ፍቅርን የመሥራት ወይም የመገንባት ሂደት ነው። በትዳር በኩል የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት የከበረ፣ ንጹህ፣ እርኪና ለባለትዳሮች የተፈቀደ ነው። (ዕብ13፡4) በክርስቲያን ባለትዳሮ መካከል ችግሮችና አለመግባባቶች እንዲፈጠሩ ከሚያደርጉ ምክንያት አንዱ በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣምና አለመርካት ወይም መልካም የሆነ ግንኙነት አለመኖር ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ራሱን የቻለ ያለመግባባት መንስኤ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በትዳር መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን የሚያባብስ አቀጣጣይ የመሆን ሚናም ይጫወታል:: በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም የሚፈጠሩ ችግሮች ግለት ቶሎ እንዳይበርድ የሚያደርግና ቀስ በቀስም የትዳርን ህልውና የሚያጠፉ የተዳፈነ እሳት ሊሆን ይችላል።

ከባህላችን ተጽዕኖ የተነሳ በትዳር ውስጥ ፍላጎታችንና ችግራችንን በፍጹም ግልጥነት የማናወራበትና የማንወያይበት ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው። የጋብቻ አስተማሪዎችም ሆንን አማካሪዎች እንደ ሌሎች ችግሮች በድፍረት የማናስተምርበትና የማናማክርበት ርዕሰ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ችግሩ ከመቼውም በበለጠ እየጨመረና እየተባባሰ በመምጣቱ ብዙዎች ለአለመግባባት፣ ለመለያየትና ለፍች ተጋላጭ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል።

በትዳር ላይ የሚፈጠር የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ችግር ጥንዶቹ ሊያስተካከሉት ፍላጎት ካላቸውና ተገቢ ጥረት ካደረጉ በሂደት ሊቀንስ ይችላል:: እንደገናም በተለያዩ እርዳታዎችና ሕክምናዎች የመሻሻልና የመስተካከል ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ልንገነዘብ ይገባል። ያላገቡና ሊያገቡ እየተዘጋጁ ያሉ እንዲህ ዓይነቱን ችግር በመፍራት ከጋብቻ በፊት መሞካከርና ወሲብ መፈጸም ዝሙት የሆነ ኃጢአት እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ድርጊት አንዱ የጋብቻ ክፍል እንጂ የትዳር ሁሉ ነገር አድርገን ከማሰብ መቆጠብና ሌላው የትዳር ገጽታ የሚጠይቀውን የሁለትዮሽ መስጠት፣ መተሳሰብና መረዳዳት መዘንጋት አይገባንም። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ስንተሳሰብና ስንረዳዳ በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ወደ መጣጣም መምጣት የሚያስችለንን መልካም ስሜት መፍጠርና ማሳደግ እንችላለን::

ከችግሩ ጥልቀት፣ አሳሳቢነትና በክርስቲያኖች ትዳር ላይ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ እንደ ባለትዳር በግልጥነት ልንነጋገርበት ይገባል። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ

ትምህርትና ምክር ሊሰጥበትና ባለትዳሮች የሆንን አንዱ ሌላውን በመረዳት፣ በመተሳሰብና በመጣጣም አንድነታችንና የጠለቀ ግንኙነታችንን እያጠናከርን ልንኖር ይጠበቅብናል። በቅርብ የተጋቡ ተጋቢዎች መካከል በግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን መዳሰስ በትዳር ውስጥ በዚህ ሰበብ የሚፈጠሩ ችግሮችን መቀነስ የሚያስችሉ መርሆዎችን መዳሰስ የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት ነው።

## II. በክርስቲያን የትዳር ሕይወት የግብረ ስጋ ግንኙነት (ሩካቤ ስጋ) ዓላማ

### 1. በትዳር ውስጥ ያለውን ግንኙነት ጥልቀቱንና አንድነቱን ለመገንባት /ዘፍ 2፡ 24-25፣ መዝ 7፡6-12/

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው በትዳር ውስጥ ያለው የግብረ ስጋ ግንኙነት አንደኛው ዓላማው በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ጥልቀት እንዲኖረውና አንድነታቸው ይበልጥ እንዲጠናከር ማድረግ ነው። በትዳር መካከል ያለውን ግንኙነት ምን ያክል የጠነከረ ግንኙነት እንደሆነና ሊሆን እንደሚገባው ሲገልጥ መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /ዘፍጥ 2፡ 24/ በማለት ያስረዳል። *"አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር"* /ዘፍ2፡ 25/ በሚለው መርህም ቅዱሱ መጽሐፍ በባለትዳሮች መካከል ግልጥነትና ነፃነት ያለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊኖር የሚገባ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ ያስረዳል:: ይህንን መረዳታችን የግብረ ስጋ ግንኙነት የተሰጠበትን ዓላማ ለመጠበቅና በግንኙነታችን መካከል ለሚፈጠረው ችግር በጋራ መፍትሔ ለማፈላለግ ጥረት እንድናደርግ ያግዘናል። በትዳር ውስጥ ያለውን አንድነት የሚያሳይና ጥልቅ የሆነ ግንኙነት መሆኑ በግንኙነቱ ሂደት ባለው ግልጥነት፣ መተፋፈር የሌለበት በመሆኑ፣ ራቁትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ መካከል የሌለበትና አንድ ስጋ የመሆን ሚስጥር ያለበት ግንኙነት በመሆኑ ተገልጧል።

### 2. ለደስታና ለእርካታ /ምሳ 5፡ 18-19፣ 1ኛቆሮ 7፡ 2-5/

ሐዋሪያው ጳውሎስ የቆሮንጦስ ክርስቲያኖች ለጻፉለት በትዳር ውስጥ ላሉ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚጀምረው በትዳር መካከል ስላለው የግብረ ስጋ ግንኙነት *"ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ"* /1ቆሮ 7፡ 3/ የሚል ግልጥ መመሪያ ለባልና ለሚስት በመስጠት ነው:: ጋብቻ በትዳር ውስጥ ባለው ግንኙነት ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ፍላጎት በማስቀደም አንዱ አካል ሌላውን ለማስደሰትና ለሌላው የእርካታ ምክንያት በመሆን ለመኖር ጥረት የሚደረግበት ተቋም ነው። እያንዳንዳችን ባለትዳሮች ልንገነዘበው የሚገባን በራሳችን ስጋ ላይ ስልጣን እንደሌለንና ስልጣኑ የትዳር አጋሮቻችን እንደሆነ ነው:: ይህንን በመገንዘብ ለሌላው ስሜትና እርካታ ራሳችንን መስጠት እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስረግጥልናል። በራሳችን አካል ላይ ስልጣን እንደሌለን ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን መከልከል እንደሌለበት ሲያስረዳም ሐዋርያው ጳውሎስ *"አትከላከሉ"* በማለት ያሳስባል። መታቀብ ካስፈለገም





ዓላማው ለጸሎት ብቻ ሊሆን ይገባል:: ይህ ዓይነቱ መታቀብ እንኳን የጋራ ስምምነትን የሚጠይቅና ለአጭር ጊዜ ብቻ መቆየት ያለበት ነው። እርስ በርሳችን በመስማማት ለጸሎት ጉዳይ ከግብረ ስጋ ግንኙነት መታቀብ የምንችል ሲሆን ይህ እርምጃ ለረጅም ጊዜ መታቀብን በማስወገድና አብሮ መኖርን በማበረታታት ራስን ባለመግዛት ለሰይጣን ፈተና አልፈን እንዳንሰጥና እንዳንጋለጥ ያደርገናል።

የእግዚአብሔር ቃል በምሳ 5፡ 18-20 *"ምንጭህ ቡሩክ ይሁን ከጉብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ። እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበችም ሚዳቋ ጡትዋ ሁልጊዜ ታርካህ በፍቅርዋም ሁልጊዜ ተጋበ"* ይላል። በባለትዳሮች መካከል አንዱ ሌላውን እንዲያረካና በትዳር የተጣመረ ሰው ከትዳር አጋሩ ጋር ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ በመወሰን ደስተኛ እንዲሆን ይመከራል። ማንኛውም ከትዳር ውጭ ያለ ግንኙነት ዝሙት ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት እኛም ለሌላ የትዳር አጋሮቻችንም ለሌላ እንዲሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ አይፈቅድም! ይልቁንም ከጉብዝና የትዳር ጓደኛችን ወይም ከመጀመሪያ የትዳር አጋራችን ጋር ብቻ ደስ ይበለን ይለናል /ምሳ 5፡ 18/:: ከትዳር አጋሮቻችን ጋር በሩካቤ ስጋ ግንኙነት እርስ በርሳችን እንረካ ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው። አንዱ ለሌላው ፍላጎትና እርካታ መጠንቀቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ነው። ምንም ዓይነት ምክንያቶች ቢኖሩን እንኳን አንዱ የሌላውን ፍላጎት ባለመረዳትና ባለማሟላት ከሚፈጠር ግጭትና መለያየት የትዳርን ግንኙነት እየጠበቁ መተሳሰብ እንጅ ማሳበብ አያዋጣንም!!

### 3. ልጅ ለመውለድ (ለመዋለድ) /ዘፍ 2፡ 27-28/

ሌላውና የመጨረሻው የግብረ ስጋ ግንኙነት በትዳር ውስጥ ያለው ዓላማ ልጆችን በመውለድ የመባዛትን ሂደት ማስቀጠል ነው:: ጋብቻ እግዚአብሔር ለባለትዳሮች ልጆችን ስጦታ አድርጎ የሚሰጥበት መንገድ ነው *"እናንተም ብዙ፥ ተባዙ በምድር ላይ ተዋለዱ፥ እርቡባትም።"* /ዘፍ 9፡ 7/:: ይህ ሲባል ከጋብቻ ውጭ ባለ የግብረ ስጋ ግንኙነት ልጆች አይወለዱም ማለት አይደለም። ደግሞም ክርስቲያን ባለትዳሮች ሆነው ልጆች የሌሏቸው ጥንዶች የሉም ለማለትም አይደለም። ልጆች ሳይኖሯቸው በደስታ የሚኖሩ ጥንዶች እንዳሉ ሁሉ እንዲሁ በሐዘን፣ በግጭት... የሚኖሩ ቁጥራቸው ጥቂት አይደሉም! ትዳር ልጆች ባይኖሩም ተዋደን፣ ተቀባብለንና ተረዳድተን የምንኖረው ቃል ኪዳናዊ ትሥሥር ነው።

ለትዳር ግንኙነታችን የልጆች አለመኖርም ሆነ መኖር ለግጭትና ላለመግባባት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ ርዕስ ውስጥ በዋናነት ለመናገር የምፈልገው እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ የፈጠረበትና ወንድና ሴት ብቻ በትዳር እንዲጣመሩ የፈለገበት አንደኛው የትዳር ዋና ዓላማ ልጆችን መውለድና የማሕበረሰብን ሂደት ማስቀጠል መሆኑን ነው:: በዚህም በትዳር በተጣመሩ ባልና ሚስት ወይም እናትና አባት ጥበቃና እንክብካቤ ልጆች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲያድጉ ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ወቅት እንዲመሠረት አድርጓል::

ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን ልጆች ለሰጪው ምስጋና እያቀረብን በአግባብ የማሳደግ ኃላፊነት አለብን:: ይህንን ኃላፊነት ተገንዝበን ልጆቻችን ባንድ በኩል ከመለኮት የተቀበልናቸው የደስታችን ምክንያቶች በሌላ በኩል ደግሞ ጠብቀንና ተንከባክበን ማሳደግ ያለብን የመለኮት አደራዎች ናቸውና ኃላፊነታችንን በአግባቡ በመወጣት የትዳር ዓላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ የድርሻችንን አስተዋጾ ማበርከት አለብን:: ከዚህ በተቃራኒ ግብረ ሰዶማዊነት የዘመኑ ሰይጣናዊና ስልጣኔ አመጣሽ የትዳር፣ የቤተሰብና የማሕበረሰብ ብሎም የትውልድ ቀጣይነት እንቅፋት በመሆን የመገለጡን ሃቅ ልብ ማለት ይኖርብናል:: ይህ የተመሳሳይ ጾታ ሰዶማዊ ግንኙነት የእግዚአብሔርን ዓላማ በሚቃወም መልኩ ዲያብሎስ እየተጠቀመበት ያለ ሰይጣናዊ ስልት ነው። ይህንን በመረዳት ትዳርን የእግዚአብሔር መልካም ዓላማ መፈጸሚያ በሚሆን መንገድ መጠበቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ ልንጠነቀቅለት የሚገባ ኃላፊነታችን ነው:: ልጆቻችንንም በእግዚአብሔር ቃልና ሰላም በተገነባ ቤተሰብ ውስጥ ተቀርጸው እንዲያድጉ የማድረግ መለኮታዊ አደራ አለብን:: ከዚህ የምንዘገይ ዳተኞች ሆነን ልጆቻችን ለትዳራችን የግጭት ምክንያት እንዳይሆኑብን ኃላፊነታችንን አውቀን የምንኖር አስተዋይ ባለ አደራዎች ልንሆን ይገባል።

ልጆች የሌሉን ባለትዳሮች ከሆንን ደግሞ መካኒቷን ሰባት እንድትወልድ ያደረገ እግዚአብሔር ዛሬም አልተለወጠምና በጸሎትና በምልጃ ከምስጋናም ጋር ልምናችንን ማሳወቅ እንጂ ተገቢ ባልሆነ ጭንቀት መሰቃየት የለብንም:: ትዳር ስንመሠርት ልጆች አልነበሩም:: ትዳሩን የመሠረትንበትን ቃል ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት የገባናውም ልጆችን አካትተን አይደለም:: በፊቱ የዕድሜ ልክ ጋብቻ ቃል ኪዳን ስንገባ አብሮን የነበረው አምላክ ልጅን የመስጠት ችሎታና አቅም ያለው እርሱ ነው:: እርሱ ደግሞ የሚያደርገውን የሚያውቅ በሥራው ጻድቅ የሆነ አምላክ ነው:: እግዚአብሔር የትዳርን መርህ ባሳወቀበት በቃሉ ልጆች ካልሰጠኋችሁ ወደ ግጭትና ወደ ፍች ሂዱ ብሎም አላዘዘንም:: ስለዚህ ይህንን እውነት በመረዳት በትዳር የተጣመርን ባልና ሚስቶች ልጅ ባለ መውለድ ምክንያት በእግዚአብሔር ቃል መርህ የተመሠረተውን ትዳር እንዳናፈርሰው ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል:: ይህ ማለት ልጅ ያለመውለድ ችግር ቀላል ነው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ችግሩ ምንም አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ሳንጋጭ ደስታችንን በጌታና ከጌታ በተሰጠን የትዳር አጋር ላይ በማድረግ ባለን ግንኙነት ማረፍን በመለማመድ ጌታን እንጠብቅ። ልጆች ሊኖሩን ባይችሉም እንኳን እግዚአብሔርን አከብሮ ማለፍ የመጀመሪያው የሕይወታችን ደስታ ሆኖ እንዲቀጥል ትዳራችንን ለዚህ ክቡር አገልግሎት ማስገዛት ዋናው የሕይወት ዓላማችን ሊሆን ይገባል::





## III. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

### I. በወንዶች ላይ የሚከሰት ፈጥኖ እርካታ ላይ የመድረስ ችግር

አንድ ወንድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እርካታ ላይ ደረሰ የሚባለው የዘር ፈሳሹን ወደሚያፈስስበት ደረጃ ሲደርስ ነው:: በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ እርካታ ላይ ደርሷል ሲባል ባል ወይም ወንዱ የፍትዎት ፍላጎቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ የጋለ ስሜት ላይ በመሆን የወንድ ዘር ማፍሰስ (መርጨት) ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ባሎች (ወንዶች) ከዚህ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የስሜት እርካታ ደረጃ ላይ የሚደርሱት ሚስቶቻቸው (ሴቶች) ገና በአግባቡ ዝግጁ ሳይሆኑ ነው:: በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ወደዚህ ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ የፍትዎት ስሜት እርካታና ደስታ ደረጃ ሚስት ከመድረሷ፣ ለመርካት ዝግጁ ከመሆኗና ከመርካቷ በፊት ባል በጥድፊያ እርካታ ላይ መድረሱ የሚስትን ስሜት የሚጎዳና ደስታዋን የሚከለክላት ችግር እንዲፈጠርባት ያደርጋል:: ሚስት ገና እርካታ ላይ መድረስ እየፈለገች ባሏ አስቀድሞ ሲረካና ግንኙነቱን ሲጨርስ የጋራ እርካታ የሚባለው መተሳሰብ ይጠፋና ሚስት የእርሱን ስሜት ለማርካት ብቻ የተፈጠረች ስሜት አልባ ተደርጋ እንደታየች እንድታስብ ያስገድዳታል:: ይህ በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ ባሎች የሚስቶችን ስሜት ሳይጠብቁ አስቀድሞ የስሜት መርካት ላይ የመድረስና የግብረ ስጋ ግንኙነትን ሂደት ቅጽበታዊ በሆነ ጥድፊያ ቀድመው የመጨርስ ችግር በሬሽዮ ሲጠና 1፡3 ሲሆን ይህ ማለት ከሶስት ወንዶች በአንድ ወንድ ላይ ሊከሰት ይችላል።[19]

እንዳቸው የሌላቸውን ስሜት ሳይጠብቁ በጥድፊያ በመርካት ችግር ምክንያት እግዚአብሔር ለሰዎች በሰጠው በትዳር ውስጥ ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት መልካም ስጦታ ከመደሰት ይልቅ የስሜትና የስነ ልቡና ቀውስ እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል:: የችግሩ ሰለባዎችም የማፈር፣ የመሸማቀቅ፣ ተገቢውን ክብርና ስፍራ ያለማግኘትና ራሳቸውን የመውቀስ ስሜት ይፈራረቅባቸዋል። በትዳራቸው ከመደሰት ይልቅ ሐዘንተኞች ይሆናሉ:: ጉዳዩ በጊዜ ካልተስተካከለ የትዳሩ ዘላቂነትም አደጋ ላይ ይወድቃል:: ችግሩ በጊዜ ይስተካከል ዘንድም የችግሩን ምክንያቶችና መፍትሔዎች

[19] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to Sexuality and Relationship Counseling, Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2009. page 82

መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች የችግሩን ምክንያቶች በማስቃኘትና መፍትሔዎችን በመጠቆም የአንባቢውን ግንዘቤ የማስፋት ጥረት ያደርጋሉ፡-

**1) ፈጥኖ የወንድ ዘር ፍሬ የመፍሰስ ችግር ምክንያቶች**

**ሀ. ስነ ልቦናዊ ምክንያቶች**

**i. በልጅነታቸው (ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሄዋን) ሳይደርሱ የደረሰባቸው ጥቃት (ጉዳት)**

እንዲህ ዓይነቱ ጥቃት በአስገድዶ መደፈር፣ በመጠለፍና በተለያዩ መንገዶች የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የመሆን ገጠመኝ ነው። ጥቃቱ ስውር በሆነ መንገድ አብረው ቤት ውስጥ በሚኖሩ የቅርብ ዘመዶች፣ ወዳጆች፣ በጎረቤት ሰዎችና ቤት ውስጥ ተቀጥረው በሚሠሩ የቤት ሠራተኞች በኩል በልጅነት ወቅት የደረሰ ጉዳት ሊሆንም ይችላል፡፡ ልጆች በተለያዩ ሰዎች ተታልለው ወይም ተገድደው የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ ራሳቸውን መጠበቅና ከጉዳት መከላከል የማይችሉ ሕጻናት ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍላቸውን በመነካካትና የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ወይም በማያውቁትና ባልገባቸው መንገድ የሌሎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ እየተገደዱ ሊያድጉ ይችላሉ፡፡ ይህ ክስተት ልጆች እያደጉ ሲመጡ በስነ ልቦናቸው ላይ የሚፈጥርባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ የልጅነት ዘመን ጉዳት ብቻ ሳሆን የሕይወት ዘመን ቁስል በመሆን ትዳር በሚመሠርቱበት ጊዜም የግንኙነት እንቅፋት ይሆናል። የእንዲህ ዓይነቱ ስውር ጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ወላጆች ከልጆች ጋር ያላቸው ግንኙነት የጠነከረ፣ ግልጥና መልካም ተግባቦት ያለው ሊሆን ይገባል። በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ተጠቂ የሆኑ ልጆች ማንነታቸው ላይ ቀውስ ሊፈጥርባቸው ይችላልና ትክክለኛ የምክር፣ የጸሎትና የመንፈሳዊ ትምህርት ድጋፍ በማግኘት በክርስቶስ ማንነት ላይ ሥር የሰደደ መሠረት እንዲኖራቸው መረባረብ ያስፈልጋል። በዓለም ላይ ወጣቶችና ሕጻናት ለግብረ ሰዶማዊነት አልፈው እንዲሰጡና ግብረ ሰዶማዊነትም እንዲስፋፋ እያደረጉ ካሉ ምክንያቶች አንዱ በልጅነታቸው በልጆች ላይ የሚደርስ ወሲባዊ ጥቃት እንደሆነ ይነገራል።[20]

**ii. ቶሎ ለመርካት ያላቸው ጉጉት**

ክርስቲያን ወንዶች እንደ ማንኛውም ሰው የፍትወት ፍላጎት አላቸው። የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ማርካት የሚቻለው ደግሞ ከትዳር አጋር ጋር በሚደረግ ግንኙነት ብቻ መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ ነው። *"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።"* /ዕብ 13፡ 4/ ለዚህ የክርስትና ሕይወት መርህ ራሳቸውን በማስገዛት ምክንያትም ከጋብቻ በፊት ከዝሙት ራሳቸውን ለመጠበቅ ስሜታቸውን በብዙ ትግል ውስጥ ሲቆጣጠሩት ኖረዋል፡፡ ለትዳርም ከፍተኛ ናፍቆትና ጉጉት አላቸው፡፡ እነዚህ ክርስቲያን ወንድሞች ወደ ጋብቻ ሲገቡ በጋብቻ

[20] Hunt, June. Counseling through your Bible Handbook page 211-212





ውስጥ ከትዳር አጋራቸው ጋር በሚያደርጉት የሩካቤ ስጋ ግንኙነት የመፈጸም ሂደት ለመርካት ባላቸው ከፍተኛ ጉጉት ምክንያት የሚሰትን ስሜት ሳይጠበቁና እነርሱ ራሳቸውም እንኳን ዝግጁ ሳይሆኑ የመርካት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

**iii. ባል ብልቴ ይቆም ይሆን የሚል ጭንቀት ሲያጋጥመው**

አንዳንዶች ወደትዳር የሚገቡ ወንዶች (ባሎች) ካሁን በፊት አሉታዊ ተጽዕኖ ያደረሰባቸው ገጠመኝ ካለ ከደረሰባቸው ስነ ልቦናዊ ችግር የተነሳ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸሚያ የሰውነት ክፍላቸው (ብልታቸው) ይቆም ይሆን የሚል ፍርሃትና ስጋት ያጋጥማቸዋል።[21] አብዛኛውን ጊዜ ፍርሃትና ስጋት በሚኖርበት ወቅት ወደ ግብረ ስጋ ግንኙነት ለመግባት ስሜታዊ ዝግጁነት ያለን መሆን ያቅተናል። ይህ ዓይነቱ የስሜት ዝግጅት አለመኖር ደግሞ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸሚያ የሰውነት ክፍሎቻችንም ለግብረ ስጋ ግንኙነት ዝግጁ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጭንቀት ውስጥ ያለ ባል የትዳር አጋሩን በግብረ ስጋ ግንኙነት ለማርካት አይችልም። ራሱም በግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ የሚገኘውን እርካታና ደስታ መካፈል አይችልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት የግንኙነት ችግር ያጋጠማቸው ባለትዳሮች ለሌሎች አለመግባባቶችና ግጭቶች አልፈው የመስጠት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

**ለ. ስነ ሕይወታዊ (ባዮሎጅካል) ምክንያቶች**

**i. የሆርሞን (የሰውነት ንጥረ-ቅመም) መጠን መዛባት**

የባሎች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ፈጥኖ የዘር ፍሬን በማፍሰስ ወደ እርካታ የመድረስ ችግር በወንድ ልጅ አካል ውስጥ የሚገኝ ቴስቴስትሮን የሚባል አካላዊ ንጥረ-ቅመም (የሆርሞን) መጠን በመዛባቱ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል። በተፈጥሯዊ ምክንያቶችና በሚወስዱ ልዩ ልዩ መድሃኒቶች ምክንያት እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሊፈጠርና ሊባባስ ይችላል። ከዚህም ባሻገር በአእምሮ (Neurotransmitters) ውስጥ ያለ የኬሚካል መጠን በመዛባቱ ምክንያትም ችግር ሊፈጠር ይችላል።[22] ይህ ከሆነ ደግሞ ችግሩ ያጋጠመው ሰው ጉዳዩ ሊፈታ የሚችል ከሆነ የምክር፣ የሕክምና ወይም ሌሎች ሙያዊ ድጋፎችን የመፈለግ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ጥፋቱ የራሱ እንደሆነ በማሰብ ራሱን መውቀስና መኰነን አይኖርበትም፡፡ ይህንን የሚያደርግ ከሆነ ያላሰባቸው ሌሎች የስነ ልቦናና የስሜት ቀውስ ችግሮች ያጋጥሙታል፡፡ የትዳር ጓደኛ የሆነችው ሚስቱም ይህንን ችግር መረዳትና መታገስ መቻል ይጠበቅባታል፡፡

**ii. የወንድ የዘር ፍሬ መርጫ ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ በትክክል አለመሥራት**

የወንድ የዘር ፍሬ መርጫ የሰውነት ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ በትክክል አለመሥራት ሌላው ተጠቃሽ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት እርካታ ላይ ለመድረስም ሆነ

[21] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to Sexuality and Relationship Counseling, Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2009. page 84

[22] pp.84

የትዳር ጓደኛን የእርካታ ፍላጎት ማሟላት ያለመቻል ምክንያት ነው። የተለያዩ የሰውነት አካል ክፍሎች በበሽታ መጠቃት ይህን ችግር የሚያስከትል ተጠቃሽ መንስኤ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያክል በሰውነት ላይ የሚፈጠር ጉዳት ወይም በእንቅርት እጢና ፕሮስቴት በመባል የሚታወቀው ከወንድ ልጅ ፊኛ በታች የሚገኝ ለወንድ ዘር የሚሆን ፈሳሽ የሚያመርት እጢ የመጎዳትና የቁስለት ችግርና ይህም ጉዳት በዘር ተላላፊ መሆኑ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።[23]

**2) ፈጥኖ የወንድ ዘር በመፍሰስ ለሚቸገሩ ባለትዳሮች መፍትሔዎች**

**ሀ. መረዳት፡- አልፎ አልፎ ሊፈጠር የሚችል ክስተት መሆኑን መረዳት**

ይህ ችግር በአብዛኛው በወንዶች ላይ የሚታይና የሚከሰት ችግር መሆኑን መገንዘብ መቻል አስፈላጊ ነው። ይህ የሚፈጠረው ችግር ምንም ዓይነት ጥንቃቄ ብናደርግም እንኳን መከሰቱ አይቀሬ እንደሆነ መረዳትና የሚከሰተው ግን አልፎ አልፎ መሆኑ ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ባሎች ስለችግሩ ምንም ያህል ቢያውቁና ችግሩን የማስቀረት ፍላጎት ኖሯቸው ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም እንኳን ችግሩን ይቀንሱት እንደሆነ እንጂ ፈጽሞ ሊያስወግዱት አይቻላቸውም፡፡ ስለዚህ ፈጥኖ የወንድ ዘር የመፍሰስ ችግር የሚያጋጥመው አልፎ አልፎ ከሆነ መታገስና መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ ችግሩ አልፎ አልፎ ከሆነ መታገስና መቀበል አስፈላጊ የሚሆነውም በሚታየው ችግር ከሚፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ራስንና የትዳርን ግንኙነት ለመጠበቅ ሲባል ነው። ይህን ማድረጉ ጊዜያዊ የሆነው ችግር ዘላቂ የሆነው ትዳር ላይ የሚከብድ ጉዳት ፈጥሮ እንዳያልፍ ለመከላከል እንዲቻል በጋራ ለመረዳትና ለመረዳዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ለቀጣይ እርዳታ የመጀመሪያው እርምጃ ችግሩ ጊዜያዊና አልፎ አልፎ ብቻ ሊከሰት የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ መቻል ነው።[24]

**ለ. መታየት፡- በሕክምና ባለሙያ መታየት**

ፈጥኖ የወንድ ዘር የማፍሰስ ችግር በተለያዩ በሽታዎች ምክንያት ወይም ለሌሎች ሕመሞች ፈውስ ለማግኘት ሲባል በሐኪም ትዕዛዝ የሚወሰዱ መድሃኒቶች በሚያስከትሉት የጎንዮሽ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰተ ሊሆን ስለሚችል የችግሩን መንስኤም ሆነ መፍትሔውን ለማፈላለግ ወደ ሕክምና ባለሙያ መሄድና ማነጋገር አስፈላጊ ነው። የሕክምና ባለሙያን ማነጋገር ሊያሸማቅቅ፣ ሊያስፈራና ሌላ ስጋት ውስጥ ሊያስገባን አይገባም። እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰድ ለችግሩ በፍጥነት መፍትሔ በማፈላለግና መፍትሄ በማግኘት በትዳር ውስጥ የሚገኘው እርካታና ደስታ ሁለቱንም ጥንዶች የሚያካትት እንዲሆን ለትዳር ግንኙነት ትኩረት መስጠትንና አሳቢነትን ያመላክታል።

[23] Sexuality and Relationship Counseling pp 84
[24] Sexuality and Relationship Counseling pp 83





በሰውነት ውስጥ በሚገኝ ንጥረ-ቅመም (ሆርሞን) መብዛትና ማነስ፣ የወንድ ዘር የመርጫ የሰውነት ስርዓት (ሲስተም) እንደሚገባ አለመሥራት ወይም ሌሎች በሽታዎችና በሽታዎችን ለማስወገድ የሚወሰዱት መድሃኒቶች ተደማምረው የሚያመጡት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊታወቅና ሊረጋገጥ መፍትሔም ሊፈለግለት የሚችለው ወደ ሕክምና ባለሙያ በመሄድ ነው፡፡ ሐኪም ማነጋገርና የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በምርመራ ውጤቱ የችግሩን እውነተኛ ገጽታ ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው። በትክክለኛ ሐኪም ታይቶና ተገቢ የሕክምና ምርመራ አድርጎ የምርመራ ውጤቱ ሳይረጋገጥና ሐኪም ትዕዛዝ ሳይሰጥ ችግሩን ለመፍታት ያግዛሉ የሚባሉ መድሃኒቶችን መጠቀም አሁን ያለውን ችግር ከማባባስ በተጨማሪ ላልታሰቡ የጎንዮሽ ተጽዕኖዎች ያጋልጣል፡፡ በዚህም ምክንያት ለሌሎች ውስብስብ ለሆኑ በሽታዎችና ችግሮች አልፈን ልንሰጥ እንችላለን።

በወንድ ልጅ ላይ የሚከሰተውን ፈጥኖ የወንድ ዘር ማፍሰስ ችግር ለመቀነስ በሐኪም ከሚታዘዙ የተለያዩ መድሃኒቶች ውስጥ አንዱ በሐኪም ትዕዛዝ ለጸረ-ድብርት (ለጸረ-ድባቴ) የሚሰጥ መድሃኒት (Antidepressant medicine) ነው፡፡ ይህን መድሃኒት መውሰድ በባሎች ላይ የሚከሰተውን በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ፈጥኖ ዘርን የማፍሰስን ሂደት የማዘገየት ተፅዕኖ አለው። ይህ መፍትሔ ፈጥኖ የወንድ ዘርን የማፍሰስ ችግርን ሲያስወግድ በአንጻሩ ደግሞ ይህን መድሃኒት የሚወስዱ ሰዎች ለፍትወት ያላቸውን ተነሳሽነት እንዲቀንስ የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖም እንዳለው መረዳት አስፈላጊ ነው።[25]

ሌላው በሕክምና ባለሙያ ለወንድ ልጅ ዘር ፈጥኖ የመፍሰስ ችግር ከሚታዘዙት መድሃኒቶች መካከል የሚታዘዘው የሚቀባ ክሬም እንዲጠቀሙ ነው። ይህ የሚቀባው ክሬም (Lidocaine or Prilocaine ) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቅባቱ የወንድን ብልት (ስሜትን) የማደንዘዝ ባህሪይ አለው። የወንድን ብልት በማደንዘዝም በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ባሎች የዘር ፈሳሻቸው ፈጥኖ እንዳይፈስ የማዘግየት ባህሪይ አለው። ነገር ግን መድሃኒቱ የሴትን ብልት የማደንዘዝና የፍትወት ፍላጎቷን የመቀነስ ባህሪይና አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል መድሃኒቱን ከመጠቀም በፊት የሐኪምን ሙያዊ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ነው።[26]

**ሐ. መጠቀም፡- የተለያዩ ዘዴዎችን (ቴክኒኮችን) መጠቀም**

**i. የመጭመቅ ቴክኒክ**

ፈጥኖ የወንድ ዘር መፍሰስን ችግር ለማስወገድና በባለትዳሮች መካከል የጋራ እርካታ የሚያስገኝ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲኖር ከሚመከረው ምክር አንደኛው ዘዴ የመጭመቅ ቴክኒክ ነው። ይህ የመጭመቅ ዘዴ አራት ደረጃ በደረጃ ሊወሰዱ የሚገቡ

[25] Sexuality and Relationship Counseling pp 86
[26] Sexuality and Relationship Counseling pp 86

እርምጃዎችን ያካተተ ነው። የመጀመሪያው ደረጃ የወንድ ዘር የመፍሰስ ስሜት እስኪጀምር ድረስ ትክክለኛ የሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነትን መቀጠልና በተለያዩ ስጋቶች ግንኙነትን አለማቋረጥን ይጠይቃል። ሌላው ሁለተኛ ደረጃ የመጭመቅ ቴክኒክ ዘዴ የወንዱ ዘር መፍሰስ ከመጀመሩ በፊት የወንድን ብልት ጫፍ ጨምቆ ለተውሰኑ ሴኮንዶች በመያዝ የማሳለፍ ዜዴ ነው። ሶስተኛው ደረጃ የመጭመቅ ዘዴ እንደ ገና የግብረ ስጋ ግንኙነት ከመጀመር በፊት ለ30 ሴኮንድ የወንዱን ብልት በመልቀቅ መጠበቅ መቻል ነው። የመጨረሻው ደረጃ ደጋግሞ በመጭመቅ ሚስቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት እስኪረኩ ድረስ መጠበቅና በጋራ የግብረ ስጋ ግንኙነት እርካታን በመጋራት በግንኙነታቸው አብረው ደስታን የሚካፈሉ የሚተሳሰቡ ጥንዶች መሆን መቻል ነው።[27]

**ii. ትንፋሽንና አሳብን የመቆጣጠር ዘዴ**

ችግሩን ለመቀነስ ከሚያግዙ የተለያዩ ዘዴዎች ሌላኛው ትንፋሽንና አሳብን የመቆጣጠር ዘዴን መጠቀም ነው። አንደኛው የዚህ ዘዴ ትግበራ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ረዘም አድርጎ ትንፋሽ በመውሰድ የተፈጠረውን ስሜት የመቆጣጠርና የማዘገየት ሂደትንና ችሎታን ማዳበር ነው። ሌላው የትግበራ ሂደት ደግሞ ባል የዘር ፈሳሹን ፈጥኖ የማፍሰስን ችግር ለማስወገድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የፍትዎት ፍላጎቱ የእርካታ ጫፍ ላይ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ወቅት ከዚህ ስሜት ሊያወጡ የሚችሉ የተለያዩ አሳቦችን የማሰብ ሂደት ነው። ብዙ ጊዜ ድርጊቶች የአስተሳሰብ ውጤቶች ናቸውና ይህንን አእምሮን በተለያዩ ሃሳቦች በመሙላት ስሜትን የመቆጣጠር ዘዴ ባሎች ሊረዱትና ሊጠቀሙበት ይገባል።[28]

**iii. ጭንቀትንና ውጥረትን የመቆጣጠር ዘዴ**

በባለትዳሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የወንድ ልጅ የዘር ፈሳሽ ፈጥኖ እንዲፈስስና ከትዳር ጓደኛ ጋር የጋራ የሆነ የስሜት እርካታ እንዳይፈጠር ከሚያደርጉት ችግሮች መካከል ሌላው ምክንያት ባል አስቀድሞ ከሚስቱ ጋር ባደረጋቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ሂደቶች ውስጥ ያጋጠሙት ተመሳሳይ ችግሮች የሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው። ከሚፈጠሩት አሉታዊ ተጽዕኖዎች መካከል አንዱ ቶሎ ስሜቴ ይረካል፣ ሚስቴን ሳላረካ ልቀር እችላለሁና ሚስቴ ምን ትለኛለች...? የሚሉ አሳቦችና ጥያቄዎች አእምሮውን ማስጨነቃቸው ነው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ አሳቦች ይበልጥ እንዲጨነቅና የስነ ልቦና ጫና ውስጥ እንዲገባ ያደርጉታል፡፡ የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርግበት ጊዜም በውስጡ ውጥረት ይፈጥራሉ።[29] ችግሩ እንዲፈታ እነዚህን ስነ ልቦናዊ ችግሮች ማስወገድ፣ መቆጣጠር፣ አንዱ ሌላውን ማበረታታትና በነገሮች ላይ በፍቅር መነጋገር ተገቢ ነው።

[27] Sexuality and Relationship Counseling PP 85
[28] Sexuality and Relationship Counseling PP 85
[29] Sexuality and Relationship Counseling PP 85





**2. በባለትዳር ሴቶች ላይ የሚፈጠር ለፍትዎት ተነሳሽነት ያለመኖር ችግር**

የፍትዎት ተነሳሽነት ፍላጎት ብለን ስናስብ አንዳንዶቹ ዝቅተኛ የሆነ ፍላጎት መኖር ችግር ሲኖርባቸው ሌሎች ደግሞ ፈጽሞ ፍላጎት የሌላቸው በመሆን ሊቸገሩ ይችላሉ። በቅርብ ዓመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አንዱ በሴቶች ላይ የሚከሰት ለፍትዎት ፍላጎት ተነሳሽነት አለመኖር ነው። ይህ ችግር ከባለትዳር ሴቶች መካከል በ20% ላይ እንደሚፈጠር ይታመናል።[30] ባለትዳር ሴቶችን የፍትዎት ፍላጎት እንዳይኖራቸው ወይም እንዲጠፋባቸው ሊያደረጉ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከእነርሱም ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ እንቃኛለን:-

**1) ፍላጎት ሳይኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸማቸው**

ባለትዳር ሴቶች የግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዲጠፋባቸው ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል የመጀመሪያው ፍላጎት ሳይኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ነው። ብዙ ጊዜ ሚስቶች የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ሳይኖራቸው እንዲሁ በባሎቻቸው ጥያቄ፣ ፍላጎትና አስገዳጅነት ብቻ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ይደረጋሉ። ያለሚስቶች ፍላጎት ወይም ፈቃደኝነት እንዲሁ በተለያየ መንገድ በማስገደድ የግብረ ስጋ ግንኙነት ውስጥ እንዲገቡ ሲደረጉ እርካታ ፈጽሞ ላይኖራቸው ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ሂደት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ከደስታ ይልቅ ሐዘንተኛ እንዲሆኑና ከእርካታ ይልቅም የሕመም ስሜት እንዲፈራረቅባቸው ያስገድዳቸዋል። ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ወቅት እርካታ ስለማያገኙ ውስጣቸው በጥላቻና በሰቀቀን ይሞላል፡፡ ይህም ከስተት በቀጣዮቹ ቀናት(ጊዜያት) የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ናፍቆት ፈጽሞ እንዳይኖራቸው ሊያደርጋቸው ይችላል።

**2) በሕመም ምክንያት የማህጸን መሳሳት**

በተለይ የማህጸን መሳሳት የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዲያጡ የሚያደርግ ምክንያት ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የማህጸን መሳሳት ሊፈጠር ይችላል። የማህጸን መሳሳት ሴቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት እንዲሰማቸውና የፍትዎት ፍላጎታቸው እንዲቀንስ፣ እንዲጠፋ ብሎም ፈጽሞ ፍላጎት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ስለሚችል አስፈላጊውን የሕክምና ምርመራና ድጋፍ እንዲያገኙ መርዳት ያስፈልጋል።[31]

**3) በከፍተኛ ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት ልምምድ ውስጥ ማለፍ**

ሚስቶች ክርስቶስን እንደ አዳኝና ጌታ መከተል ከመጀመራቸው ማለትም ክርስቲያን ከመሆናቸውና ከጋብቻ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ በግብረ ስጋ ግንኙነት ልምምድ ውስጥ ያለፉ መሆናቸው ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው

[30] Sexuality and Relationship Counseling PP 70
[31] Sexuality and Relationship Counseling pp 71

የሚያደርግ ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ነገሮችን ለምደው መቆየታቸውና ብዙ ጊዜ አዘውትረው መለማመዳቸው አሁን በትዳር ሕይወታቸው ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ሊጠፋባቸው ይላል፡፡ እንደ ቀድሞው የሆነ የፍትዎት ፍላጎት ሳይኖራቸው ነገር ግን ግንኙነታቸውን ከፍትዎት ባለፈ አብሮ በብዙ ነገር እየተረዳዱ መኖር ላይ ትኩረት በማድረግ በትዳር ውስጥ ሊቀጥሉ ይችላሉ።[32]

**4) በሴቶች ላይ የሚፈጠር የሥራ ጫና**

በሴቶች ላይ የሚፈጠር የሥራ ጫናም ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ምክንያት ነው። ከባህል አንጻር አብዛኛውን ጊዜ የቤት ሥራዎች፣ ልጆችን የመመገብ፣ የመንከባከብና ምግብ የማብሰል ኃላፊነቶች ለሚስቶች ብቻ ይተዋሉ፡፡ ሚስቶች የውጭ ሥራዎችን ሲሠሩ ውለው ወደ ቤት ሲመለሱ ከውጭ ሥራዎቻቸው በተጨማሪ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ሁሉ እንዲሠሩ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ገጠመኝ ተዳምሮ መሸከም ከሚችሉት በላይ ከፍተኛ የሥራ ጫና ይሆንባቸዋል። በቤትም ሆነ በውጭ የሚፈጠርባቸው የሥራ ጫና አካለዊ ድካም በማምጣት ሌላ ነገር እንዳያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ የሕይወት ሸክም የስሜትና የስነ ልቡና ጉዳት በማድረስ በፍትዎት ፍላጎታቸው ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ባለትዳሮች በመተሳሰብ የሥራ ክፍፍል ካላደረጉ በስተቀር በሴቶች ላይ ብቻ የሥራ ጫና ማሳረፍ ሊያስመርራቸው፣ ፍላጎት ሊያሳጣቸውና እንዳልተፈቀሩ እንዲያስቡና ለትዳር አጋራቸው ያላቸውን የፍቅር ፍልቀ ስሜት ሊያጠፋባቸው ይችላል። የባለትዳር ሴቶች ከትዳር አጋራቸው ጋር ያላቸው የፍቅር ፍልቀ ስሜት መጥፋት ለፍትዎት ፍላጎት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል።[33]

**5) ከፍተኛ የሆነ ውጥረትና ጭንቀት መኖር**

ሌላው ሚስቶች የፍትዎት ፍላጎት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ተጠቃሽ ምክንያት በግልም ሆነ በትዳር መካከል ከፍተኛ የሆነ ውጥረትና ጭንቀት መኖር ነው። በባለትዳሮች መካከል በብዙ ነገር አለመግባባትና መጋጨት ካለ ሚስቶች ስሜታቸው ስለሚጎዳ ለፍትዎት ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጠፋ የማድረግ አቅም አለው። የተጎዳ ስሜት ሲኖር ባለትዳሮች እርስ በርስ እንዳይቀራረቡ፣ መልካም ተግባቦት እና የጠለቀና የጠነከረ ግንኙነት እንዳይኖራቸው ከማድረጉ ባሻገር ሴቶች በሚኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።

**6) የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ**

ሚስቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዲያጡ በማድረግ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል ሌላው ምክንያት የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው። የስነ ተዋልዶን ሂደት ለማዘግየት ወይም

[32] Sexuality and Relationship Counseling pp 71
[33] Sexuality and Relationship Counseling pp 71





ለማስቀረት በማሰብ ሚስቶች የሚወስዷቸው ብዙዎቹ የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒቶች የሚያመጡት አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ መድሃኒቱን እንደሚወስዱት ሴቶች ስነሕይወታዊ (ተፈጥሯዊ) ልዩነትና እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያው ዘዴ ዓይነት ቢለያይም የጎንዮሽ( ሳይድ ኢፌክት) ተጽዕኖ ማምጣታቸው ግን አይቀሬ ነው። ለአንዳንድ ሴቶች የተስማማው የወሊድ መቆጣጠሪያ ለሌሎች ሴቶች የማይስማማ ሁኖ የሚታየውና ለሁሉም ሴቶች አንድ ዓይነት የሆነ የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሃኒት የማይታዘዝበት አንዱ ተጠቃሽ ምክኒያትም ይህ ነው።[34]

**7) በሴቶች ላይ በሕጻንነት የሚደረግ ግርዛት**

በአንዳንድ ቦታዎች የሚከሰተው በሴቶች ላይ በሕጻንነት የሚደረግ ግርዛት ሌላው ሴቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዳይኖራቸው ተጽዕኖ የሚያሳድር ምክንያት ነው። ካልተገረዙ ሴቶች ይልቅ የተገረዙ ሴቶች ለግብረ ስጋ ግንኙነት ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው። ይህ እንዲከሰት የሚያደርገው በሴት ልጅ ላይ ግርዛት በሚፈጸም ወቅት ለፍትዎት ፍላጎት ሊያነሳሷቸው የሚችሉ ነርቮች መነካታቸው ነው። ይህ ችግር በሕጻንነታቸው ያጋጠማቸው ሚስቶች በትዳር ውስጥ ከባላቸው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎታቸው ደካማ ይሆናል፡፡ በትዳር ውስጥ በግብረ ስጋ ግንኙነት ለባላቸው ሊሰጡት የሚችሉትን ጋርዮሻዊ የደስታ ስጦታና እርካታም መስጠትና መቀበል ያቅታቸዋል፡፡ ይህን ቀውስ ፈጣሪ የሆነው ባህልም ሊወገድ ይገባል። ቀውሱን ፈጣሪ የሆነው ሴት ልጅን የመግረዝ አጉል ልማድና የሚያስከትለውን ችግርም በግልጥ በማሳየት ሕብረተሰባችንን ማስተማር የሚገባ ጉዳይ ሲሆን የሴቶችን ግርዛት ማስወገድ እንዲቻል ጥረቱ መቀጠል አለበት።[35]

**8) በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የተለያየ የሕመም ስሜት መፈጠር**

በተለያዩ ምክንያቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት ሊፈጠር ይችላል። አንዳንዶቹ ዝቅተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆን ወይም ፈጽሞ ፍላጎት አለመኖር፣ በሴቶች ላይ ለፍትዎት ሲነሳሱ የሚመነጭ ፈሳሽ አለመኖር ብልቶታቸው የመድረቅና የመጠንከር ሁኔታ ስለሚገጥማቸው በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሕመም ስሜት ሊፈጠርባቸውና በግብረ ስጋ ግንኙነት ከመደሰት ይልቅ ሊጠሉ፣ ሰበብ እየፈለጉ መከላከልና እንደ መከራ ሊቆጥሩት ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ የሕመም ስሜት ሊፈጠርበት የሚችለበትን ምክንያት ለመረዳት በግልጥነት ማውራት፣ መመካከርና በጋራ መፍትሔ ማፈላለግ ተገቢ ነው።

[34] Sexuality and Relationship Counseling 71
[35] Women and Global HumanRights.http://www2.webster.edu/woolflm/fgm.htmlFemaleGenitalMutilation accessed 05/20/2014

## 3. በወንዶችና በሴቶች ላይ የሚከሰት የቀድሞ የከንፈር ወዳጅን የማሰብ ክስተት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል ሌላው ሁለቱም ጥንዶች ወይም አንደኛቸው የቀድሞ ወዳጅን በማሰብ ከአዲሱ የትዳር አጋር ጋር በደስታ አብሮ ለመኖር መቸገራቸው ነው። እንዲህ ዓይነት ችግሮች በአብዛኛው የሚከሰትባቸው ባለትዳሮች በተለይ በጌታ ከመሆናቸው በፊት የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲያዘወትሩ የነበሩ ናቸው። ሌላው በጌታ ሁነው በመንፈሳዊ ሕይወት በደከሙበት ወቅት የዝሙት ኃጢአት የተለማመዱ ከሆነ በእንዲህ ዓይነት ልምድ ውስጥ ያለፉ የትዳር አጋሮች ተጠቃሽ የሚሆኑ የችግሩ ሰለባዎች ናቸው። ሶስተኛው ምክንያት ከትዳር በፊትም ሆነ በኋላ ለፍትዎት ፍላጎት አነሳሽ የሆኑ ፊልሞችና ቪዲዮዎች ወይም ፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑ ባለትዳሮች ለዚህ ችግር ተጋላጭ ይሆናሉ።

በመጨረሻ ልጠቅሰው የምፈልገው ደግሞ ከጥንዶቹ አንዱ አካል አግብቶ በተለያዩ ምክንያቶች ፍች ከፈጸመ በኋላ ሁለተኛ ጋብቻ ውስጥ በሚገባበት ወቅት ችግሩ ሊያጋጥም የሚችል መሆኑን ነው:: በተለያየ ምክንያት ማለትም የትዳር ጓደኛቸውን በሞት በማጣትም ይሁን ፍች በመፈጸም ሁለተኛ ያገቡ የትዳር አጋሮች የቀድሞ ትዳራቸውን እያሰቡ ከአሁን የትዳር አጋሮቻቸው ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የመርካት እንቅፋት የሚሆንባቸው የስሜትና የስነ ልቦና ተጽዕኖ ያጋጥማቸዋል:: ይህም በትዳር ውስጥ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚገኘውን ደስታና እርካታ እንዳይሰጡና እንዳይቀበሉ በማድረግ ለግጭት ምክንያት ሊሆንባቸው ይችላል። ለየት ያለ ጥንቃቄ ካላደረጉ ችግሩ ወደ ቀድሞ ወዳጆቻቸው እንዲመለሱ ወይም በቀላሉ ለተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ፈተናና ለዝሙት እንዲጋለጡ ሊያደርጋቸው ይችላል። *"ከዝሙት ሽሹ"* /1ኛቆሮ.6፡ 11/

## IV. በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት ለሚፈጠሩት ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መጸለይ፡- እንደ መንፈሳዊ ሰው በጋራ በእግዚአብሔር ፊት መጸለይ /ያዕ 5፡ 13-15፣ ኤር 33፡ 3/

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ መሠረት ባደረገ መንገድ የግል ሕይወታቸውንም ሆነ የትዳር ኃላፊነታቸውን የሚወጡት በራሳቸው ጥረት ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ በመስጠት ከእነርሱ ጋር ይሆናል:: ስለዚህ ይህንን እውነት በመረዳት እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ጥንዶቹ በጋራ ችግሮቻቸውን ይዘው በእግዚአብሔር ፊት መቅረባቸው በጣም አስፈላጊ ነው። ባለትዳሮች ችግር የሆነባቸውን፣ ከአቅማቸው በላይ ያጋጠማቸውንና ለግጭት ምክንያት በመሆን ሰላም የነሳቸውን ሸክም ይዘው ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ዙፋን በእምነት



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

መቅረብ ይኖርባቸዋል። *"እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።"* /ዕብ 4፡ 16/

በጋራ በመስማማት ወደ እግዚአብሔር በጸሎት መቅረባቸው ችግሩ ከአቅማቸው በላይ መሆኑን፣ ለችግራቸው መፍትሔ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዳለ ማመናቸውን፣ በጋራ የተስማሙበት መፍትሔ ለማግኘት አብረው እየተጉ መሆኑን፣ የሚያገኙት መፍትሔ ለትዳራቸው በጋራ እንዲሠራ ፍላጎት ያላቸው መሆኑንና በጋራም ጥረት ማድረጋቸውን አመላካች ሊሆን ይችላል። እነዚህ የጤናማነትና የጤናማ ትዳር አመላካች የሆኑ መሠረታዊ እውነቶች ያሏቸውን ባለትዳሮች የሚረዳ አምላክና አባት፣ ግሩም የሆነ አማካሪ መንፈስ ቅዱስ ለልባቸው በመናገርና በጸጋው እነርሱን በመደገፍ ችግራቸውን ማወቅ እንዲችሉ፣ ለችግራቸው መፍትሔ እንዲያገኙና በሕይወታቸው የሚታነጽ ለውጥ እንዲመጣ አብሯቸው ይሠራል።

### 2. መወጣት፡- ግንኙነትን ለማጠናከር ጥንዶች የየበኩላቸውን ድርሻ መወጣት

በአብዛኛው በቅርብ ጊዜ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የፍትዎት መቀነስ ወይም ተነሳሽነት መጥፋት የሚታየው በሴቶች ላይ ነው። የፍትዎት ፍላጎት ለቀነሰባቸውና ለጠፋባቸው ሚስቶች ባል የሚስትን የፍትዎት ፍላጎትና ስሜት ለማነሳሳትና የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት እንዲኖራት የሚያግዛት እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅበታል:: ይህንንም ማድረግ የሚችለው ከእርሷ ጋር አብሮ ጥሩ ጊዜ በማሳለፍ፣ በማድነቅ፣ በመንከባከብ እንዲሁም በጋራ የስሜት እርካታ ላይ መድረስ እንዲችሉ የሚያግዟቸውን ስሜት ቀስቃሽ ጨዋታዎች በመጫዎትና የተለያዩ ከክርስቲያን ስነ ምግባር ያልወጡ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ቀስቃሽ ድርጊቶችን በመለማመድ ነው። ይህንን ኃላፊነቱን ባል በአግባቡ በመወጣት ሚስትም ኃላፊነቷን ተረድታ ወደ መወጣት እንድትመጣ ጉልህ ሚና መጫዎት ይችላል::

### 3. መበጀት፡- ጊዜ በመበጀት አብሮ ማሳለፍን ማዘውተር

አብሮ የመሆን አስፈላጊነቱ ላቅ ያለ በመሆኑ የትዳርን ግንኙነት ለማጠናከር የአብሮነት ጊዜን መበጀትና ያንን ጊዜም አስደሳችና ፍቅርን ገንቢ በሆነ መንገድ መጠቀም ተገቢ ነው። ለሁሉም ጊዜ አለውና!! ነገርን ጊዜን በአግባብ በመከፋፈል፣ በልክና ለጋራ ጥቅም እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ባለትዳሮች የጋራ ጊዜ እንዳይኖራቸውና ግንኙነታቸውን እንዳያጠናክሩ ከሚያደረጓቸው የተለያዩ ሁኔታዎች መካከል ሥራ፣ ትምህርት፣ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራምና አገልግሎት ተጠቃሽ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ጊዜ እያላቸው ነገር ግን ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር አብረው ጊዜ እንዳያሳልፉ የመገናኛ ብዙሃንና ማሕበራዊ ድረ-ገጾች ማለትም ቴሌቪዥን፣ የኢንተርኔት መረብ፣ ፌስ ቡክ፣ የቤት ሥራ፣ የቤተ ዘመድ አብሮ መኖር የመሳሰሉ ችግሮች ተጽዕኖ ያሳድሩባቸዋል። ሌሎች ባለትዳሮች ደግሞ ጊዜ እያላቸው ነገር ግን አብረው ለማሳለፍ የማይስማሙ፣

አብረው ቢሆኑ በጋራ የሚያወሩት የሌላቸው፣ ሲያወሩም የማይግባቡ፣ የተግባቦት ችግር ያለባቸውና በተቻለ መጠን አብረው ላለማሳለፍ ሰበብ የሚፈልጉ ጥንዶች ናቸው። እነዚህን ሁሉ ችግሮቻቸውን በመረዳት በተቻለ መጠን ያላቸውን ጊዜ ለትዳራቸውና ለቤተሰባቸው በመስጠትና አብሮ በማሳለፍ የትዳር ግንኙነታቸው ይበልጥ እንዲጠናከር እድል የሚሰጡና የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ የሚጠቀሙ ባለትዳሮች ወደመሆን ለመለወጥ መትጋት ይጠበቅባቸዋል።

ለጠበቀና እጅግ በጣም ለጠለቀ ግንኙነት አብሮ ጊዜ ማሳለፍ፣ ጊዜ መበጀት፣ ጊዜን በአግባብ መጠቀም ብልህነት ነው። ሊረሳ የማይገባው ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎት ባለቤት መሆንና የግብረ ስጋ ግንኙነት በማድረግ በጋራ እርካታንና ደስታን ማግኘት አብረን በጋራ በምናሳልፈው ጣፋጭ ጊዜ ሊወሰን እንደሚችል ነው፡፡ ይህንን መረዳትና ሰበብ ፈልጎ ከትዳር አጋር ጋር አብሮ መልካም ጊዜ ማሳለፉን መለማመድ በትዳር ውስጥ የራሳችንን አስደሳችና ደስተኛ ትንሽ ዓለም በመፍጠር አርፈንና ረክተን እግዚአብሔርን በማክበርና በመተናነጽ ኅብረት የምንኖርበት መሠረት ነው።

**4. መነጋገር፡- በጋራ በመነጋገር ፍላጎትን መግለጥ**

ባለትዳሮች አብሮ ለመሆን የጋራ ጊዜ በመበጀት ያስፈለጋቸው በንግግር (በቃላት) የማይገለጡ የደስታ ጊዜያቶች ከማሳለፍ ባሻገር በጋራ መነጋገር፣ መወያየትና ፍቅርንም በቃላት መግለጥ የሚችሉበት ጊዜ እንዲኖራቸው ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ኅብረት በባለትዳሮች መካከል በጣም አስፈላጊና አስበውበት ሊፈጥሩትና ሊጠቀሙበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ባለትዳሮች ቢያንስ በቀን ውስጥ በአራት ክፈለ ጊዜያቶች ለአራት ደቂቃዎች ቢነጋገሩ መልካም ነው ተብሎ ይታመናል።[36]

ከእነዚህ አራት ክፍል ጊዜያት፡- **የመጀመሪያው** ማለዳ ከእንቅልፍ ሲነሱ ለአራት ደቂቃዎች የሚለዋወጡት ንግግር ነው፡፡ **ሁለተኛው** ደግሞ አብረው ቆይተው አንደኛው አካል በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰኑ ሰዓቶች የሚለይ ሲሆንና ስንብት ሲያደርግ ያሉት አራት ደቂቃዎች ንግግር ነው። **ሶስተኛው** ክፍለ ጊዜ ጥንዶቹ ተለያይተው ቆይተው እንደገና ሲገናኙ የሚነጋገሩባቸው የመጀመሪያዎቹ አራት ደቂቃዎች ናቸው፡፡ **የመጨረሻው** አራተኛው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ወደ መኝታ በሚሄዱበት ሰዓት የሚደረግ የአራት ደቂቃዎች ንግግር ነው።[37] በዚህ የግንኙነት ሞዴል የክፍለ ጊዜ ክፍፍል ማሳየት የተፈለገው ለጤናማ የትዳር ግንኙነት መልካም የሆነ ተግባቦት አስፈላጊ እንደሆነ ነው። የጤናማ ባለትዳሮች አንዱ መለያ በየጊዜው የሚያወሩ፣ የሚነጋገሩና የሚግባቡ መሆናቸው ነው።

[36] Sexuality and Relationship Counseling

[37] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

ለግብረ ስጋ ግንኙነት መነሳሳት እንዲቻል በጋራ ማውራት ተገቢ ነው። በተለይ አንሶላ ውስጥ በመሆን ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅትና ከግብረ ስጋ ግንኙነት በኋላ የሚደረጉ የጋራ ምክክሮች(ውይይቶች) ጠቀሜታቸው ላቅ ያለ ነው። ይህ መልካም የተግባቦት ሂደት የጥንዶቹ የጋራ የተግባቦት ደረጃ እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ አንዱ ለሌላው ትኩረት፣ ዋጋና እንክብካቤ የሰጠና የሚሰጥ መሆኑን አመላካች ነው። ጥንዶቹ ባላቸው ነፃነት የተሞላው ተግባቦት አንሶላ በመጋፈፍ ወቅት እርስ በርስ መጨዋወት፣ ለሩካቤ ስጋ የሚያነሳሳ ንግግርና ወሬ በማውራትና ሁኔታዎችን በመቀየር ምቹ ኅብረቶችን የመፍጠር ጤናማነትና መንፈሳዊነትም ነው።

**5. መደባበስ፡- አንዱ የሌላውን የሰውነት ክፍል መደባበስ /መኃ 4፡ 1 - 16፤ 8፡ 1-4/**

የትዳር ጓደኛን የሰውነት ክፍል መነካካት አንዱ የፍቅር መግለጫና የግብረ ስጋ ግንኙነትን መቀስቀሻ መንገድ ነው። አንዱ የሌላውን የሰውነት አካል መነካካት ሲባል መሳሳም፣ መዳሰስ፣ መተቃቀፍ፣ እጅ ለእጅ መያያዝ፣ የተለያዩ የሰውነትን ክፍል መነካካትን ሊያጠቃልል ይችላል። የባለትዳሮች የግብረ ስጋ ግንኙነት የጋራ የሆነ መጣጣም እንዲኖርበትና የሚያስገኘውም እርካታ ከፍተኛ እንዲሆን አካላዊ መነካካት ጠቃሚ ነው። አንዲት የእግዚአብሔር ሴት የሆነች መምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪዎችን ስለጋብቻ ትምህርት በምታስተምርበት ወቅት "**በአፍሪካውያን ባለትዳሮች ዘንድ ሶስት ጨለማዎች አሉ**" በማለት አንድ የተጠና ጥናት አካፈለቻቸው። እነርሱም በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት የሚታዩ ጨለማዎች ሲሆኑ፡- የመጀመሪያው ጨለማ ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት መብራት ማጥፋት ነው፡፡ ሁለተኛው ጨለማ በብርድ ልብስ ውስጥ መግባትና መሸፈን ነው፡፡ ሶስተኛው ጨለማ ደግሞ አይን በመጨፈን የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ናቸው።[38]

አንዳንድ ቦታ ላይ ምናልባት የኑሮ ሁኔታ፣ ባህልና የጥንዶቹ የጋራ የመግባባት ደረጃ አደገ ቢባል እንኳን ከሶስቱ ጨለማዎች ሁለቱ ወይም አንዱ ጨለማ መኖሩ የግድ ወይም አይቀሬ ሊሆን ይችላል። የጥናቱም ሆነ የእኔ የጽሑፌ ሃሳብ ፍጹም ግልጥ በሆነና ክርስቲያናዊ ስነምግባርን በጠበቀ መንገድ አካላዊ መነካካት ያለበት ስሜት ለስሜት የሆነ ግንኙነት አካላዊ መቀራረብንና ለግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት መነሳሳትን የመፍጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ለማሳየት ነው።

**6. መሆን፡- በርኅራኄ የተሞላና በመልካምነት የታነጸ ማንነት ያለን መሆን**

ሌላው አስፈላጊ ነገር ከትዳር አጋር ጋር አብሮ ጊዜ ከማሳለፍ፣ ከመነጋገርና ከአካላዊ መነካካት ጋር ፍቅርና ርኅራኄ በተሞላ ማንነትና በበጎነት መልካም የሆነ

[38] Addis Ababa Bible Collage. Marriage course class lecture 2002.

ግንኙነት መፍጠር መቻል ነው። ስሜትን የሚጎዳና ተነሳሽነትን የሚያጠፋ ከማንኛውም ክፉና ራስ ወዳድ ከሆነ ማንነት ራስን መጠበቅና ክፉ ባህርይዎችን ከሕይወት፣ ከግንኙነት ማስወገድ ክርስቲያናዊ ግዴታችንና የመልካም ባለትዳርነት መለያችን ሊሆን ይገባል። ፍቅርን በተግባርና በመልካም ባህርይ መገለጥም ይገባናል። *"ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።"* /1ኛዮሐ 3፡ 18/

## 7. መራቅና መርዳት፡- ስሜትን ከሚጎዱ ነገሮች መራቅና ሌላውም የትዳር አጋር እንዲርቅ መርዳት

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዱ የሌላውን ስሜት ሊጎዳ የሚችል ወይም የሚጎዳ ድርጊት ሊፈጽም ይችላል። በማወቅ የሚደረግን ጉዳት በመጸጸትና በይቅርታ ማስተካከል አስፈላጊ ነው። ባለማወቅ አንዱ የሌላውን ስሜት በሚጎዳበት ወቅት ተጎጅው አካል ስሜቱን የሚገልጥበትና የሚያሳውቅበት መንገድ መፈጠር መቻል አለበት። በወቅቱ የሚሰማንን ስሜት በመግለጥ መፍታትና መግባባት ካልተቻለ የስሜት መራራቅ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ያለመነሳሳት ሊያመጣና የጥንዶችን ግንኙነት በማሻከር ሊያለያይ ይችላል። የፍች የመጀመሪያው እርምጃ በስሜት በመራራቅ መፋታት መጀመር ነው። ጥንዶች እርስ በርሳቸው ለየት ያለ እንግዳ የሆነ መልካም ያልሆነ የስሜት ለውጥ ሲያዩ በእርጋታ ችግሩ ምንድን እንደ ሆነ በመጠየቅ ስሜታቸውን የጎዳውን ጉዳይ የማጣራትና ፈጥኖ መፍትሔ የማፈላለግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ባለትዳሮች ይህን ማድረጋችን ለትዳራችን፣ ለአካላዊ፣ ለመንፈሳዊ፣ ለስነ ልቦናዊ ጤንነታችንና ለማሕበራዊ ግንኙነታችን ምትክ የለሽ የሆነ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

## 8. መመርመር፡- የሕክምና ባለሙያ በማነጋገር መመርመር

በባለትዳሮች መካከል ሚስቶችን ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደረገውን ችግር ለመረዳት የሐኪም ወይም የባለሙያ እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ይህ በሚሆንበት ወቅት ወደ ሕክምና ባለሙያ በመሄድ ለግብረ ስጋ ግንኙነት ተነሳሽነት እንደጠፋባቸው በግልጥ በመናገርና ምርመራ በማድረግ የችግሩን ምንነት ሊያረጋግጡ ይገባል። በሕክምና ችግራቸውን ያረጋገጡ ሚስቶች (ጥንዶች) በሐኪም የሚታዘዝላቸውን የሕክምና ክትትል በመቀጠል መፍትሔ በጋራ እንዲያፈላልጉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በሰለጠኑ አገሮች የተለያዩ ክርስቲያን ፕሮፌሽናልና ክሊኒካል የሆነ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል ለተጠቀሰው ችግር ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር ተያዥነት ያላቸው ችግሮችን ለመፍታት የሰለጠኑ ባለሙያዎች መኖራቸው ጠቃሚ ነው። በምድራችን በተለያዩ ሙያዎችና ክህሎቶች የሰለጠኑ ባለሙያ የሆኑ ክርስቲያን አማካሪዎች ቢኖሩና ሕዝቡም የምክር አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን ችግሩ ባለትዳሮችን ከማጥቃቱና ፍችን ከማስከተሉ በፊት አስፈላጊውን እርዳታ





በማግኘት ችግሮቻቸውን ሊቀርፉ ቢችሉ ትልቅ ደስታን ይሰጠናል፡፡ ይህ ተከናውኖ ባለትዳሮች ችግራቸውን ሲቀርፉ ማየት የውስጥ ጩኸቴና ጸሎቴም ነው።

## 9. መቻል፡- በወንድና በሴት መካከል ያለውን የተፈጥሮ ልዩነት መረዳት መቻል

ባለትዳሮች በወንድና በሴት መካከል ያለውን የተፈጥሮ ልዩነት መረዳት መቻላቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርጉበትም ወቅትም ሆነ በአጠቃላይ በትዳር ውስጥ በሚኖራቸው ኅብረት በመግባባት፣ በመቀባበል፣ በመረዳዳትና አንዱ ለሌላው የደስታና የእረፍት ምክንያት በመሆን እንዲኖሩ ከፍተኛ እገዛ ያደርግላቸዋል። ስለዚህ ወንድና ሴት ሆነን በመፈጠራችንና በፆታችን ልዩነት ምክንያት የሚመጣውን ተጽዕኖ፣ የፍላጎት፣ የጸባይ፣ የእሴትና የእይታ ልዩነታችንን በመገንዘብ ትዳራችንን ማነጽ ይኖርብናል። ይህ ዓይነቱ ግንዛቤ ልዩነታችንን ለማጥበብ፣ ለመረዳዳትና የጋራ ለሆነ ግብረ ስጋዊ ግንኙነት እርካታ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም። ክርስቲያን ባለትዳሮች ልዩነታቸውን በመረዳት በልዩነታቸው ምክንያት በመካከላቸው ሊፈጠር የሚችለውን ያለመጣጣምና ግጭት አስወግደው እርስ በእርስ በመሟላት በሚገኘው እርካታ፣ ሰላምና እረፍት ደስተኛ ሆነው እንዲኖሩ ለማገዝ በሚከተለው ሰንጠረዥ በወንድና በሴት መካከል ያለውን ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዘ የተፈጥሮ ልዩነት ባጭሩ እንቃኛለን፡-

<u>በግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ የባልና የሚስት ተፈጥሯዊ ልዩነት</u>

| ተ.ቁ | ተፈጥሯዊ ልዩነት | ወንዶች (ባሎች) | ሴቶች (ሚስቶች) |
|---|---|---|---|
| 1 | ጠባይ፣ ሁኔታ | አካላዊ | ግንኙነታዊና ሁለንተናዊ |
| 2 | መነሳሳት | አካላዊ አቋም ላይ ያተኮረ<br>እይታ<br>መዓዛ (ሽታ)<br>ተግባር | ማንነት<br>ንኪኪ<br>ጠባይ፣ ሁኔታ፣ አኳኋን<br>ቃላት/ ንግግር/ |
| 3 | ፍላጎት | መከበር<br>ሰውነት (አካላዊ የሆነ ግንኙነት) | መከበር<br>ስሜታዊ ግንኙነት<br>የቀረበ ግንኙነት |
| 4 | ለግበረ ስጋ ግንኙነት ያላቸው ምላሽ | ላይ በላይ (ግልብ የሆነ ስሜታዊነት)<br>ፈጣን የሆነ<br>አሳባቸው በሌላ ነገር ቶሎ የማይወሰድ | ውህደት<br>የዘገየ (ረጋ ያለ)<br>በተለያዩ ሁኔታዎች ቶሎ አሳባቸው ሊወሰድ የሚችል |
| 5 | ወሲባዊ እርካታ | ባጭር ጊዜ (በቶሎ) የሚጠናቀቅ<br>የጋለ ስሜት<br>አብዛኛው አካላዊ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው። | ረዘም ያለ ጊዜ የሚፈልግ (በጥልቀት)<br>አብዛኛውን ጊዜ ስሜታዊ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸው ነው። |

ሰንጠረዥ 2[39]

## 10. መጠንቀቅ፡- የባልና ሚስት የሚፈልጉትን ለይተው ማወቅና ለጋራ ፍላጎት መጠንቀቅን መለማመድ

አብዛኛውን ጊዜ ባሎች ከሚስቶቻቸውና ሚስቶች ከባሎቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት በምክር አገልግሎት፣ በጋብቻ ትምህርትና በውይይት ወቅት ፍላጎታቸውን በስሞታ መልክ ሲናገሩ ይደመጣሉ:: በእንደዚህ ዓይነት የውይይት ወቅት ስሜታቸውን ሲገልጡ ያንጸባርቋቸውን ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በተለይ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን እና ስነ ልቦናዊና አካላዊ መቀራረብን በተመለከተ ያላቸው ልዩነት በሚከተለው ሰንጠረዥ (ቻርት) ባጭሩ ቀርቧል። ይህን አሳብ በሰንጠረዡ ውስጥ ማቅረብ የተፈለገው በቻርቱ ውስጥ የቀረበው ሃሳብ በሁሉም ባለትዳሮች ዘንድ ይከሰታል ለማለት ሳይሆን በአብዛኛው ባለትዳሮች ላይ የሚታይ በመሆኑ ነው:: ዓላማውም ባለትዳሮች እርስ በርስ በመረዳዳት የትዳር ጓደኛቸውን ፍላጎት በመገንዘብ አብረው

[39] Dr. Gary & Barbara Rosberg with Ginger Kolbabathe. <u>The 5 sex needs of men and women</u> Tyndale House Publishes, Inc. Carol Stream, illinois 2006.





እንዲኖሩና የትዳር ጓደኛቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅትም መከላከል እንዳይኖር፣ መጣጣም እንዲችሉና አንዳቸው ለሌላቸው የእረፍት ምክንያት እንዲሆኑ እገዛ የሚያደርግ ሃሳብ ለመስጠት ነው።

| ተ.ቁ | ባሎች ከሚስቶች የሚፈልጓቸው፣ የሚጠብቋቸውና ለሚስቶች የሚናገሯቸው፡- | ሚስቶች ከባሎች የሚፈልጓቸው፣ የሚጠብቋቸውና ለባሎች የሚናገሯቸው፡- |
|---|---|---|
| 1 | በግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ንቁ እንድትሆኑልን፣ | በፍቅር በሆነ ስሜታዊ መቀራረብ ቅረቡን |
| 2 | በተለያዩ ጉዳዮች ወንድነታችንን እወቁልን ብሎም በንግግርና በመታዘዝ አክብሮትን ስጡን፣ | ለግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን እንዲሁ አብራችሁን ሆናችሁ እንድትደባብሱን እንፈልጋለን፣ |
| 3 | የምንፈልገውን የመጠየቅ ነፃነት ስጡን፤ በተለይም በግብረ ስጋ ግንኙነት መቀጣት ይቁምልን፣ | የጠለቀ የፍቅር ግንኙነት እንዲኖርን እንጂ የስሜታችሁ ማርኪያ ብቻ መሆን እንደማንፈልግ ተረዱን፣ |
| 4 | የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎታችንን ተረዱንና በጠየቅን ወቅት አዎንታዊ ምላሽ ስጡን እና | ሁለንተናዊ የሆነ ንጽህናን ከእናንተ እንፈልጋለን ይህን ስንል የአይን፣ የስሜት፣ የመንፈስና የአካል ንጽህና እንዲኖራችሁ እንፈልጋለን እና |
| 5 | ታማኝ ሁነን እንድንቀጥል የእናንተን ሁለንተናዊ እርዳታ እንፈልጋለን የሚሉ ናቸው:: | ታማኝ ሁኑልን የሚሉ ናቸው:: |

ሰንጠረዥ 3[40]

[40] Focus on The Family, <u>The first Five Years of Marriage</u>: Tyndale House publishing Inc Carol stream: Illinois, 2006. pp168-173

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ዘጠኝ (9)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የግብረ ስጋ ግንኙነትን ምንነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱን በመጥቀስ ተወያዩበት፡፡
2. በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ያለውን ዓላማና ሚና በመግለጥ በፍጹም ነፃነት ተነጋገሩበት፡፡
3. በመካከላችሁ በግብረ ስጋ ግንኙነት መጣጣም ከሌለ ችግሩ ጎልቶ የሚታየው በማን ላይ እንደሆነና መንስኤው ምን ሊሆን እንደሚችልና ማረጋገጫዎችን በመጥቀስ በግልጥነት ተወያዩበት፡፡
4. በጋራ በወያየት፣ የችግሩን መንስኤ በመረዳትና በጋራ የመፍትሔ ሃሳብ በመፈለግ አስፈላጊ ነው የምትሉትን ወቅታዊ የሆነ እርምጃ ላይ ተወያዩ፡፡ መወሰድ ያለበት እርምጃ ምንድን ነው ትላላችሁ? በጋራ በመወያየት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመውሰድ አቅዱ፡፡
5. በወንዶችና በሴቶች /በባልና በሚስት/ የግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ሊፈጠር ስለሚችል ልዩነት በግልጥነት በመወያየት ወደ ፊት ልዩነትን በመረዳት ለማጥበብና በጋራ ለመረዳዳት ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
6. እንደ ባለትዳር አንዱ ከሌላው ምን እንደምትፈልጉ ስሜታችሁንና ፍላጎታችሁን በነፃነት የምትገልጹበት እንዲሁም የሌላውን አካል ፍላጎት ለመረዳት የምትችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለመረዳዳት ጥረት በማድረግ ተወያዩበት፡፡





# ምዕራፍ አስር(10)

# የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት

## I. የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምንነት

የጥንዶች መሠረታዊ የእምነት ልዩነት የምንለው ጥንዶቹ የተለያየ ሃይማኖት ተከታይ በሚሆኑበት ጊዜ የሚያጋጥም ልዩነት ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ክስተት ጥንዶቹ በጌታ ከመሆናቸው በፊት የተጋቡ ሲሆንና አንዳቸው ብቻ ጌታን ሲቀበሉ ሊፈጠር ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አማኝ የሆኑ ወንድሞች ወይም እህቶች በሕይወታቸው ድካም ላይ በሆኑበት ወቅት ወይም በአስተሳሰብ መንጋደድ፣ ትክክለኛ ባልሆነ ፍላጎት ወይም በሌሎች ምክንያቶች አማኝ ካልሆኑ ሰዎች ጋር በትዳር በሚጣመሩበት ጊዜ የእምነት ልዩነት ሊፈጠር ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ጥንዶች ወደ ጽድቅ በሚወስደው የደህንነት መንገድ ላይ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡

የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት የምንለው ደግሞ በክርስቶስ አምኖ በመዳን ጉዳይ ላይ አንድ አቋም ኖሯቸው ነገር ግን በሌሎች የቤተ እምነቶች የዶክትሪንና የልምምድ ልዩነቶች አለመስማማትን የሚያመለክት ነው። በአንድ ቤተ እምነትና በአንድ አጥቢያ ውስጥ አባል ሆነው በመንፈሳዊ መረዳትና በሕይወት ብስለት ልዩነት ያላቸው ባልና ሚስትም የመረዳት ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ መንፈሳዊ መረዳት ስንል በየጊዜው በክርስትና ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል አብርሆት መለወጥ፣ ማደግ፣ መብሰልና መጠንከር የሚመጣ የክርስትና ሕይወት እድገት ባህርይ ነው /**1ኛጴጥ 2፡ 1-2**/፡፡ ይህ ርዕስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በተፈጠረው የመረዳት ልዩነት ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በመረዳት ለመቀነስና በጋራ በእርጋታ የእግዚአብሔርን ቃል በልበ ሰፊነት በመመርመር ለመማር፣ ለመለወጥና ለማደግ ራስን፣ ትዳርንና ቤተሰብን ለሕይወት ኃላፊነት ለማዘጋጀት እንዲችሉ ክርስቲያን ባለትዳሮችን ለመርዳት ነው።

## II. በመንፈሳዊ ሕይወትና መረዳት ልዩነት መሠረት የግጭት መንስኤዎች

ጥንዶች የተለያዩ ሰዎች እንደመሆናቸው በመካከላቸው የዕድሜ፣ የአካል፣ የመንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ፣ የመንፈሳዊ ዕድገት፣ የብስለት ደረጃና አንዳንድ ጊዜም የሃይማኖት ልዩነቶች ሊኖሯቸው ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ በጥንዶች መካከል ያለው የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ደግሞ በልዩ ልዩ ገጠመኞች ወቅት በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑ አይቀሬ ነው። በእርግጥ በመንፈሳዊ ብስለትና እንቅስቃሴ ሁሉ ባልና ሚስት አንድ ዓይነት አንሆንም፡፡ ደግሞም በሁሉም ነገር አንድ ዓይነት መሆን የለብንም! ነገር ግን ልዩነታችን ለግጭትና ላለመግባባት ምክንያትን መስጠት የለበትም፡፡ ለምሳሌ፡- የንጉስ ዳዊትንና የሚስቱን የሜልኮልን የመንፈሳዊ ሕይወትና የመረዳት ልዩነት ልንጠቅስ እንችላለን፡፡

ንጉስ ዳዊት እግዚአብሔርን ለማክበር በሁለንተናዊ መሰጠት አምልኮውን በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበ ሲሆን፡፡ ለእግዚአብሔር ክብር በሚያደርገው አምልኮ ምክንያት መናቅም ቢደርስበት እንኳን ያለጸጸትና ያለማመቻመች ለንጉስነት ክብሩ ሳይጨነቅ አምልኮውን ለአምላኩ ለማቅረብ የማያወላውል አቋም ይዞ ነበር፡፡ እውነተኛው የሕይወቱ ኃላፊነትም ራሱን በመናቅና ዝቅ በማድረግ እግዚአብሔርን ማክበር መሆኑን በአግባቡ ተረድቶ ስለነበር በንግስና ስርዓት ጭምብል ውስጥ ተደብቆ ግላዊ ክብሩን መንከባከብ ላይ ያተኮረ አቋምና ኑሮ አልነበረውም፡፡ በተቃራኒው ሚስቱ ሜልኮል ደግሞ እግዚአብሔርን ለማክበር ዳዊት ያደረገውን የአምልኮ ተግባር ለንጉስ የማይገባ እንደሆነ አቋም ይዛ ነበር፡፡

ንጉሱ ዳዊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው አምልኮም የንጉስነት ክብሩንና ማዕረጉን በሚመጥንና ማሕበራዊ ክብሩን በጠበቀ መልኩ ብቻ ሊደረግ ይገባል የሚል አመለካከት ታራምድ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት መረዳት ላይ የተመሠረተ አቋም ስለነበራትም ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ግላዊና ማሕበራዊ ክብሩን በመጣል ባደረገው እንቅስቃሴ ደስ ባለመሰኘት ናቀችው፡፡ ባደረገውም ነገር መሸማቀቅና እፍረት እንዲሰማው ተጽዕኖ ልታደርግበት ሞከረች፡፡ ይህም ክስተት መጽሐፍ ቅዱስ *"የእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ በደረሰ ጊዜ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች ንጉሡም ዳዊት ሲዘፍንና ሲጫወት አይታ በልቧ ናቀችው።"* **/1ኛዜና 15: 29፤ 2ሳሙ 6: 20-22/** በማለት እንደሚናገረው በግንኙነታቸው ላይ ግልጥ የሆነ ክፍተትና አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮ ነበር። ስለዚህ ክርስቲያን ባለትዳሮች ይህን እውነታ በመረዳት በመካከላቸው ያለውን የብስለትና የመረዳት ልዩነት ለማጥበብ፣ እርስ በእርስ በሚገባ ለመተዋወቅና የተሻለ የሚባለው አካል ደካማውን በመረዳት፣ በመሸከምና በመታገስ በጥሩ ኅብረትና ስምምነት አብረው ጌታን በማክበር ሊኖሩ ይገባል፡፡ እንደዚህ ማድረጋቸው በመጀመሪያው አስር አመታት የጋብቻ ዘመናቸው የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት ደረጃና የመረዳት ልዩነት ምክንያት ሊፈጠሩ በሚችሉ ችግሮች ሰበብ የሚነሱ ግጭቶችን ለመቀነስና በመልካም ሁኔታ ለመቆጣጠር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። እነዚህን በትዳር ውስጥ ለግጭትና አለመግባባት መፈጠር ምክንያት የሆኑ ከእምነትና ከመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን በሚከተሉት ነጥቦች በመቃኘት ጥንዶች ግንዛቤ እንዲያገኙና መፍትሔዎችን በመጠቀም ከችግሩ ትዳራቸውን እንዲጠብቁ የመርዳት ጥረታችንን እንቀጥላለን፡፡

## 1. አንዱ አካል በጌታ ያላመነ መሆን

ይህ ርዕሰ ጉዳይ መነሳቱ በክርስቲያናዊ ትዳር ያመነ ካላመነ ጋር ሊጋቡ ይችላሉን? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። እውነት ነው ያመነ ካላመነ ጋር መጋባት እንደሌለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይናገራል። በአካባቢያችንና በየአጥቢያች ቤተ ክርስቲያናችን እንደምናየው እንዲሁም በማማከር አገልግሎት ካጋጠሙኝ ልዩ ልዩ ክስተቶች በመነሳት





ለምን አማኝ ያላመነን ሊያገባ እንደሚችል በሚከተሉት አሳቦች ባጭሩ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

ችግሩ በሁሉም ቦታ የሚታይ ቢሆንም ከአገር ቤት ውጭ የሚኖሩ አማኞች በአገር ቤት ከሚኖሩት ይልቅ ለዚህ ችግር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው። በጌታ ሆነው ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻ የሚፈጽሙ ወገኖች ይህን የሚያደርጉባቸው የየራሳቸው ምክንያቶች አሏቸው፡፡ **አንዳንዶች** ኑሮን ለማሸነፍ፣ ሌሎች ማግባት ያለባቸው ጊዜ ያለፈባቸው ሲመስላቸው፣ ተገቢ ባልሆነ መቀራረብ ምክንያት፣ ውጫዊ በሆነ ነገር ሲሳቡና ሲፈተኑ፣ በወቅቱ ከጌታ በመራቅ ዓለማዊነት ሲያሸንፋቸውና ከጋብቻ በኋላ ወደ ጌታ ይመጣል የሚል ተገቢ ያልሆነና የተሳሳተ ተስፋን ምክንያት በማድረግ አማኝ የሆኑ ወንድሞችና እህቶች ከማያምን ሰው ጋር ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ወደ ጌታ ከመምጣታቸው በፊት ትዳር ከመሠረቱ ባለትዳሮች መካከል አንደኛው አካል ብቻ ጌታን የግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል ክርስቲያን በሚሆንበት ወቅት አንዱ አካል አማኝ ሌላው አካል የማያምን የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል።

አማኝና አላማኝ በሆኑ ጥንዶች መካከል ግጭት ቢፈጠር ምንም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። በሁለቱ መካከል ያለው መንፈሳዊ ልዩነት በብርሃንና በጨለማ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያክል ክፍተት ነውና! *"ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?"* **/2ኛቆሮ 6: 14-15/**፡፡ አማኝ የሆነ ወንድም ወይም እህት ከማያምን ሰው ጋር መጋባት ፈጽሞ ስህተት እንደሆነ ማሰብና ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን ያለበት በቅድመ ጋብቻ ወቅት እንጂ ከተጋቡ በኋላ አይደለም፡፡ ባላመኑና አማኝ በሆኑ የትዳር ጓደኞች መካከል በሚፈጠር የማያቋርጥ ግጭት የሚሰቃዩና ብሎም ትዳራቸውን በማፍረስ በፍች የተለያዩ ክርስቲያን ባለትዳሮች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። ነገር ግን አማኞች መረዳት ያለባቸው ስቃዩና ችግሩ ምንም ቢበዛ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የቅዱሳት መጽሐፍትን መርህ ተላልፈው ከማያምን ሰው ጋር በትዳር ከተጣመሩ በኋላ በጌታ ነኝ፣ መንፈሳዊ ነገር አሁን በርቶልኛል፣ ሕይወት አግኝቻለሁ፣ እንደ በፊቱ አይደለሁምና ድሮ ሳይገባኝ የፈጸምኩት ይበቃኛል የመሳሰሉ ምክንያቶችን በማንሳት ትዳራቸውን ለማፍረስ ሰበብ የመፈለግ መብት የሌላቸው መሆኑን ነው።

## 2. የመንፈሳዊ ብስለት ልዩነት

ክርስትና ሁልጊዜ ከክርስቶስ ጋር፣ በክርስቶስና ለክርስቶስ መኖርን የሚጠይቅ የየዕለት ኑሮ ነው። የተለያዩ የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍሎች ሥር መስደድ፣ ማደግ፣ መጠንከርና ወደ ሙላቱ ልክ ማደግ ... በሚሉ አሳቦች የመንፈሳዊ ብስለትን አስፈላጊነት ግልጥ በሆነ መንገድ ያሳያሉ፡፡ *"እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ። ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፥ እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ ምስጋናም ይብዛላችሁ።"* **/ቆላ 2: 6-7/**፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በክርስቶስ ሕጻናት (ብስለት የጎደላቸው አማኞች) እና

ስጋዊያን መሆን እንደማይገባን *"ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና..."* /ዕብ 5፡ 11-14፤ 1ኛቆሮ 3፡ 1-3/ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል።

**አንዳንዶች** ተመስክሮላቸው ወደ ጌታ እንደመጡ ብዙ በክርስትና ሳይቆዩ ወደ ትዳር ዓለም ይገባሉ:: የተወሰነ አመት በክርስትና አስቆጥረው ነገር ግን አጠንክረው ክርስትናን ሳይዙ የፕሮግራም ደንበኛ በመሆን ብቻ አመታትን ይቆጥራሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ከቤተሰብ ክርስትናን ወርሰዋል እንጂ በግላቸው ጌታን የግል አዳኝ አድርገው በመቀበል የተለወጠ ማንነት የሌላቸው ይሆናሉ:: የቤተ ክርስቲያን ስርዓትና ቋንቋ በመልመድ ለጊዜው የሚፈልጉትን እስኪያገኙ ድረስ በማስመሰል መቆየት የሚችሉ ሰዎችን ማየት በአሁኑ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንግዳ ክስተት አይደለም። በእነዚህ ሁሉ መንገዶች ውስጥ እየተጓዙ ያሉ ወገኖች ክርስቲያን በመባል ይታወቃሉ:: በቤተ ክርስቲያን ስርዓት መሠረትም ከክርስቲያን ወገኖች ጋር ትዳር ይመሠርታሉ:: ነገር ግን በዚህ መንገድ ወደትዳር በመግባት የባልና ሚስት ውል የፈጸሙት ክርስቲያን ወንድምና ክርስቲያን እህት ጥቂት ጊዜ አብረው እንደቆዩ በመካከላቸው ሰፊ የሆነ የመንፈሳዊ መረዳትና ብስለት ልዩነት እንዳለ ይገነዘባሉ::

ልዩነታቸውም ልዩ ልዩ ግጭቶችና አለመግባባቶች በመካከላቸው እንዲፈጠር መነሻ ምክንያት ይሆናል:: ይህ ሁኔታ የሚያሳየን በመንፈሳዊ ብስለት ደረጃችንና ለመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት በምንሰጠው እሴት ልዩነት ምክንያት በትዳራችን ግጭትና አለመግባባት የመፈጠር እድሉ ሰፊ መሆኑን ነው:: እንደዚህ ዓይነቱም ልዩነት በሕይወት ለውጥና በማያቋርጥ እድገት ክፍተቱ ካልጠበበ ለፍችም ተጋላጭ ሊያደረገን ይችላል::

## 3. ለቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ያልተመጣጠነ ትኩረት መስጠት

ክርስቲያኖች ከጋብቻ በፊት የነበራቸው ለራስ በራስ የመወሰን፣ ጊዜን ለፈለጉት ጉዳይ የመጠቀም፣ በቤተ ክርስቲያን ባሉት ፕሮግራሞች ሁሉ የመሳተፍና የማገልገል ልምድ በቀላሉ አይለቃቸውም። ወደ ትዳር በሚገቡበትና ወላጅ በሚሆኑበት ወቅት ሁኔታዎች በላጤነትና ልጆች ባልተወለዱበት ወቅት እንደነበረው ላይቀጥሉ ይችላሉ። ቀድሞ የነበረው ልምምድ እንዲቀንስ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር በብስጩነት ስሜታዊ በመሆን ወደ ግጭት ለመግባት ይጋበዛሉ። ትዳርን፣ ቤተሰብን፣ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራምንና አገልግሎትንም ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ ማከናወን ካልተቻለ ሌላኛው ግጭት የሚፈጠርበት ምክንያት መሆኑ የግድ ነው። ሁልጊዜ ሚዛን ያልጠበቀ ድርጊት ሲኖር ማለትም ወደ አንድ ጽንፍ የተለጠጠ አመለካከትና የሕይወት ልምምድ ሲጀመር ጉዳዩ ከተጠበቀው ውጤት የተለየ አቅጣጫ የመያዙ እድል በጣም ከፍተኛ ነው። በቤተ ክርስቲያን የሚከናወኑ የተለያዩ የጸሎት፣ የአምልኮ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ





ጥናት፣ የልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ ፕሮግራሞችና የቤተ ክርስቲያን ትናንሽና ትላልቅ ስብሰባዎች ሁሉ ትርጉም ያለው ጊዜን የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህን ጊዜ ጠያቂ የሆኑ ተግባሮች ከትዳርና ከቤተሰብ ሕይወት ጋር አጣጥሞ ለማስኬድ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ጉዳይ መለየትና መመጠን ያስፈልጋል።

በነገሮች ላይ በግልጥነት ተወያይቶ መግባባትና መረዳዳት እንደተጠበቀ ሆኖ ለትዳርና ለቤተሰብ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ግን የማያወላዳ አቋም ልንይዝ ይገባል። ለትዳራቸው ቅድሚያ በማይሰጡ፣ በጣም መንፈሳዊ የሆኑ በሚመስላቸውና በብዙ ፕሮግራሞች ላይ መገኘትና መሳተፍ አለብኝ ብለው በሚያስቡ አንዳንድ ጥንዶች ትዳር ላይ የማያቋርጥ ግጭት ይፈጠራል:: ግንኙነታቸውም ይሻክራል። መንፈሳዊ እንደሆኑ የሚነግራቸው ስሜታቸውም ሳያስቡት ይከዳቸዋል:: በስተመጨረሻም በትዳር ውስጥ በሚያጋጥማቸው ግጭትና ቀውስ ምክንያት በሚካፈሏቸው መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ብዛትና በሃይማኖት ስርዓቶች ተጀቡኖ መንፈሳዊ ጭምብል የተላበሰው ስጋዊና ያልበሰለ ማንነታቸው በግል ሕይወታቸውና በትዳራቸው ውስጥ የሚገለጥበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህንን በማስተዋልና አርቆ በማሰብ ክርስቲያን ባለትዳሮች እውነተኛውን መንፈሳዊነት በግል ሕይወታችን ከዚያም ከትዳር ጓደኞችን ጋር ባለን ጤናማ ኅብረት እንዲሁም ለቤታችንና ለትዳራችን በምንሰጠው በቂና የተመጣጠነ ጊዜ ልንኖረው ይገባል::

## 4. የራዕይ ልዩነት

የራዕይ ልዩነት ሲባል በሕይወት፣ በኑሮና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ጥንዶቹ የሚኖራቸው የተለያየ እይታ ነው። ለምሳሌ ያክል አንደኛው የትዳር አጋር ስለአገልግሎት ያለው መረዳትና የተሰጠው ራዕይ ከሌላው የትዳር አጋር መረዳትና ራዕይ ጋር ያለውን ልዩነት በብስለት መያዝ ካልተቻለ በመካከላቸው አለመግባባትና ግጭት ሊፈጥር ይችላል። አንዱ የትዳር አጋር ያለው የአገልግሎት ራዕይ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ ካስፈለገ የመጀመሪያውን ትብብር የሚያገኘው ከትዳር አጋሩ ሊሆን ይገባል። ይህ እንዲሆን ራዕይን በግልጥ የማካፈልና አስረድቶ የማሳመን ትጋቱን ተቀባይነት እስኪያገኝ ድረስ በትዕግስት በጋራ በመጸለይና በመወያየት መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ዋጋ ከፍሎ የትዳር አጋርን የአገልግሎት ራዕይ ተካፋይ ማድረግ መንፈሳዊነትም ብስለትም ነው። ራዕይ ከሚጠይቃቸው ነገሮች መካከል አንዱ ተባባሪ ሰዎችን ማፍራት ነው። ይህ አልሳካ ብሎ የትዳር አጋር የአገልግሎት ራዕይ ተባባሪ ከመሆን ይልቅ ተከራካሪና ተቃዋሚ በሚሆንበት ወቅት ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነው:: ግጭቱም ተባብሶ ግንኙነትን ከማሻከር ባሻገር የአገልግሎት ተነሳሽነትንም ሊያጠፋ ይችላል።

## 5. አስራት፣ መባና ስጦታ ላይ የጎላ ልዩነት መፈጠር

በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠረው ችግር አንዱ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ አማኞች እንዲሰጡ የታዘዘውን አስራትና መባ መስጠትና አለመስጠትን

በተመለከተ ካላቸው ልዩነት ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ሰዎች የገቢያቸውን አንድ አስረኛ ማለትም የአስራታቸውን መጠን ሌሎች ጉድለቶችን ይሸፍናል ብለው በማሰብና ጉድለትን ለመድፈን በሚደረግ ውጥረት አስራትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማምጣትና ለመስጠት ሲቸግራቸው ይደመጣሉ። አንዳንዶችም ስለአስራት አዲስ ኪዳን ምንም አይልም የሚል ማብራሪያ በማቅረብ አስራትን ለቤተ ክርስቲያን ከመስጠት ይልቅ ላለመስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ምክንያት ማቅረብ ይመርጣሉ። አስራት ማውጣት አንዱ ከገንዘብ በላይ እግዚአብሔር የሕይወታችን ገዥና አለቃ መሆኑን የምንመሰክርበትና ሁሉንም እርሱ እንደሰጠንና ሁሉ የእርሱ እንደሆነ እውቅና የምንሰጥበት ነው።

## III. በእምነትና በመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. *መሆን፡- በጌታ የሆነው አካል በክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ምሳሌ መሆን*

ዳግም ልደትን በማግኘት ክርስቲያን ያልሆኑ የትዳር ጓደኞች ክርስትናን ባለመረዳትና በሚከተሉት እምነት ተጽዕኖ ምክንያት አማኙን የትዳር ጓደኛቸውን መቃወም ጽድቅ አድርገው በመቁጠር በትዳር አጋራቸው ላይ ጎጂ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ይችላሉ። በአንዳንዶቹ በተለያየ የሰይጣን አሠራር ተጽዕኖ ውስጥ መሆንና በተለያዩ ሱሶች በመጠመድ ምክንያት ግጭቱ ሊባባስ ይችላል። በዚህ ወቅት ክርስቲያን የሆነው አካል ክርስቲያናዊ በሆነ ሕይወት ምሳሌ መሆን ይጠበቅበታል።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያን በሆኑ የትዳር ጓደኞች በኩል የሚታየው ችግር የክርስትናን ሕይወት የሚያስነቅፍ ኑሮ መኖራቸው ነው። በአሁኑ ወቅት ከማያምኑት ያልተሻለ አንዳንዴም የባሰ የስነ-ምግባር ዝቅጠት በኑሯቸው የሚያሳዩ ክርስቲያን የትዳር ጓደኞችን ለማየት ብዙ ጥረት አይደለም። የማናስተውላቸው ነገር ግን የሕይወትን ንጽህናና የትዳርን ግንኙነት የሚያቫክሩ እንደ ቁጣ፣ ስድብ፣ ሐሜት፣ ምሬት፣ ማኩረፍ፣ የስንፋና ንግግር፣ የትዳር ጓደኛን አለማክበርና ገንዘብን መውደድ የመሳሰሉ ኃጢአቶች በክርስቲያን ባለትዳሮች ዘንድ መዘውተራቸው ክርስቲያን የትዳር አጋሮች የክርስቲያናዊ ስነ-ምግባርን ክቡርነት ዋጋ ዝቅ ያደረገ አኗኗር መከተላቸውን የሚያሳዩ ናቸው። እንዲህ አይነት ኑሮ በክርስቲያን ሕይወት ሊታይና ሊዘወተር እንደማይገባ *"እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው። በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል። እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ። አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ። እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።"* /ቆላ 3፡ 5-10/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል መርህ አስረግጦ ይነግረናል።





በተለይም በወንጌሉ እውነት አማኝ ያልሆኑ የትዳር ጓደኞች ካሉን እንደ ክርስቲያን የላቀ፡ ምሳሌነት የተሞላ፣ ክርስቶስን የሚገልጥና የሚያሳይ ኑሮን በየዕለቱ በመኖር ክርስቶስን ያለመቀበል ፍላጎት እንዳይኖራቸው የሚያደርግን ማንኛውንም እንቅፋት የሚሆን ነገር ከቤታችንና ከኑሯችን ልናስወግድ ይገባል፡፡ ይልቁንም በሕይወት ተማርከው ክርስቶስን እንዲያምኑና እንዲከተሉ ለማገዝ መልካም ተፅዕኖ ማምጣት የሚችል መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የሕይወት ክቡርነት የሚያሳይ ኑሮ የመኖር ኃላፊነት አለብን። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ *"በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።"* /1ኛጢሞ 4፡ 12/ በማለት የመከረውን ምክር እንደ መርህ በመውሰድ አማኝ የሆኑ የትዳር ጓደኞች ምሳሌነታቸው አማኝ ባልሆነ የትዳር አጋር ዘንድ አክብሮትን የሚያስገኝላቸውና ንቀትን የሚያርቅላቸው ሊሆን ይገባዋል።

### 2. *መፍቀድ፡- ሁልጊዜ ለመማርና ለማደግ መፍቀድ*

የክርስትና ሕይወት ከዳግም መወለድና መንፈሳዊ ሕጻን ከመሆን ይጀምራል። ይህንን ሕይወት የጀመሩ አማኞች ሁሉ ከሕጻንነት ሕይወት ለመውጣት ሁል ጊዜ ለመማርና ለማደግ የሚፈልጉ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመሆን ትጋት የሕይወት ዘመናቸውን መምራት አለባቸው፡፡ በክርስትና ሕይወት ሁሉን አውቆ እድገትን መጨረስ የሚባል ነገር የለም። ነገር ግን ሁልጊዜ በእድገትና ክርስቶስን በመምሰል የማያቋርጥ ምኞት፣ እርምጃና ግስጋሴ መስመር ላይ እየተጓዝን ዘመናችንን ለመፈጸም ዝግጁ መሆን አለብን። ከዚህ የሕይወት መርህ ጋር ከተግባባን ደግሞ *"እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፥ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።"* /1ኛጴጥ 2፡ 2-3/ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል በመረዳት እንደ ክርስቲያን ባልና ሚስት በጋራ ለማደግ መነሳትና መደጋገፍ ያስፈልገናል።

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር በክርስትናና በመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ጎዳና ላይ ወደፊት ለመገስገስ ቤታችን አንዱና ዋናው ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት አስፈላጊ የሆኑት የጸሎት፣ የቃሉ ጥናትና የአምልኮ ኅብረት የማድረግ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴዎችንና አገልግሎትን የምንለምድበት የመጀመሪያው ቦታ ሊሆን ይገባዋል። ተምሮ መመረቅና እድገት መጨረስ በሌለበት የክርስትና ሕይወት ትምህርት ቤት ውስጥ ሁልጊዜ ቃሉን በመማርና ስር በመሰደድ እግዚአብሔርን በየዕለቱ ለማወቅና ለማምለክ ራሳችንን መስጠት ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ሕይወት የሚከፈለውን ዋጋ በመክፈል ለማደግ ጥረት ማድረግ *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።"* /ኢያሱ 24፡ 15/ ከሚለው የኢያሱ አቋም ጋር መስማማታችንን በተግባራዊ ምላሽ የምናረጋግጥበት የሕይወት አዋጅ ነው። በእንዲህ ዓይነት የሕይወት መርህ ለመኖር ከተስማማንና አቋም ከያዝን በትዳራችን ውስጥ ብስለት በማጣትና በመንፈሳዊ ቀውስ ውስጥ በመገኘት ምክንያት ሊፈጠር የሚችለውን ግጭትና አለመግባባት አስቀድመን

መከላከል የምንችልበት ዝግጁነት ላይ ደርሰናል ማለት ነው:: የመከላከል ጥረታችንን አልፎ ችግር ከተፈጠረም ችግሩን መፍታት የምንችልበት ዝግጁነት ላይ መገኘታችን ችግሩን ለመፍታት በጣም ጠቃሚ መሳሪያ በመሆን ያገለግለናል::

## 3. መጠበቅ፡- ጥንዶቹ በጋራ በቤታቸው የጸሎትና የአምልኮ ሕይወትን መጠበቅ

የግለሰብም ሆነ የጥንዶች ሕይወት ከጌታ ጋር ያላቸው የየግልና የጋራ የጽሞና ጊዜ ወሳኝ ነው። ከጌታ ጋር ያለን የአባትና የልጅ ግንኙነት በጸሎት ፊቱን በመፈለግ ሊጠናከር ይገባል:: የነፍስና የተለያዩ መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶቻችንን ከእርሱ በጸሎት ለምነን ለመቀበልና የእውነተኛ በረከት ሁሉ ምንጭ የሆነውን አምላክ ለማመስገን ፊቱን በጸሎት መፈለግ ምንም ጉዳት የሌለው ልምምድ ነው። አብዝተን ብንጸልይ አብዝተን እንባረካለን! ጥንዶች በቤታቸው በግልና በጋራ በፊቱ የሚሆኑበት መስዋዕት የማቅረቢያ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል። በጋራ ተንበርክከው ፊቱን በመፈለግ የከፋውን የዲያቢሎስን ሥራ ካለፈረሱና እግዚአብሔርን በማስቀደም ትዳራቸውን ካልመሩ ለሌሎች ግጭቶችና ፈተናዎች ተጋላጭና ተሸናፊ መሆናቸው አይቀሬ ነው።

ጥንዶቹ በጋራ መጸለይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል በግልና በጋራ መስማት፣ ማንበብ፣ ማጥናት፣ ማሰላሰልና በእምነት መታዘዝ ሌላው የመንፈሳዊነት መገለጫ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክት ከልጅነትህ ጀምሮ ከማን እንደተማርከው ታውቃለህና በማለት ከቤተሰቡ እንደተማረው መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ያረጋግጥልናል /**2ኛጢሞ 1: 5 እና 3: 15/**። የእግዚአብሔር ቃል በግልም ሆነ በጋራ ላለው ሕይወት መሠረትና መመሪያ ስለሆነ ቅድሚያ በመስጠት ቃሉን ልንመገብ ይገባል።

ጥንዶቹ ሁሉን የሚችል አምላክን ማምለክን ቋሚ የሕይወት ልምምድ ሊያደርጉት ይገባል። አምልኮ ለእግዚአብሔር መገዛት፣ መሰጠት፣ መስገድና እግዚአብሔርን ማክበር ሲሆን ይህም በእውነትና በመንፈስ የሚከናወን እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል /**ዮሐ 4: 24/**። እግዚአብሔር አምላክ እንደ አምላክነቱ፣ ገዥነቱ፣ አባትነቱና ሁሉን ቻይነቱ... ሊመለክ ይገባዋል። ጥንዶች በጋራ እግዚአብሔርን ማምለክ ዓላማቸውና መለያቸው ሊሆን ይገባል። *"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን"* /**ኢያሱ 24: 15/** በጊዜና በቦታ ለማይወሰነው አምላክና የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ስርዓት በመረዳት አምላኪ በመሆን ሕይወታቸውንና የትዳር ግንኙነታቸውን እግዚአብሔርን በማስቀደም፣ መሪና አስተዳዳሪ በማድረግ ሊመሩ ይገባል።

## 4. መለማመድ፡- ፍጹምነትን ከትዳር አጋር አለመጠበቅን መለማመድ

ክርስቲያናዊ ትዳር ማለት የሁለት ዘመናቸውን ሁሉ ሞት እስኪለያቸው ድረስ በመደጋገፍና በመረዳዳት አብረው ለመኖር የተስማሙ እቻ የሆኑ ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች ቃል ኪዳናዊ ጥምረት ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎች ብርታትና ደካማ ጎን ያላቸው





ሰዎች ናቸው:: ክርስትና ማለት ክርስቶስን አንተ ለእኔ ብቃቴና ጽድቄ ነህ ብሎ መቀበልና በዚህ ሕይወት መኖር ነው። እነዚህ ክርስቶስን የተቀበሉ ሰዎች በክርስቶስ ፍፁምነትና የጽድቅ ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቃን ተብለው ተቀባይነት አገኙ እንጂ እነርሱ በራሳቸው ጽድቅን ሁሉ በተግባር የፈጸሙ ወይም መፈጸም የሚችሉ የበቁ ሰዎች ወደ መሆን ደረጃ አልመጡም:: መንፈሳዊነት ፍጹምነት ሳይሆን ወደ ፍጹምነት በየጊዜው የሚደረግ ሂደትና ለውጥ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሯቸው ፍጹምነትን ከራሳቸው፣ ከትዳር አጋርቸውና ከሌሎች ሰዎች የሚጠብቁ በመሆናቸው የፈለጉትን ፍጹምነት በራሳቸውም ኑሮ ውስጥ ይሁን በሌሎች ሰዎች ኑሮ ውስጥ ማግኘት አልችል ሲሉ በራሳቸውም ሆነ በሌሎች መንፈሳዊ ሕይወት ቶሎ ተስፋ ይቆርጣሉ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች መሠረታዊ ችግራቸው የወደቀው አዳም ልጆች በዚህኛው ዓለም ውስጥ በአካለ ስጋ እስካሉ ድረስ ሊኖራቸው የማይችለውን የፍጹምነት የሕይወት ጥራት ከትዳር አጋራቸው መፈለጋቸው ነው:: የእግዚአብሔር ቃል *". . . እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ። "* /**ኤፌ 4፡ 11-13/** በሚለው አሳቡ በግልጥ እንደሚያሳየን የአማኞች የክርስትና ሕይወት ጉዞም ወደ ሙላቱ ልክ የማደግ እንጅ የበቁ ፍጹማን ሆነው የመገኘት ብቃት ጉዳይ አይደለም::

እያንዳንዳችን ፍጹም እንከን የለሽ ልንሆን አንችልምና ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ስህተት ክፍተት በመስጠትና በጋራ አንዱ የሌላውን ክፍተት በብርቱ ጎናችን በማሟላትና በመደጋገፍ አብረን ልንኖር ይበጃል። አንዱ በሌላው ድካም ከመፍረድ ይልቅ ደካማውን በመደገፍ መተናነጽ መንፈሳዊነት ነው። ሰዎች እንከን የለሽ ብንሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ *"እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልከተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። "* /**ዕብ 12: 1-2/** የሚል መመሪያ በመስጠት ብዙ የእምነት አባቶች እያሉልን ኢየሱስን ተመልከቱ አይለንም ነበር።

## 5. መገንዘብ፡- ትዳርና ቤተሰብ ቅድሚያ የሚሰጠው ኃላፊነታችን እንደሆነ መገንዘብ

ከትዳርና ከቤተሰብ ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ቅድሚያና ትኩረት መስጠት ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ አካሄድ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል። ነገር ግን ጥቂት የማይባሉ ክርስቲያን ባለትዳሮች **ማቴ 10: 37-38** የመሳሰሉ ጥቅሶችን በማጣቀስና ለሚያጋጥሟቸው ችግሮችና ጥያቄዎች ትክክለኛ ያልሆኑ መልሶች በመስጠት ለጋብቻ ሕይወትና ለቤተሰብ መስጠት ያለባቸውን ኃላፊነት ችላ ሲሉ

ይታያሉ፡፡ በእርግጥ ለትዳር ጓደኛና ለቤተሰብ ያለን ፍቅር ከጌታ ፍቅር ሲበልጥብንና ክርስቶስን እንዳንከተለው የሚከለክለን ሲሆን በሞቱ ሕይወት የሰጠንን ጌታ በማንኛውም መስዋዕትነት ውስጥ የመከተል ቅድሚያ ልንሰጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነት ችግር በሌለበት ለትዳርና ለቤተሰብ የሚሰጠውን ጊዜና ትኩረት በመተው በሙሉ ኃይላችንና ትኩረታችን ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያለ አገልግሎት ላይ መሰለፍ ተገቢ አይደለም። ትክክለኛ አገልግሎት ለትዳርና ለቤተሰብ እንክብካቤንና ትኩረትን ከመስጠት ይጀምራል።

**ትክክለኛ አገልግሎት ለትዳርና ለቤተሰብ እንክብካቤንና ትኩረትን ከመስጠት እንደሚጀምር አንዘንጋ!!**

ነገር ግን በተሳሳተ ሁኔታ ጥቅስን በማጣቀስ ራስን ከትዳርና ከቤተሰብ አርቆ አገልግሎትን መደበቂያ ከማድረግ በፍጥነት መመለስ ካልተቻለ አንድ ቀን በዚህ ስህተት የመጀመሪያው ተጠቂ ትዳርና ቤተሰብ እንደሚሆን ከወዲሁ መረዳት ያስፈልጋል። ከቤት ያልተጀመረ አገልግሎት ትክክለኛ አገልግሎት ካለመሆኑም ባሻገር አገልግሎቱ ዘላቂ አይሆንም። *"ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?"* /1ኛጢሞ 3፡ 4-5/፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ የትዳር አጋር አንዱ የሌላውን የጸጋ ስጦታ እንዲረዳ በማገዝ በዚያው ጸጋ እርስ በእርስና ቅዱሳን እንዲገለገሉበት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተገቢ ነው። ለትዳርና ለቤተሰብ ቅድሚያ በመስጠት ጌታን በታማኝነት ለማገልገልና ለቅዱሳን መታነጽ መኖር የሚቻልበት ትክክለኛ የሕይወት መስመርና የልምምድ ተቋም ነው። *"እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤"* /1ኛጴጥ 4፡ 10/፡፡

## 6. መጣር፡- በትክክለኛ ራዕይ ቢጋራ ለማደግ መጣር

በምድር ስንኖር ጌታ ፈጽመነው እንድናልፍ ወይም ለቀጣይ ትውልድ እንድናስተላፈው የሰጠን ራዕይ ሊኖር ይችላል። በራዕይ ለመኖርና ራዕይን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ባለው ሂደት ከትዳር አጋር ጋር በተለያየ መልኩ አብሮ መቆም ወሳኝ ነው። በዚህ ሂደት በሙሉ መሰጠት ከመተባበር በፊት በራዕይ ላይ ወደ ጋራ ስምምነት የመድረሱ ሂደት መቀባበልን ይጠይቃል። ይህን ሂደት በአግባቡ ለማሳካት ራዕይን ጥበብ በሞላው ብስለት ለትዳር ጓደኛ ማካፈል አስፈላጊ ነው። በተሳካ ሁኔታ ይህን ተግባር ለማከናወን ራዕይን የምናካፍለበት ትክክለኛ ጊዜ፣ ምቹ ቦታና ስልት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። *"ራእዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውም ይቸኩላል፥ እርሱም አይዋሽም ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም።"* /ዕን 2፡ 3/

እንደ ባለትዳር ከሁለት አቅጣጫ ሚዛንን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። እንደ ባለራዕይ ደግሞ በራዕይ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ራዕይን የጋራ ለማድረግ ወይም





ተደጋግፎ ራዕይን ወደፍጻሜ የመውሰድ ስምምነት ላይ ለመድረስ የትዳር አጋሮች ራዕይውን አምነው እስኪቀበሉት ድረስ ጥረት በማድረግ የመጠበቅ ባህል ቢኖር ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። በሚደገረው ጥረት ውስጥ ከመተባበር ይልቅ መከራከር የሚያጋጥም ከሆነ በትዕግስት፣ በማስተዋልና በፍቅር ማሸነፍ የሚቻልበትን መንገድ መፍጠር ተገቢ ነው። ራይውን የሚካፈለው የትዳር አጋርም አስቀድሞ ተቃዋሚ ከመሆንና ግጭት ውስጥ ከመግባት ይልቅ ራዕዩን ለመረዳትና የትዳር ጓደኛን ለመርዳት ከመነሳት መጀመር መንፈሳዊነት ነው። በእርግጥ ትክክለኛ ራዕይ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስለሆነ ከባለራዕዩና ከተባባሪዎች አቅም ያለፈ ነው። ስለዚህ የትዳር ጓደኞች ከአቅም በላይ የሚመስለው ራዕይ አስፈርቶን ወይም በተሳሳተ መንገድ ተረድተነው ለራዕይው ተባባሪ ወዳለመሆን ከመግባት ይልቅ ከጥቂትና ከትንሽ የሚጀመርበትን ስልት በመቀየስ ተባባሪነታችንን ማሳየት ተገቢ ነው። በዚሁ አጋጣሚ በአገልግሎት ራዕይ ላይ በአሳብ፣ በጸሎትና በገንዘብ በመተባበር ቅዱሳንን ለማገልገል ዕድል እንዳገኝ የምትረዳኝ ባለቤቴን ላመሰግን እወዳለሁ።

ምናልባት ራዕዩ የሚጠይቀውን የጊዜና የገንዘብ እንዲሁም የሰው ኃይል መጠን ለመቀበል ቢከብድም እንኳን በራዕዩ አሳብ ላይ መቀባበል ካለ ባለመስማማት መስማማትና ውጤቱን መጠበቅ መልካም ነው። በራዕይው ላይ እርግጠኛ የሆነ መሠረታዊ ተቃውሞ ከሌለንና ነገር ግን ራዕይውን እኛ ማየት ካልቻልን ከባለ ራዕዩ ጋር መተባበር፤ መተባበር ከከበደን ደግሞ ባለራዕይው ጉዞውን እንዲቀጥል አምነን መልቀቅ ተገቢ ነው። በሚደረገው ሂደት ስህተት፣ ድካምና አለመሳካት ሊፈጠር ይችላልና መፍረድ ሳይሆን ከተፈጠረው ስህተት እንዲማሩ ብሎም እንደ ገና እንዲነሱ ማበረታታት የትዳር አጋርነት ኃላፊነት ሊሆን ይገባል። *"እኔም። እኛ ያለንበትን ጉስቍልና ኢየሩሳሌም እንደ ፈረሰች፥ በሮችዋም በእሳት እንደ ተቃጠሉ ታያላችሁ አሁንም ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ አልኋቸው። የአምላኬም እጅ በእኔ ላይ መልካም እንደሆነች፥ ንጉሡም የነገረኝን ቃል ነገርኋቸው። እርሱም፡- እንነሣና እንሥራ አሉ። እጃቸውንም ለበጎ ሥራ አበረቱ። ... የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል፥ እኛም ባሪያዎቹ ተነሥተን እንሠራለን እናንተ ግን በኢየሩሳሌም እድል ፈንታና መብት መታሰቢያም የላችሁም አልኋቸው።"* /ነህ 2፡ 17-20/

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አሰር (10)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የእምነትንና የመንፈሳዊ መረዳትን ልዩነት ምንነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ተወያዩበት።
2. በባለትዳሮች መካከል የእምነትና የመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ሊፈጠር የሚችልባቸውን አጋጣሚዎች በመዘርዘር ውይይት አድርጉ::
3. በባለትዳሮች መካከል በእምነትና በመንፈሳዊ መረዳት ልዩነት ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችን ዘርዝሩ:: የእናንተን የግል የግጭት ምክንያት የሆነውን ለይታችሁ በማውጣት ተነጋገሩበት::
4. እንደ መንፈሳዊ ሰው ያላችሁ ራዕይ ምንድን ነው? የራዕይ ስምምነት እንዲኖራችሁ ምን አደረጋችሁ ወይም ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
5. በእምነትና በመንፈሳዊ ልዩነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች የመፍትሔ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? በዝርዝር በመወያየት የግል የግጭት መንስኤ ለሆኑ ችግሮቻችሁ ልትወስዱት የሚገባ እርምጃ ምንድን ሊሆን ይገባል ትላላችሁ?
6. እንደ ባለትዳርና ቤተሰብ የግል የጸሎት፣ የአምልኮና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ እንዲኖራችሁና በጋራ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለማቀድ ምቹ የሆነ ጊዜና ቦታ በማመቻቸት ለማቀድ ዝግጅት አድርጉ።





## ምዕራፍ አስራ አንድ(11)

## የባልና የሚስት ኃላፊነትና የተለያየ ሚና

### I. የክርስቲያን ባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ምንነት

አንድ ክርስቲያን ወንድምና አንዲት ክርስቲያን እህት በእውነተኛ ፍቅር ላይ በተመሠረተ የትዳር ሕይወት በዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን በመጣመር ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም ይመሠርታሉ:: በዚህ ተቋም ውስጥ ባልና ሚስት በየራሳቸውና በትብብር የሚሸከሟቸውና ሊወጧቸው የሚገቡ ኃላፊነቶችና ሚናዎች አሏቸው:: ልጆች በሚወለዱበት ጊዜ ደግሞ የወላጅነትን ኃላፊነት በጋራ የመወጣት ግዴታ ያለባቸው ሲሆን የአባትነትና የእናትነትን ኃላፊነት ለመወጣት ደግሞ የየራሳቸው ሚና ያኖራቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን እውነት በማስረገጥ ወንዱ የባልነትና የአባትነት ሴቷ ደግሞ የሚስትነትና የእናትነት ኃላፊነትና ሚና እንዳለባቸው በመረዳት እርስ በርሳቸው የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በመናገር የሚናቸውን ምንነት ግልጥ አድርጓል /ኤፌ.5:21-33/። ይህ ምዕራፍም የሚያተኩረው በዚህ አብይ ጉዳይ ላይ ነው::

### II. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

ይህ ምዕራፍ ባልና ሚስት የየግል የጋራ ኃላፊነታቸውን እንደሚገባ ካለመረዳትና ካለመወጣት ጋር በተያያዘ በትዳር ውስጥ ግጭት የሚያመጡ ምክንያቶችን በማሳየት ጥንዶች የግጭት ሰበቦችን ለመቀነስ ሚናቸውን እንዲረዱና እንዲወጡ የማስቻል ዓላማ አለው:: ባልና ሚስት ትክክለኛ የአጋርነትን ሚና የመወጣት ክርስቲያናዊ፣ ፍጥረታዊና ማሕበራዊ ግዴታ አለባቸው:: ይህን ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት ከቻሉ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በጥሩ መሠረት ላይ በመታነጽ ሥር እየሰደደ ሰላምና መግባባት የሞላበት ይሆናል:: ግዴታቸውን በአግባቡ ካልተወጡ ደግሞ የሕብረታቸው መሠረት ይናጋል:: ግንኙነታቸውም በአለመግባባትና በግጭት የሚናወጥ የጦር ሜዳ ወደ መሆን ይሻገራል:: ስለዚህ ባልና ሚስት የጋራና የየግል ኃላፊታቸውን በመረዳት ለትዳራቸው ጤናማነትና ሰላማዊነት መትጋትን ቀዳሚ ጉዳያቸው ሊያደርጉት ይገባል:: ጥንዶቹ የጋራና የየግላቸው ከሆነው ኃላፊነት ባሻገር ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ኃላፊነት እንደሚገባ በማወቅና አንዱ ለሌላው እርዳታ፣ ትብብርና ድጋፍ በማሳየት ግጭቶችን ቀንሰው የሚፈጠሩ ችግሮችን በአግባብ በመፍታትና እርስ በእርስ በመግባባት ቤታቸውን ሊያንጹና ሊጠብቁ ይገባል።

አንዳንድ ባሎች ሚስት የሚያገቡበት ዓላማ በቤት ውስጥ የሚሠሩ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ስለሚችሉና ይህንን ክፍተት የምታሟላ አጋዥ እንድትኖራቸው በማሰብ ነው። የዛሬ አስራ ስድስት ዓመት ገደማ አገር ቤት እያለን ወንድሞች ሰብሰብ ብለን ስናወራ የእግር ካልሲውን ማጠብ የሰለቸው አንድ ወንድም "አሁንስ ካልሲዬን

የምታጥብ ሚስት ጌታ በሰጠኝ" አለን:: እኔም ለዚህ ወንድም "አንተ ሚስት ሳይሆን የምትፈልገው የቤት ሠራተኛ ነው" በማለት እንደመለስኩለት አስታውሳለሁ። ከአደግንበትና ከተቀረጽንበት ባህል አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ ስለሚስት ስናስብ እነዚህን የመሳሰሉ አስተሳሰቦች እናንጸባርቃለን። ሚስት የቤት ሠራተኛ አይደለችም! ሚስት ለባሏ አጋዢ እንድትሆን የተፈጠረችና የባሏ አቻ ወይም እኩያ የሆነች ምቹ ረዳቱ ናት። እርሱም የባልነት ኃላፊነቱን በመወጣት የሚስቱ የትዳር አጋር ነው /ዘፍ 2፡ 23-24፣ ምሳ 18፡ 22፣ 31፡ 11-12/:: ስለዚህ ሚስት ባል አምባገነን በመሆን እንዲሁ እንደፈለገ የሚረግጣት ምንጣፍ አይደለችም! ባል እንደ ወደደና እንደ ፈለገ በሚያስበው በሁሉም አሳቡ ሚስት እንድትስማማ የሚጠበቅባትና የምትባለውን ሁሉ የምትፈጽም የራሷ የሆነ ፈቃድ የሌላት አይደለችም። ከባሏ የበታች ሁና የምትኖር ሳትሆን የራሷ የሆነ መልካም አሳብ ያላት ቤታቸውን ከእርሱ ጋር በአቻነት አብራ የምትሠራ፣ የምትገነባ፣ ትዳሯንና ቤተሰቧን የምትንከባከብ አምላካዊ ስጦታ፣ በረከትና ረዳት ናት። ከዚህ በመነሳት የሚስትነትን ኃላፊነትና ሚናን ባለመረዳት የሚፈጠሩ የግጭት ምክንያቶችን በሚከተሉት ነጥቦች በመዘርዘር ለመጠቆም እሞክራለሁ:-

## 1. ሚስት ለቧላ ትገዛ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ በተሳሳተ መንገድ መረዳት

*መጽሐፍ ቅዱስ* የመታዘዝንና የመገዛትን ትዕዛዝ የሚሰጠው በጋራ ለባልና ለሚስት ነው:- *"ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።"* /ኤፌ 5፡ 21/:: አንዱ ለሌላው የመገዛታቸውና የመታዘዛቸው መለኪያው ደግሞ ሌላ ሳይሆን በክርስቶስ ፍርሃት መኖር ነው። ለክርስቶስ የተገዛች ሚስት ለባሏ ለመገዛት፣ ለክርስቶስ የተገዛ ባል ደግሞ ለሚስቱ ለመገዛት አይከብደውም። መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ለባሏ እንድትገዛ በግልጥ ቢያዝም ነገር ግን ሁለቱንም በክርስቶስ ፍርሃት አንዳቸው ለሌላቸው እንዲገዙ ያስተማረ መሆኑን በማስተዋል የመጽሐፉን አጠቃላይ ምክር መረዳት አስፈላጊ ነው:: ስለዚህ ባሎች ይህን ሃሳብ በመሰረዝ የመታዘዝን ኃላፊነት በሚስት ላይ ብቻ የተጫነ ግዴታ አድርገን በመቁጠር ሚስቶችን የምናዝዝ አለቆች መሆንና በአይነኬ የገዥነት ዙፋን ላይ ተቀምጠን ለመኖር ማለም የለብንም። በክርስትና ሕይወት ውስጥ አንዳችን ለሌላችን የመገዛት ኃላፊነት ባሎችንም የሚያጠቃልል ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ መሆኑ የእግዚአብሔር ቃል አስረግጦ የሚያስተምረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው /ፊል 2፡3-4፣ 1ኛ ጴጥ 5፡5፣ ሮሜ 13፡1ና ዕብ 13፡7/::

*" ሚስት ለባሏ ትገዛ "* የሚለው መሠረታዊ የሆነ የትዳር ግንኙነት መርህ ሚስት ባሪያ መሆን አለባት የሚል ትርጓሜ ሊሰጠው አይገባም! ቀድሞ እንደ ነበረው የባሪያ አገዛዝ ዘመን ሚስቱን ምንም መብት የሌላት ተናገሪና ተንቀሳቃሽ የሆነች ሕይወት ያላት እቃ አድርጎ የሚያስብ ወንድ ካለ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ያልገባውና ለጋብቻ ኃላፊነትም ፈጽሞ ያልተዘጋጀ ማንነት ያለው ሰው ነው።





*"አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ።"* /ምሳ 31፡ 26/ የሚለው የእግዚአብሔር ምክር ሚስት የባሏን የተሳሳተ መረዳት ልታስተካክል የምትችል ረዳት እንደሆነች ያሳየናል። *"...ማኑሄም ሚስቱን:- እግዚአብሔርን አይተናልና ሞት እንሞታለን አላት። ሚስቱም:- እግዚአብሔርስ ሊገድለን ቢወድድ ኖሮ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን ከእጃችን ባልተቀበለን፥ ይህንም ነገር ሁሉ ባላሳየን፥ እንዲህ ያለ ነገርም በዚህ ጊዜ ባላስታወቀን ነበር አለችው።"* /መሳ 13፡ 21-23/ ነገር ግን ምንም መናገር የሌለባቸው (የማይናገሩ) እና መልካም ሃሳብና ፈቃድ የሌላቸው አድርጎ ሚስቶችን መቁጠር በትዳር ላይ ግጭትን ማብዛትና መለያየትን የሚያስከትል አፍራሽ አመለካከትና ተግባር ነው።

በአንዳንዶቹ ትዳር ውስጥ ሚስትን በቤት ውስጥ ካሉ የተለያዩ የቤት ዕቃዎች መካከል እንደ አንዱ አድርጎ መቁጠርና የሚገባትን ዋጋ አለመስጠት በንግግር ባይገለጽም ከዚህ ባልተናነሰ አመለካከት በተግባር ሲገለጽ ይታያል። ሚስት ባል እንደፈለገ የሚያደርጋት የቤት ዕቃ ሳትሆን ከባሏ ጋር በአቻነት አብራ የሃብቷ ባለቤትና ቤታቸውንና ያላቸውን ሁሉ በመንከባከብ ሚናዋን የምትወጣ አጋር ናት። *"እርሻንም ተመልክታ ትገዛለች ከእጅዋም ፍሬ ወይን ትተክላለች። ወገብዋን በኃይል ትታጠቃለች፥ ክንድዋንም ታበረታለች። ንግድዋ መልካም እንደ ሆነ ትመለከታለች መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም።"* /ምሳሌ 31፡ 16-18/::

## 2. ሚስት ብቻ የገቢ ምንጭ መሆን ወይም በገቢ መጠን ከባሏ መብለጥ

ይህ ችግር በገንዝብና በንብረት ላይ እንደ አንድ ችግር አስቀድሞ የተጠቀሰ ቢሆንም እንኳን በባልና በሚስት ኃላፊነትና ሚና ላይ የሚያመጣው አሉታዊ የሆነ የሚናና የስርዓት ለውጥ ቀላል አይደለምና በድጋሚ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የገንዘብ አቅም ያላቸው ሰዎች በቤት፣ በትዳር፣ በቤተሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን ብሎም በአገር ላይ የሚያመጡት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ጤነኛ ያልሆነ የገንዘብ ተጽዕኖ ከማንነት፣ ከችሎታ፣ ከጸጋ ስጦታ፣ ከልምድ፣ ከክህሎት፣ ከስልጠናና ከመልካም ልምዶች ወደ ኋላ ሊያስብልም ይችላል:: በዚህ ስፍራ ላይ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በድጋሚ ማንሳት ያስፈለገው ያለን የልማዳዊ አመለካከት ተጽዕኖ ወይም የሕይወትን ኃላፊነት ለመሸከም የምንችልበት ብስለት ሳይኖረን ገንዘብ ማግኘታችን ከትዳር ጀምሮ በተዋረድ የሰዎችን ኃላፊነትና ሚና በአፍራሽነት ሊያስቀይር ስለሚችል ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ ከሚያመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ይልቅ አሉታዊ ተጽዕኖው ጎልቶ ሊታይ ይችላልና ልዩ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው መሆኑን ማሳየትም የዚህ ነጥብ መሠረታዊ ትኩረት ነው::

በብዙ አገሮች ባህልና በታሪካዊው ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የባል የቤቱ የገቢ ምንጭ መሆን የተለመደና የሚጠበቅም ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር በእኛ አገር ባህል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ባህል ውስጥ የሚታይ ችግር ነው። በቅርብ ጊዜ የሌላ አገር ዜጋ የሆኑ ለ25 ዓመት በትዳር ላይ የቆዩ ባልና ሚስቶች የምክር አገልግሎት ፈልገው የምሠራበትን የካውንስሊግ ሴንተር ጎብኝተው ነበር:: የትዳራቸው ችግር ምንድን

እንደሆነ በምጠይቅበት ወቅት እንደተረዳሁት አንዱ ችግራቸው ባል በጊዜው ሥራ አጥ መሆኑና ለቤተሰቡ የገቢ ምንጭ አለመሆኑ በነፃነት አሳቡን መግለጽ እንዳይችል ያሳደረበት አሉታዊ ተጽዕኖ ነው:: ያጋጠመው የሥራ አጥነትና ለቤተሰቡ የገቢ ምንጭ አለመሆን ችግር በማንነቱም ላይ የበታችነት ስሜት ፈጥሮበታል:: ስነ-ልቦናው ተጎድቷል፣ ብስጩነትና ድብርትም እንደያዘው ገለጾልኛል።

ከአሁን በፊት የገቢ ምንጭ በመሆን ሲያስተዳድር የነበረ ባል በተለያየ ምክንያት ሥራ አጥ ሲሆን ወይም  የገቢው መጠን ከሚስቱ ገቢ ያነሰ በሚሆንበት ወቅት ሊፈጠርበት በሚችለው ስነ ልቦናዊ አሉታዊ ተጽዕኖና የማንነት ቀውስ ምክንያት የባህርይ ለውጥ ሊያመጣና ሰብብ ፈልጎ መጋጭት የየዕለቱ ልምዱ ሊሆን ይችላል። በአንድ ወቅት አገር ቤት ለአገልጋዮች ስለማማከር አገልግሎት ስልጠና እሰጥ ነበር:: በባህላችን በተለይ ሚስቶች ብቻ የገቢ ምንጭ የሚሆኑበት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ በትዳር ግንኙነት ውስጥ ችግር ሊፈጠር የሚችል መሆኑን ማብራራት ስጀምር አንድ ምስክርነት ነገሩኝ:: ታሪኩ በአንድ ወቅት ትዳር መሥርተው አብረው ይኖሩ በነበሩ ጥንዶች መካከል የተፈጠረ ታሪክ ነው:: ባልና ሚስት አብረው በሰላም ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ አንድ ቀን በመካከላቸው ግጭት ይፈጠራል:: ባልና ሚስት በተጋጩ ወቅት ባል የአካባቢው ባህልና ወግ በቀረጸው አስተሳሰቡ በስሜታዊነት በተሞላ ንግግር ***"ከዚህ ቤት ውልቅ ብለሽ ትወጫለሽ"*** ብሎ በቁጣ ይናገራል:: ሚስትም በምላሹ የእነርሱን ቤት ነባራዊ እውነታ ባንጸባረቀ ንግግሯ ***"አንተ ነህ ወይንስ እኔ ነኝ ከዚህ ቤት መውጣት ያለብን?"*** በማለት ባል ላቀረበው የውጭልኝ ትዕዛዝ መጠይቃዊ መመሪያ ትሰጣለች::

ባል በዚህ ጊዜ ከጋረደው ባህላዊና ልማዳዊ የአስተሳሰብ ጭጋግ አዕምሮውን በማጽዳት ተጨባጩን እውነታ ለማገናዘብ ሲሞክር ለካስ ሙሉ በሆነ ቤት ውስጥ ሻንጣውን ይዞ ወደ ዚህ ቤት የገባውና በኢኮኖሚ የሚስቱ ጥገኛ የሆነው እርሱ ነበር:: ምስክርነቱን ያካፈሉኝ ሰዎች ባል ይህንን ገሃዳዊ እውነት ባስተዋለ ጊዜ "እኔ ነኝ ለካስ የምወጣው" እንዳለ አጫውተውኛል። ከታሪኩ እንደምንገነዘበው በዚህ ትዳር ውስጥ የንብረት ባለቤትነት ጋርዮሻዊ አልነበረም:: በዚህ ቤት ንብረት በባለቤትነት የተመዘገበው መጀመሪያ በገዛው ሰው ማለትም በሚስት ስም ነው:: በእርግጥ በታሪኩ እንደተገለጠው አንዳንድ ባሎች የፍጹማዊ አንባገነን ባሕርይ ባለቤት በመሆን በትዳር ውስጥ ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ እንኳን ማገናዘብ አይችሉም:: በሌላ በኩል ብቸኛ የቤተሰብ የገቢ ምንጭና የኢኮኖሚ መሠረት የሆኑ ሚስቶችም የያዙትን ኢኮኖሚያዊ የኃይል የበላይነት ትዳራቸውን ለመጠበቅ ሳይሆን ግላዊ መብታቸውን ለማስጠበቅ የሚጠቀሙበት ኃይልና ጉልበት አድርገው በመውሰድ ክርስትና ስለጋብቻ ከሚያስተምረው ትምህርት በተቃራኒ ለመኖር የሚመርጡ መሆኑን ነው።

በተለይ በአሁኑ ዘመን ከአገር ቤት በእድገትና በስልጣኔ ሂደት በመንግስትና በግል ስራ ላይ የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ በመጣበት ወቅት የሚስቶች የገቢ





ሃብትም ከባሎች ሊበልጥ በሚችልበት አልያም ከባል ጋር በማይተናነስበት ዘመን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የትዳርን ግንኙነት መጠበቅ ካልተቻለ በሚፈጠሩ ከፍተቶች ትዳር ለከፋ አለመግባባትና ግጭት ሊጋለጥ ይችላል። ባለትዳሮች በየግል በሚያገኙት የገቢ መጠን የበላይና የበታችነት ስሜት እየተፈጠረባቸው የትዳር ግንኙነታቸው እንዳይሻከር ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከትዳር ጓደኛ ጋር ያለው ግንኙነት ላይ ማተኮር ተገቢ ነው። በለውጥና በእድገት ዘመን እኛ በገቢና በኢኮኖሚ የምንበልጠው ሰው የተለያዩ የእድገት እድሎችን በማግኘት እኛን ሊበልጠን ይችላል። በተለይ በትዳር ውስጥ ያለን ሰዎች እንዲህ ዓይነት መልካም አጋጣሚ ሲፈጠር እድገቱ የመጣው በባልም ይሁን በሚስት በኩል ጉዳዩን ትክክለኛና ጤነኛ በሆነ መንገድ በማየት ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ የሚጠቅም የእድገት በረከት መምጣቱን በመረዳት ሁላችንም ደስተኛና እግዚአብሔርን የምናመሰግን ልንሆን ይገባል::

በውጩ ዓለም የሚኖሩ ሀበሻዎች እንደየሚኖሩበት አገርና እንዳለው የሥራ ሁኔታ ሴቶች (ሚስቶች) የተሻለ የሥራ እድል ሊያገኙ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ባሎች የበታችነት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል:: ይህ በበታችነት ስሜት የመጠቃት ሁኔታ በባሎች ላይ የባሕርይ ለውጥና የማንነት ቀውስ እንዳያስከትልና ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መግለጽ ወደ ማይችሉበት የተግባቦት ደረጃ አድርሷቸው ነፃነታቸውን እንዳይነፍጋቸው መጠንቀቅ ተገቢ ነው። አገር ቤት በነበሩበት ወቅት የነበረ መተሳሰብ ብዙ ዕድል በበዛበት አገር ሊጠፋ አይገባም። እውነተኛ የሆነ መታዘዝን፣ መቀባበልንና ባለን ገንዘብ በጋራ መጠቀም መለማመድን ማቆም መንፈሳዊነት አይደለም። እውነተኛ መታዘዝና መከባበር ምንም ምርጫ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ብዙ ምርጫ በበዛበት ሁኔታ ውስጥ የሚገለጽ ክርስቲያናዊ የሕይወት ኃላፊነት ነው።

## 3. ጾታን ብቻ መሠረት ያደረገ የሥራ ክፍፍል

ከጾታ አንጻር አቅማችን፣ ጉልበታችን፣ እይታችን፣ ችሎታችን ሊለያይ ይችላል:: ነገር ግን በትዳር ውስጥ ያለውን የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነት ልማዳዊውን ወይም ባህላዊውን አስተሳሰብ በመከተል ከጾታ አንጻር ብቻ በማየት የሚደረግ የሥራ ክፍፍል በጋራ መረዳዳትን ማዕከል ያላደረገ ስለሚሆን በጥንዶቹ ተደጋግፈው መኖር ላይ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በአብዛኛው ሐበሻ ዘንድ ከጾታ አንጻር ብቻ ማንኛውንም የቤት ውስጥ ሥራ የሚስት ኃላፊነት ከቤት ውጭ ሠርቶ የቤት ወጭን የማምጣትንና ቤተሰብን የማስተዳደርን ኃላፊነት ደግሞ የባል ብቻ አድርጎ የመቁጠር አስተሳሰብና ተግባር ጥንታዊነት ከጥንት ጀምሮ የተለመደ ነው:: ይህ አመለካከት መተሳሰብንና በሁሉም ነገር መደጋገፍን የሚያስቀር በአሁኑ የለውጥና የእድገት ዘመን ሊታይ የማይገባው ልምምድ ነው። በተቻለ መጠን አለማወቅ፣ በትክክለኛው እውቀት መኖርን አለመለመድና መኖር አለመቻል የሚቀረፍበትን መንገድ እየፈጠሩ ባል ሚስትን ሚስት ደግሞ ባልን የምትረዳበት መንገድ ማሰብ ተገቢ ነው።

ይህ የሴት ወይም ይህ የወንድ ሥራ ነው ብሎ ሥራን ለተቃራኒ ጾታ በመመደብ መተው ትክክለኛ ግንዛቤና ተግባር አይደለም:: የባሎች የቤት ወጭ እስከሰጡ ድረስ የራሳቸውን ኃላፊነት እንደተወጡ አድርገው በመቁጠር ሚስቶች ከውጭ ሥራ በተጨማሪ በአጠቃላይ የቤት ሥራን ሁሉ እንዲሸከሙ በማድረግ የሥራ ጫናን በሚስቶች ላይ ማብዛት ሊወገድ ይገባል:: አንዳንዶች ደግሞ ከቅዱሳት መጽሐፍት መርህ ጋር በማይስማማና ጽንፈኛ በሆነ መንገድ በድህረ-ዘመናዊው ፍልስፍና የአስተሳሰብ ተጽዕኖ ስር በመውደቅ የሴቶች የበላይነት በሚንጸባረቅበት ቤተሰብ ውስጥ በማደግ ወይም በስንፍና ምክንያት በባሎች ላይ አግባብነት የሌለው ጫና የሚያበዙ ሚስቶች መኖራቸው የዘመናዊውና የድህረ-ዘመናዊው ዓለም እውነታ ነው:: እንደዚህ ዓይነት የትዳር ሕይወት የሚመሩ ክርስቲያን ሚስቶች ደግሞ አመለካከታቸውን በማስተካከል፣ ባሕርያቸውና ልምዳቸው ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው አኗኗር እንዲለወጥ በመትጋትና ስንፍናቸውን በማስወገድ አንዱ ሌላውን ለመረዳትና ለመርዳት እየተዘጋጁ ኃላፊነታቸውን ተሸክመው ወደ መኖር መምጣት አለባቸው:: ሁለቱም ጥንዶች ይህንን ማድረግ ከቻሉ ትዳራቸው ጠንካራና ጽኑ ይሆናል:: ሞት እስኪለያቸው ድረስ በሚዘልቅ ሰላም የተሞላ ቤተሰብ እንዲኖራቸውም ያስችላቸዋል።

## III. ከባልና ሚስት ኃላፊነትና ሚና ጋር በተያያዘ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መለማመድ:- የሚስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃላፊነትን መረዳትና የሚስትነትን ኃላፊነት መለማመድ

ሚስት ለባሏ ትገዛ (ትታዘዝ) የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ አሳብ መረዳት ባልና ሚስት ለሚኖራቸው ግንኙነት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ሚስት ለባሏ የምትገዛው በፈቃዷ እንጅ በባሏ አስገዳጅነት ሊሆን አይገባውም /ኤፌ 5፡ 22፣ 1ጴጥ3፡ 1/። ሚስት ለባሏ መገዛት ወይም መታዘዝ አለባት የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ቀጣይነት ያለውና የማይሻር የሕይወት መርህ ነው። ይህ ማለት ሁኔታን እያዩ፣ መልካም ነገር በተደረገ ጊዜ፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት መጣጣምና እርካታ በኖረ ወቅት... ብቻ ሳይሆን በማይመች ወቅትም ጭምር ሚስቶች ፈልገውና ፈቅደው በዚህ መርህ ለመኖር ለእግዚአብሔር ቃል ራሳቸውን ማስገዛት አለባቸው።

መታዘዝና መገዛት ክርስቲያናዊ ግዴታ እንጂ በፍላጎታችን የምንቀበለው ወይም ሲያሰኘን የምንጥለው ግላዊ ምርጫችን ብቻ አይደለም። በመልካም ጊዜ ወይም እንክብካቤ በበዛበት ወቅት ብቻ የሚሆንና የምናደርገው ሳይሆን በልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታ ውስጥ በምናልፍበትም ወቅት ሊፈጸም የሚገባው ቋሚ የሆነ የክርስቲያናዊ ትዳር መርህ ነው። መታዘዝ ወይም መገዛት የሚለው ቃል በአእምሯችን ውስጥ ፈጥኖ እንደሚመጣልን ዓይነት አሉታዊ ትርጉም የያዘ አሳብ አይደለም:: መገዛት ለሚለው አሳብ አዎንታዊ እንጂ አሉታዊ ትርጉምና (መረዳት) ልንሰጠው አይገባም:: ሚስት





ያላትን ሁሉ ማለትም ከባሏ የምትሻልበት ችሎታ፣ ሙያና ዕውቀት እያላት ነገር ግን ራሷን በፈቃዷ ከባሏ አስተዳደር ስር በማድረግ ለትዳሯና ለቤተሰቧ ስትል የአለቅነት ትግሏን መተው ስትችልና ፍቅርን መሠረት ባደረገ ስምምነት ብቃቶቿን ቤተሰቧን ለመጥቀም ስትገለገልባቸው የሚያሳይ መርህ ነው።

ሚስት ለባሏ ትገዛ ወይም ትታዘዝ የሚለው መርህ የሚስትን አስተሳሰብና ተግባር የሚጠይቅ ነው:: *"ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል። በሕይወቷ ዘመን ሁሉ መልካም ታደርግለታለች፥ ክፉም አታደርግም። የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች፥ በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች።"* /ምሳሌ 31፡ 10-13/ የሚስት መገዛት ምሳሌነቱ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መታመንንና ለእርሱ እውቅና በመስጠት የምታድረገውን ሁሉ እርሱን በማክበር ልታደርገው ይገባል። *"ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።"* /ኤፌ 5፡ 24፣ 1፡ 22፣ ቆላ 3፡ 17፣ 1ኛቆሮ 10፡ 31/

ሚስት ለባሏ ትገዛ የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ከባል (ከወንድ) ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝን ያስቀደመ መሆኑ *"...ለክርስቶስ እንደምትገዛ..."* /ኤፌ 5፡ 24/ በሚለው ቃል ግልጥ ተደርጓል:: የሚስት መታዘዝ የማይተገበረው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረንና ኃጢአት የሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ብቻ ነው። *"... ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።"* /ሐዋ 5፡ 29/ በትዳር ውስጥ የምንጠየቀው መታዘዝ ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ኃላፊነታችንና እግዚአብሔርን ከማምለክ ኑሯችን ጋር የሚቃረን ከሆነ ሊተገበር አይገባውም:: ለምሳሌ ያክል እንደ ኢዮብ ሚስት አይነት *"አስከ አሁን ፍጹምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ሰደብና ሙት ..."* /ኢዮብ 2፡ 9-10/ የሚል ትእዛዝ የሚያመጣ የትዳር ጓደኛ ካጋጠመን የመታዘዝ ኃላፊነት ያለብን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። አስፈላጊ ሲሆን እግዚአብሔርን እንደቃሉ በመኖር እያመለክን ለትዳር ጓደኛችን የስንፍና አሳብ ያለመገዛት እምቢተኝነት ምላሽ መስጠት ትክክለኛው ኃላፊነታችን ነው:: ይህም ማለት አንዳንድ ጊዜ ለሰው ባለመታዘዝ ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ተግባር የምንፈጽምበት ግዴታ ውስጥ እንገባለን ማለት ነው።

### 2. መሆን:- የባል እውነተኛ በሆነ ክርስቶሳዊ ፍቅር አገልጋይ መሪ መሆን

ክርስቲያን ባል ለሚስቱ አገልጋይ መሪ ሊሆን እንደሚገባው የእግዚአብሔር ቃል *"ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።"* /ኤፌ 5፡ 23/ በማለት ይመክራል። አገልጋይ መሪ ትዕዛዝ ሰጭ አለቃ በመሆን ለራሱ ግለ-ፍላጎት ብቻ የሚያስብና በሌሎች ላይ የሚሰለጥን አይደለም። የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት ስንመለከት ኢየሱስ በፈቃዱ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም አገልጋይ በመሆን የመራ መሪ ነው። *"እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።"* /ማቴ 20፡ 20-28፣ ፊል 2፡ 6-8፣ ማር 10፡ 45፣ ኤፌ 1፡ 22-23/ የቤተሰቡ አገልጋይ መሪ የሆነ ባል ኃላፊነትም የግል ፍላጎቱን፣ ጊዜውንና ገንዘቡን ለትዳሩና ለቤተሰቡ ጥቅም ማዋልንናና ሕይወቱን በሙሉ ፈቃዱ ለቤተሰቡ ደህንነትና

ሰላም በመስጠት መስዋዕት መሆን የሚጠይቅ ነው /ዮሐ 13፡ 1-15፣ 1ኛጴጥ 5፡ 3፣ 2ኛተሰ 2፡ 5-11፣ ፊል 2፡ 6-8/፡፡

የኢየሱስ አገልጋይ መሪነት ምሳሌነት ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው የክርስቶስ አገልጋይ መሪነት ምሳሌነት በሕዝቡ መካከል የሚሆን፣ ሲፈለግ ሊገኝ የሚችልና ከተከታዮቹ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው መልካም እረኛ መሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ ጴጥሮስ ባል ከሚስቱ ጋር እንዲሆን አጥብቆ እንዲህ ሲል ያዛል፡-*"እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።* /**1ኛጴጥ** 3፡ 7/፡፡ በመልካም ምሳሌነት በመምራት "ተከተሉኝ" እና "ምሳሌ ትቸላችኋለሁ" በማለት የተናገራቸው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃላቶች እዚህ ላይ መጠቀስ ያለባቸው ናቸው። በምሳሌነት መምራት ሌላው አካል ለመታዘዝና ለመገዛት እንዲችል የሚያበረታታና የኃላፊነቱን ክብደት የሚያቀልል መንገድ የማሳየት ሂደት ነው /**ፊል** 4፡9፣ 1ኛተሰ 2፡7-10፣ 1ኛጴጥ 5፡ 3/፡፡

ባል ለሚስቱ አገልጋይ መሪ ሊሆን ይገባል ሲባል በተቻለ መጠን በመንፈሳዊ ሕይወት፣ በቅድስና፣ በመሰጠት፣ በፅሞና ምሳሌና አርአያ ሊሆን ይገባል ማለት ነው። ፍፁም ምሳሌ የሚሆን ሰው (ባል) ሊኖር አይችልም! ነገር ግን ባል ጥፋት ባጠፋ ጊዜ እንኳን አጥፍቻለሁ፣ ተሳስቻለሁ፣ ኃጢአት ሰርቻለሁ ... በማለት ይቅርታ የሚጠይቅ በይቅርታ የመኖር ምሳሌና በየጊዜው ራሱን በማሻሻል የንስሃ ፍሬ እያፈራ የሚኖር ለመልካም ለውጥ የተዘጋጀ መሆን አለበት /**ፊል** 3፡ 12-14/፡፡

ሌላው ባል ለሚስቱ አገልጋይ መሪ መሆን የሚችለው ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት የሚችልና ኃላፊነትን የሚያካፍል በመሆን ነው። እንደ ክርስቲያን ባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ትክክለኛ፣ ጽድቅ የተሞላና አግባብነት ያለው ውሳኔ ሰጭ ሊሆን ይገባል። ግልጥ የሆኑ የኃላፊነትና የግዴታ አቅጣጫዎችን በማሳየት፣ ሚስት የራሷን ተነሳሽነትና ፈጠራ እንድትጠቀም እድል ለመስጠት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆን ይጠበቅበታል።

ባል ለሚስቱ አፍቃሪ መሪ የመሆን ሚና እንዳለው ቃሉ ይገልጻል፡፡ *"... እንደ ገዛ ሰጋው አድርጎ ይውደዳት"* እና *"ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ..."* /**በኤፌ** 5፡ 25፣ 28፣ 33/ የሚሉት ትዕዛዛት ባል ሚስቱን እንዴት መውደድ እንዳለበት መለኪያውን ግልጥ የሚያደርጉ ዘመን አይሽሬ መመሪያዎች ናቸው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንዲሁ የተሰጠ /**ሮሜ** 5፡ 8/፣ ጥልቀት ያለው /**ዮሐ** 13፡ 1፣ **ኤፌ** 3፡ 18-19፣ **ኤፌ** 5፡ 2፣25/፣ ራስ ወዳድ ያልሆነ /**ፊል** 2፡ 6-7/፣ መሥዋትነት የተሞላ /**ኤፌ** 5፡ 2፣25፣ ገላ 2፡ 20፣ 1ኛጴጥ 3፡ 18፣ ሮሜ 5፡ 6-11፣ 1ኛጴጥ 2፡ 24/ እና በቃልና በተግባር የሚገለፅ /**ዮሐ** 10፡ 1-14፣ 14፡ 1-3፣ 13፡ 34፣35፣ 15፡ 9-10፣ **ሮሜ** 8፡ 32፣ **ፊል** 4፡ 13፣ 19 **ዕብ** 4፡ 14-16/ ፍቅር ነው፡፡

ባል ለሚስቱ አፍቃሪና መሪ ባል መሆኑ የሚገለጠው፡- በፍቅርና በመልካም ቃላት በመግባባት፣ ለሚስት የሚያስፈልጋትን በማቅረብና በማሟላት /**1ኛጢሞ** 5፡ 8፣ 1ኛዮሐ





3፡17፣ **ኤፌ** 5፡ 28/፣ ሚስቱን ከተለያዩ ጉዳት አምጭ ነገሮች በመጠበቅ (በመከላከል)፣ ሚስቱን በሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ በመርዳት፣ ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ በመደጋገፍ /**ኤፌ** 5፡ 28/፣ ራስን በመስጠት (መሥዋዕትነት በመክፈል) /**ኤፌ** 5፡ 25፣ **ፊል** 2፡ 5-6/፣ ሕይወቱን እንድትካፈል በመፍቀድ /**1ኛጴጥ** 3፡ 7/፣ የትዳር አጋርን ከሌሎች ሴቶች ጋር ማወዳደርን በማስወገድ፣ በሕይወቱ የመጀመሪያ (ቀዳሚ) ስፍራ በመስጠት፣ የገባቸውን ተስፋዎችና የተናገራቸውን ቃላቶች በተግባር በማሳየት፣ የተለያዩ የሚያዝናኑ፣ የሚያስደስቱና የሚያበረታቱ ተግባራትን በማከናወን፣ አክብሮትን በመስጠት /**ኤፌ** 5፡ 28፣**ቆላ** 3፡ 19፣ **1ኛቆሮ** 13፡ 4-5/ እንዲሁም መልካምነቷን በምስጋና ውበቷን ደግሞ በአድናቆት በመግለጥ /**1ኛጴጥ** 3፡ 7፣ **ምሳ** 31፡ 28/ ሊሆን ይገባል።

## 3. መጀመር፡- አዎንታዊ ከሆነ አስተሳሰብ መጀመር

በትዳር መካከል ኃላፊነትን ባለመረዳት የሚፈጠር አንዳንድ የሥራ ብልሽት ሲፈጠር፣ ያልታሰበና ያልተፈለገ ነገር በሚከናወንበት ወቅት ፈጥኖ በቁጣ፣ በፍርድ፣ በሚያስደነግጥና ስሜትን በሚጎዳ መንገድ ከመቅረብ በፊት የአዎንታዊ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ለመልካም ግንኙነት መሠረት በመጣል ከባሰ ግጭት ጥንዶችን ይጠብቃል። አንዳንድ ያልተፈለጉ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ትዳርን ለመሥራት፣ የትዳር አጋርን ለመርዳትና ለመደጋገፍ ብለው በሚያደርጉት ጥረት እንደ ተሳሳቱ ከማሰብ በፊት ትልቁን መልካም አላማ ማየት ተገቢ ነው። ትልቁን መልካም ዓላማ ማየት የቻሉ ባለትዳሮች የትዳር ጓደኞቻቸው በቅንነት ትዳራቸውን ለመሥራትና ቤተሰባቸውን ለማገዝ በሚያደርጓቸው ድርጊቶች ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮችን በአዎንታዊ ሃሳብ በመገንዘብ በተረጋጋ መንፈስ መቃኘት የሚችል አስተዋይ አዕምሮ ያላቸውና ስህተትን ለማስተካከል እንኳን የተደረገውን ጥረት በማድነቅ የሚጀምሩ በሳል የፍቅር ሰዎች ይሆናሉ።

ባለትዳሮች ከእንዲህ ዓይነት መልካም መሠረት የግንኙነት ጉዟቸውን ሲጀምሩ አንዳንድ ጊዜ ነገሮች እንደታሰበው ሳይሆኑ ሲቀሩ የጥረቱን ውጤት፣ ለውጤቱ የሚሰጠውን ምላሽ፣ የተሠራውን ሥራና ያመጣውን መልካም ተጽዕኖ በማየት ሊፈጠር የሚችለውን ግጭት ሊያስቀር የሚችል እርምጃ መውሰድ አይቸግራቸውም። ቆይተው በጸጸት ላለመሞላት ነገሮችን በቀና መንፈስ የማየት ተገቢነትም ለእነርሱ እንግዳ አይደለም። ስለዚህ ይህንን በመረዳት ክርስቲያን ባለትዳሮች ሁልጊዜም በእንዲህ ዓይነት የሕይወት ውበት እየታነጽን የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ከመልካም አስተሳሰብ መጀመርን መማርና ያለማቋረጥ መለማመድ ይጠበቅብናል፡፡

## 4. መመልከት፡- ከጾታዊ ልዩነት ይልቅ ተሰጥዖንና ችሎታን መመልከት

ጾታዊ ልዩነት የሥራ ኃላፊነት የተለያየ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል። ሴት እንደ ሴትነት ተፈጥሮዋ ሚስት፣ እናትና እህት የመሆን ሚና ሲኖራት ወንድ ደግሞ እንደ

ወንድነት ተፈጥሮው ባል፣ አባትና ወንድም የመሆን ሚና አለው። እነዚህ ሚናዎች ተፈጥሯዊ ሚናዎች በመሆናቸው የምንቀበላቸው እንጂ በምርጫ የምንለውጣቸው አይደሉም:: ሌላኛው ከእነዚህ ውጭ መጠቀስ የሚችለው ሙያዊ የሆነው የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነት ምደባ ሲሆን ከባህልና ከልምድ በመነሳት ሙያዊ የሥራ ኃላፊነቶችን ጾታን መሠረት በማድረግ የመመደቡ ሂደት ያደግንበትና ዛሬም በብዙ ባለትዳሮች ቤት የሚታይ እውነታ ነው:: ይህ ጾታ ላይ ብቻ በማተኮር የሥራ ኃላፊነትን የመመደቡ ሂደት ተፈጥሯዊ ያልሆነና ሊለዋወጥ የሚችል የሥራ ኃላፊነት ቢሆንም ብዙዎች ባለትዳሮች ባህላዊ የሆነውን አመለካከት ብቻ በሚከተሉበት ጊዜ ለግጭት መነሻና መባባሻ ምክንያት ሲሆን ይታያል። ነገር ግን ባለትዳሮች ልንረዳው የሚገባን መሠረታዊ ጉዳይ በቤት ውስጥም ይሁን ከቤት ውጭ የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የቤተሰብ የሥራ ኃላፊነቶች ሙያን፣ ችሎታንና ተሰጥዖን እንጅ የግድ ጾታዊ ልዩነትን መሠረት ማድረግ የሌለባቸው መሆኑን ነው:: ስለዚህ የትዳር አጋርን ተሰጥዖው/ዋ/ ወይም ዝንባሌው ምንድን ነው? የትኛውን ሥራ ስኬታማ በሆነ መንገድ መሥራት ይቀለዋል/ላታል/? ስራውን ለማከናወን የተሻለ ሙያ ወይም እውቀት ያለው ማን ነው? ... የሚሉ ጥያቄዎችን ባግባቡ በመመለስና እርስ በርስ በመተዋወቅ፣ በመረዳዳት፣ የሥራ ኃላፊነትን የጾታ ልዩነትን ሳይሆን ተሰጥዖንና ችሎታን መሠረት በማድረግ ለትክክለኛው ሰው እየሰጠን ትዳራችንን መንከባከብ ጥበበኛነት ነው።

**የባልና የሚስት የሥራ ኃላፊነቶች ሙያን፣ ችሎታንና ተሰጥዖን እንጂ የግድ ጾታዊ ልዩነትን መሠረት ብቻ በማድረግ ማሰብና ማቀድ አይገባንም ።**

## 5. መጠበቅ፡- የጥንዶቹ የገቢ ምንጭ ምክንያት ቢሆኑም ባይሆኑም የሚዛናዊ ስሜት ባለቤት መሆን

በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈጠር የባል የገቢ ምንጭ ምክንያት በመሆንና አለመሆን ጊዜ የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች መፈጠራቸው የማይቀር ነው:: ባል ለቤተሰቡ ፍላጎት ማሟላት የሚያስፈልገውን ገቢ ማቅረብ በሚችልበት ወቅት አስቸጋሪ የሚባል ነገር ላይፈጠር ይችላል:: ይህ የተለመደ ማሕበረሰባዊ ባህል ነውና! ነገር ግን ባል ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ገቢ ማቅረብ ሲሳነው ይህን ሚናውን መወጣት የሚችል ባለመሆኑ ማሕበራዊ ዋጋው እንዳነሰ ስለሚሰማው የስነ ልቦናና የስሜት ቀውስ ሊፈጠርበት ይችላል:: ስለዚህ ባለትዳሮች ይህንን እውነታ በመረዳት የሚፈጠሩትን የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች አስቀድሞ መረዳትና መቆጣጠር ለመቻል መዘጋጀት ኃላፊነታቸው ነው። ከባህላችን አንጻር ወንድ ልጅ የገቢ ምንጭ ሆኖ መኖሩ በተለመደበት ማሕበረሰብ አውድ ውስጥ በሚስት የገቢ ምንጭነት የሚገኝን ገቢ የቤተሰብ መተዳደሪያ አድርጎ በትዳር በሰላም መቀጠል የበታችንነት ስሜት ይፈጥርበታል። ይህ የበታችነት ስሜት





በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ፣ ንዴታም፣ ቁጡ፣ መራርና ተነጫናጭ ያደርገዋል። እነዚህ ስሜቶች በጥንዶች የኮሙኒኬሽን ክህሎት ላይ የሚፈጥሩት አሉታዊ ተጽዕኖ ደግሞ ቀላል የሚባል አይለም።

በባል ላይ የበታችነት ስሜት እየተፈጠረ ባለበት ወቅት ደግሞ በተቃራኒው ለቤቱ የገቢ ምንጭ የሆነችው ሚስት የበላይነት ስሜት ሊሰማት ይችላል። ሚስት የበላይነት ስሜት የተሰማት ከሆነ ቀድሞ ምንም ምርጫ ባልነበረበትና ምናልባትም ባል ሠርቶ በሚያስገባው ገቢ ብቻ በሚተዳደሩ ጊዜ በመካከላቸው የነበረው መቀባበል ይጠፋል። ባል ለሚያሳየው የነጭናጭነትና የቁጡነት ስሜታዊነት ሚስት በኩራትና በማን አለብኝነት አጸፋዊ የትዕቢት ምላሽ ትሰጣለች:: ይህ ዓይነት ባሕርይ ካሁን በፊት አሳይታ ስለማታውቅ ባል የሚስቱን የባሕርይ ለውጥ ሲያይ ገንዘብ ስለሌው የተናቀና ተቀባይነት ያጣ መሆኑ የበለጠ ይሰማዋል:: ጥንዶቹ የተፈጠረው ችግር ገብቷቸው ነገሩን በመረዳት በተረጋጋ ስሜት ሊቃኙትና ተወያይተው ሁኔታውን ሊያረግቡት ካልቻሉ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው እየተባባሰ ወደከፋ አለመግባባትና ግጭት ያድጋል:: የበላይነት ስሜት ሲፈጠር አንዱ ለሌላው ሊኖረው የሚገባ መታዘዝ ሊጠፋና በምትኩ በበላይነት የመቆጣጠርና እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የማለት ልምምድ ውስጥ መግባትን ያስከትላል::

የበላይነት ስሜት የተሰማው የትዳር ጓደኛም በቤት ንብረቶች ላይ የሌላውን አካል የመጠቀም ነፃነት የመገደብ፣ በሁሉ ነገር ላይ በበላይነት የመሰልጠንና ግለኝነትን የመንከባከብ ፍላጎቱ እየጨመረ ስለሚመጣ ትዳራቸው ለበለጠ ቀውስ ተጋላጭ ይሆናል:: የጥንዶቹ የትዳር ግንኙነትም የተገነባበት መተማመን እየተሸረሸረ በጥርጣሬ የሚሻከርበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ስለዚህ ባልና ሚስት አስቀድመው በትክክለኛ እውቀት በመታነጽ ቤተሰብን የመመገብ ኃላፊነት የሁለቱም ሚና እንደሆነ መረዳት አለባቸው:: ከዚያም ቢቻል ሁለቱም ያለዚያ ደግሞ ባሉት የሙያና የእውቀት ሀብቶች ምክንያት የተሻለ ገቢ ማምጣት የሚችለው የትዳር ጓደኛ ሠርቶ በሚያስገኘው ገቢ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቤተሰባቸውን የማስተዳደር ብስለትና ስምምነት ሊኖራቸው ይገባል።

ሥራን መሥራት እንድንችልና የቤተሰብ የገቢ ምንጭ ምክንያት እንድንሆን የረዳንና የሚረዳንም እግዚአብሔር ነው። እኛም በማናችንም በኩል ቤተሰብ የሚተዳደርበት ገቢ የተገኘ ቢሆንም እንኳን በጸጋውና በመልካም አዘጋጅነቱ የረዳንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን በተሰጠን ገንዘብና ንብረት የትዳር አንድነታችንና ቤተሰባዊ ደህንነታችንን ልንጠብቅበት ይገባል። በዚህ መርህ አስተሳሰባቸውንና ስሜታቸውን በማሰልጠን ባሎች ሊፈጠርባቸው ከሚችል የበታችነት ስሜት፤ ሚስቶችም ሊፈጠርባቸው ከሚችል የበላይነት ስሜት ሕይወታቸውን በመጠበቅ አሁን ያለውን

ሁኔታ በመቀበል በትህትናና በመታዘዝ ግንኙነትን ለመጠበቅ የሚችል ማንነት ይዘው መገኘት ተገቢ ነው።

## 6. መፍቀድ፡- አንዳንድ ጊዜ ለየት ያለ አጋጣሚንና ልምምድን ለማስተናገድ መፍቀድ

በትዳር ሕይወት ውስጥ በጥንዶቹ ግንኙነት መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩና ያልተጠበቁ ክስተቶችን ለመቀበል አስቀድሞ ማሰብና የአዕምሮና የስሜት ዝግጅት ማድረግ ከጥንዶቹ ይጠበቃል፡፡ በትዳር ውስጥ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ የተለያዩና ያልተጠበቁ ክስተቶች ጥቂቶቹ፡- መውለድ አለመቻል፣ እርግዝና፣ መውለድ፣ አከታትሎ መወለድ፣ ውርጃ፣ ከወሊድ በኋላ የሚፈጠር ድብርት ወይም ሌላ ያልተጠበቀ ክስተት ... የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላው በሕይወት የሚገጥሙ ውጣ ውረዶች፣ ከፍታና ዝቅታዎች፣ የጤንነትና የሕመም ወቅቶች፣ የደስታና የሐዘን ጊዜያት፣ የማግኘትና የማጣት... ሁኔታዎችም ሊፈራረቁባቸው ይችላሉ። እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ በሞት መለየት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በእነዚህ አስቸጋሪና የጭንቀትና የደስታ ጊዜያት፣ ምንም ማድረግ በማይቻልበት ወቅትና ነገሮች እንደጠበቅናቸውና እንደ አጀማመራቸው ባልቀጠሉ ጊዜ አንዱ የሌላውን ኃላፊነት የመሸፈን፣ የሌላውን ሚና የመወጣትና የመረዳዳት ባህል እንዲኖረን አስቀድሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ባል የሚስትን፣ ሚስት የባልን የተለመደ ሙያና ኃላፊነት ለሚጠይቁ ወቅቶች የትዳር አጋራቸውን ጠንካራ ጎን የመጠቀምን አስፈላጊነት በሚችሉት መጠን ጥንዶች ሁሉ መረዳታቸውና ለመቀበል ዝግጁ ሆነው መገኘታቸው አስተዋይነት ነው።





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ አንድ (11)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የባልና የሚስት ኃላፊነትና ሚና ማለት ምንድን ነው?
2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የባልና የሚስት ኃላፊነትና ሚና ምንድን እንደሆነ በዝርዝር ተወያዩበት፡፡
3. እንደ ባልና ሚስት ብሎም እንደ አባትና እናት ለግጭት መንስኤ የሆኑና ያልተወጣናቸው ኃላፊነቶችና ሚናዎችን ለይቶ ለማውጣት በፍጹም ነፃነት ውይይት አድርጉ።
4. ሚስት ለባሏ ትገዛ የሚለውንና ባል ሚስቱን ይውደድ በሚለው አምላካዊ ትዕዛዝ ላይ በመወያየት ለውጥ በሚያስፈልጋችሁ አስተሳሰብና ተግባር ላይ እርምጃ ለመውሰድ ተነጋገሩበት፡፡
5. አንድ ጊዜ የቤታችሁን የሥራ ክፍፍል በመቃኘት እንዴት የሥራ ክፍፍል እንዳደረጋችሁ፣ የሥራ ኃላፊነት ጫና ማን ላይ እንደሚበዛና የሥራ ክፍፍላችሁህ ምንን መሠረት በማድረግ የተከፋፈለ እንደሆነ በግልጥነት ተወያዩ፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሁለት(12)
# ፖርኖግራፊ

## I. የፖርኖግራፊ ምንነት

*ፖርኖግራፊ፡-* በዘመናዊውና በድህረ ዘመናዊው ዓለም ውስጥ የወንድና የሴት የግል የሰውነት ክፍሎችንና ጾታዊ እንቅስቃሴዎችን በማሳየት ሰዎችን ለፍትወት ለማነሳሳት በጽሁፍ የታተመ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስልነት የሚታይ ልቅ የወሲብ ግንኙነት ትእይንት ነው። በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ቦታዎች ሰዎችን ስለወሲብ ግንኙነት፣ ስለወሲብ ግንኙነት የተለያዩ አቅጣጫዎችና እንቅስቃሴዎች፣ በአጠቃላይ ስለ ወሲብ ነክ ተግባራትና የወሲብ ግንኙነት እርካታን ለማሳየት፣ ለመግለጥና ለማስተማር ይጠቀሙበታል። ፖርኖግራፊ ዛሬ ዛሬ ኢንዱስትሪ ሁኖ ዓለምን ከማጥለቀለቁ በፊት በቅርጻ ቅርጽ፣ በስዕልና በስነፅሑፍ ላይ ብቻ ይታይ ነበር። በአሁኑ ወቅት ፖርኖግራፊ የተለያዩ ሚዲያዎችን፣ መጽሔቶችን፣ ፖስት ካርዶችን፣ ስዕሎችን፣ ቅቦችን፣ ድምጾችን፣ ፊልሞችን፣ ቪዲዮዎችንና የቪዲዮ መጫዎቻወችን በመጠቀም ወሲብ የሚስፋፋበት ዋና መንገድ ሆኗል።[41]

በተለይም ዛሬ የመገናኛ መረብ (ኢንተርኔት) ዓለምን እንደ አንድ መንደር ማስተሳሰሩን ተከትሎ የጾታ ስሜትን የሚያነሳሱ ወሲባዊ ቪዲዮዎችን፣ ሥዕሎችንና ጽሑፎችን በመጠቀም የሰለጠነው ዓለም ቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሆኑ የዓለማችን ዳርቻዎችን ሁሉ ሳይቀር በማጥለቅለቅ ላይ መሆኑ ሙግት የማያስፈልገው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ሰዎችን ለወሲብ ለማነሳሳት ሲባል በመረጃ መረብ (በኢንተርኔት) አማካኝነት ስለፖርኖግራፊ ገንዘቤ ለሌላቸው የመረጃ መረብ ተጠቃሚዎች ሳይቀር ሳይፈልጓቸው የሚላኩ የተለያዩ ወሲባዊ ይዘት ያላቸው ጽሑፎች፣ ፎቶዎች፣ ማስታወቂያዎችና ቪዲዮዎችን ሥራየ ብለው የሚያሰራጩ ሰዎች መኖራቸው ደግሞ ጉዳዩን እያባባሰው ይገኛል። ቀውሱ በጣም መስፋፋቱም ለመልካም ዓላማ የምንጠቀምባቸውን ስልኮቻችንን ሳይቀር ሰዎችን ለወሲብ ፍላጎት የሚቀሰቅሱና የሚያነሳሱ ወሲባዊ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ለመለዋወጥና መልክቶችን ለማስተላለፍ አገልግሎት በማዋል ከፍተኛ በሆነ መንገድ የሞራልን ክቡርነት ዝቅ የሚያደርግና የሚያራክስ አፍራሽ ተጽዕኖ በሰዎች ላይ እንዲያሳድሩ እያደረገ ነው።

## II. የፖርኖግራፊ መስፋፋት

አሁን ያለንበት ዘመን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የወሲብ ልቅነት እየጨመረ የመጣበት ዘመን ነው። ይህ የወሲብ ችግር ከጥንት የነበረ የሰዎች ችግር ቢሆንም የመረጃ መረብ (የኢንተርኔት) ዓለምን እየተቆጣጠርና እያጥለቀለቀ በመምጣቱ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መስፋፋቱ ይበልጥ እየጨመረ የሚሔድ መሆኑን ለመተንበይ ነቢይ

[41] Clinton, Tim & Hawkins, Ron. Biblical Counseling p195





አያስፈልገንም። በአገራችን በኢትዮጵያም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢንተርኔት እየተስፋፋ ለመሆኑና ብዙዎች የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች እየሆኑ ለመምጣታቸው የአይን ምስክሮች ነን። ሰዎች ለመዝናናትና ለማረፊያነት የሚጠቀሙባቸው ሆቴሎች ነፃ የሆነ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሆን አለመሆናቸው የደንበኞች ቋሚ ጥያቄ ከሆነ ሰንበት አድርጓል:: ሆቴሎችም ደንበኞችን ለመሳብ ከሚጠቀሙባቸው ዋና መንገዶች አንዱና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣው ነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት አለ የሚለው ማስታወቂያ ነው::

ከኢንተርኔት አገልለግሎት መስፋፋት ጋር በመያያዝ ሊነሳ ከሚገባው የቴክኖሎጅው እድገት አሉታዊ ተጽዕኖ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ፖርኖግራፊ ነው። በኢንተርኔት ዓለም ካሉት የተለያዩ ድረ ገጾች መካከል የፖርኖግራፊ ድረ ገጾች ሳይት ብዛት 4.2. ሚሊዮን ሲሆን ይህም ከሌሎች ብዙ ከሆኑ የተለያዩ ድረ ገጾች ጋር ሲነፃፀር የአጠቃላዩን ድረ ገጽ 12% ያህሉን እንደሚይዝ መረጃዎች ያሳያሉ።[42] በየቀኑ 68 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች የፖርኖግራፊ ድረ ገጾችን ይጎበኛሉ። ይህም በአጠቃላይ ከሚጎበኙ ድረ ገጾች ጋር ሲወዳደር 25% ያህሉን ይይዛል። የፖርኖግራፊ ሱስ ከሌሎች ሱሶች በበለጠ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን፣ ያገቡትንና ያላገቡትን፣ የተማሩትንና ያልተማሩትን... ሊያጠቃ የሚችል ሱስ ነው። በአንድ ጥናት የቀረበ ማስረጃ እንደሚያሳየው በዚህ ሱስ ተጠምደው ቆይተው ከዚህ ሱስ ለመላቀቅና ነፃ ለመውጣት ቃል ከገቡ ሰዎች መካከል 53% ያህሉ እንደገና ወደ ተጠመዱበት ሱስ እንደተመለሱ አስረድቷል ማለትም ከግማሽ በላይ የሆኑት ሱሰኞች ከተጠመዱበት ሱስ ነጻ የመውጣት ጥረታቸው አልተሳካላቸውም። በአሜሪካን አገር የፖርኖግራፊ ድረ ገጽ ለክርስቲያን ባለትዳሮችም ከፍተኛ ችግር የመሆን ተጽእኖው 47% እንደደረሰ በዚህ ጥናት ውጤት ተገልጧል።[43]

## III. የፖርኖግራፊ ተጠቃሚዎች አመለካከት

ብዙ ክርስቲያኖች በሕይዎት በመድከማቸው ብሎም ለአመጽ እጃቸውን የሰጡና መለወጥ ያቃታቸው በመሆናቸው የቅዱሳት መጽሐፍት ጥቅሶችን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ለደካማ ህሊናቸው ምላሽ ለመስጠት ጥረት ያደርጋሉ:: አእምሮቸውን ትክክለኛ ባልሆኑ አመለካከቶች በማሳመንና ልባቸውን በማደንደን እርኩሰት ለሞላበት ሕይወት ፈቃዳቸውን ይሰጣሉ:: በዚህ ሂደት ለፖርኖግራፊ ተጋላጭ የሆኑ ክርስቲያን ወጣቶች፣ ላጤዎችና ባለትዳሮች ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። አንዳንድ ያልተለወጡና

[42] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to sexuality and relationship counseling Baker books, a division of baker publishing Group: Grand Rapids, Michigan, 2010. p158

[43] Clinton, Tim & Laaser, Mark. The Quick-Reference Guide to sexuality and relationship counseling p158

የዚህ አስከፊ ሱስ ሰለባ የሆኑ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚጽፉትና የሚያስተምሩት ዝሙትን የሚያስፋፋና ባለትዳሮችን ከትዳራቸው ውጭ የዝሙት ሰለባ እንዲሆኑ የሚጋብዝና የሚያበረታታ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ደግሞ ሰዎች ከአመጻቸው በመፀፀት በንስሃ እንዳይመለሱ ይልቁንም እንደ መልካም ነገር እየቆጠሩት በልምምዱ ውስጥ እንዲሰነብቱ ያደርጋቸዋል:: ከዚህም ባሻገር በአሁኑ ወቅት ሌሎችን በዚህ ከፉ የተጽዕኖ መረባቸው ውስጥ ለማስገባት ጥረት ያደርጋሉ:: ክርስቲያኖች የዚህ ቅድስናንና ጽድቅን የሚቃረን ልምምድ ሰላባ እንዳይሆኑ ለማስጠንቀቅና ልምምዱን አጥብቆ በማውገዝ የጋብቻን ሕይወት ክቡርነት፣ የትዳርን ጤንነትና አንድነት በመጠበቅ እንዲኖሩ ግንዛቤ የማስጨበጡንና አቋም እንዲይዙ የመርዳቱን ዓላማ ለማሳካት በዚህ በሶስተኛው ነጥብ የፖርኖግራፊ ተጠቃሚዎችን አመለካከትና ፍልስፍና እንደሚመለከተው በመዘርዘር እንቃኛለን፡-

## 1. ተጎጅ የሌለበት ኃጢአት

ዓለምን እያጥለቀለቀና ብዙዎችን ሰዎች እያጠቃ ያለው የፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑና ተጠቃሚ ለመሆን የሚዳዳቸው ብዙ ሰዎች ለድርጊታቸው የሚያቀርቧቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው። አእምሮቸውን ለማሳመን ከሚጠቅሷቸው ምክንያቶች አንዱ ማንም ተጎጅ ያልሆነበት ኃጢአት ነው በማለት የሚጠቅሱት አጥፊ መርህ ነው። ይህ መንገድ የግብረ ስጋ ፍላጎትን ለማርካት በሚደረገው ሂደት የሌላ ተቃራኒ ጾታ አካል፣ ስሜትና ስነ ልቡና የማይጎዳበት መንገድ መሆኑን በማስረዳት ራሳቸውን ያታልላሉ። የሌላኛው ሰው አካል ብቻ ሳይሆን በፍትዎት ችግር ምክንያት የግብረ ስጋ ግንኙነት ለሚፈልገውና ለሚጠቀመው ሰውም የሚፈጠርበትና የሚገጥመው ችግር አለመኖሩንም ያስረዳሉ። ክርስቲያን የፖርኖግራፊ ተጠቃሚዎች ልምምዱ ኃጢአት መሆኑን ቢያምኑም ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር ከመገዛት ይልቅ ለራሳቸው ተድላና ምኞት መሟላት በመኖር ለስጋዊ ፍላጎታቸው ብቻ ለመገዛት የሚያስቡ ራስ ወዳድ መሆናቸው መሠረታዊ ችግራቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በዘመን መጨረሻ እንዲህ ዓይነቱ የሕይወት ቀውስ እየተባባሰ እንደሚሄድ ሲያስረዳ፡- *"ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤"* /**2ኛጢሞ 3፡ 1-4**/ በማለት ይናገራል::

## 2. ሌላ መዘዝ የሌለበት የፍትዎት ፍላጎት ማርኪያ መንገድ

እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ትኩረታቸው ኃጢአት መሥራታቸውና አለመሥራታቸው ላይ ሳይሆን ልቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊያስከትልባቸው የሚችለውን መዘዝ በማሰብ ራሳቸውን የፖርኖግራፊ ደንበኛ አድርገው በዝሙት ከሚመጡ ልዩ ልዩ





መዘዞች ማስመለጣቸው ላይ ነው።[44] የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ ቪዲዮዎችንና ፎቶግራፎችን... በመመልከት የፍትዎት ፍላጎታቸውን ለማርካትም ይጥራሉ። በዚህ መንገድ በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ያልተፈለገ እርግዝናና ተላላፊ በሽታዎች ጉዳት ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ይህን የሕይወት መስመር መከተል ይመርጣሉ። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን ከተላላፊ በሽታዎች መጠበቃቸውንና ከኃላፊነትና ከተጠያቂነት ማስመለጣቸውን እንጂ ባሪያ በማድረግ በሚገዛቸው የፍትዎት ኃጢአት ሱስ መጠመዳቸውን አላስተዋሉትም። *"ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።"* /**ያዕቆብ 1፡ 14-15**/

## 3. ማስተርቤሽን/ ግለ ወሲብ /

ይህ ሂደት የራስን የፍትዎት ፍላጎት በራስ የማሟላት የወሲብ ስሜትን ማርኪያ መንገድ እንደሆነ ይህንን ልምምድ የሚያዘወተሩ ሰዎች ያስባሉ። አንዳንዶች የራስን ስሜት በራስ በማርካት ጥሩ ስሜት ይፈጥራል ብለው ሲናገሩም ይደመጣሉ። ሌሎች ደግሞ እንዲህ ዓይነቱ የራስን የፍትዎት ፍላጎት በራስ የማርካት መንገድ የትዳር አጋር በቅርብ በማይኖርበት ጊዜ አስፈላጊ አማራጭ እንደሆነም ያምናሉ:: ራሳቸው የራሳቸውን የፍትዎት ፍላጎት ለማርካትም ይጠቀሙበታል። የራስን የፍትዎት ፍላጎት በራስ ማርካት የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ውጥረትን ይቀንሳል ደግሞም እርግዝናንና ተላላፊ በሽታን ይከላከላል በማለትም በአእምሯቸው ለሚሰማቸው የበደለኝነት ስሜት ምላሽ ይሰጣሉ::[45] ለፍትወትም ራሳቸውን ያበረታታሉ። *"ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከዝሙት እንድትርቁ፥ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ምኞት ሳይደለም እንጂ፥ ከእናንተ እያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ፤"* /**1ኛተሰ 4፡ 3-5**/ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መርህ ባለመታዘዝ የእርኩሰት መንገድን በመምረጥም ክቡር የሆነውን ሰውነታቸውን ያዋርዳሉ::

# IV. ፖርኖግራፊ በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

## 1. ኃጢአት ነው

ስለፖርኖግራፊ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት የእግዚአብሔርን ቃል አሳብ ለማስቀደምና ለቃሉ ለመታዘዝ ይረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ ውጭ የሆነ ማንኛውም የፍትዎት ምኞትና ልምምድ ኃጢአት እንደሆነ፡- *"እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው።"* /**ቆላ 3፡ 5፤ 1ኛተሰ 4፡ 3-5**/ ሲል ይገልጻል:: በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ ወደ ሴት ማየትና መመኘት ኃጢአት እንደሆነ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ያስረግጥልናል። *"አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥*

[44] sexuality and relationship counseling p.158

[45] sexuality and relationship counseling p.157

*ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"* /**ማቴ** 5፡ 27-28/። ስለዚህ ከእንዲህ ዓይነቱ የፍትዎት ምኞትና ድርጊት መሸሽ እንጅ በምንም ዓይነት ምክንያት ከጋብቻ ውጭ ወደ ሆነ ማንኛውም ዓይነት የወሲብ ልምምድና ፍትዎትን የሚያነሳሳ ተግባር መሳብ ኃጢአት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነትም አስረግጦ የሚያስተምረውና የሚመከረው ይህንን ነው፡፡ ከዚህ እውነት ጋር በመስማማት መኖር የእያንዳንዱ ክርስቲያን በተለይም ደግሞ ቤተሰብ በመባል የሚጠሩት ትናንንሽ አብያተ ክርስቲያናት መሪና አገልጋይ የሆኑት የባልና ሚስት ኃላፊነትና የክርስቲያናዊ ሕይወትና አገልግሎታዊ አደራ ግዴታ ነው። *"ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል"* /**፩ቆሮ** 6፡ 18/፡፡

## 2. ስጋዊ ምኞት ነው

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ዓይነቱን ልቅ በፍትወት የመቃጠልና የወሲብ ልምምድ ሱስ ነፍስን የሚዋጋ ስጋዊ ምኞት በማለት ይጠራዋል። ክርስቲያኖች ለዚህ ምድር እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችን መጠን እንዲህ ዓይነቱን ሰዎችን ለስጋዊና ዓለማዊ ምኞት ተገዥ የሚያደርግ ልምምድ ማስወገድና ከዚህ መራቅ ይጠበቅብናል። *"ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤"* /**፩ጴጥ** 2፡ 1/፡፡

## 3. እንዴት መመላለስ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል

እንደ ክርስቲያን ባለትዳርነታችን መጽሐፍ ቅዱስ ምትክ የለሹና ብቸኛው የግልና የቤተሰብ ሕይወት መመሪያችን ነው፡፡ ይህ የሕይወት መመሪያችን እንዴት መኖርና መመላለስ እንዳለብን አሻሚ ባልሆነ መንገድ በግልጥ ይመክረናል። ቃለ እግዚአብሔር እንደ ብርሃን ልጆች የብርሃን ምሳሌነት የተሞላው ሕይወት እንድንኖር ያዛል። ክርስቲያን ሊመላለስበት የማይገባው ኑሮ፤ በዘፈንና በስካር፣ በዝሙትና በመዳራት እንዲሁም በክርክርና በቅናት መመላለስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ እርሱን በመልበስና በማሳየት መመላለስ እንዳለብን ይገልጣል። በእርግጥም ለፍትዎት ፍላጎት አልፈን እንዳንሰጥ ስለስጋ ማሰብን ማቆምና ስለመንፈሳዊና ስለሰማያዊ ጉዳይ ማሰብ እንዳለብን *"በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በስካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።"* /**ሮሜ** 13፡ 13-14/ በማለት የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በመስማትና በመታዘዝ መኖር ይጠበቅብናል።

## 4. ቅጣቱ የከፋ ነው

የፍትዎት ስሜትን ለማርካት ፖርኖግራፊን የሚጠቀሙና የሚለማመዱ ሰዎች በፍትዎት ሱስ የተጠመዱ የዘመናችን ሴሰኞች፣ አመንዝራዎች፣ ጋለሞታዎችና ዘማውያን ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት የሕይወት ልምምድን ፈቅደውና ፈልገው የሚያዘወትሩ ዘማውያን በሱሰኝነት ከመጠመዳቸውም ባሻገር ንስሃ ካልገቡና ከልምምዱ ፈጥነው የማይወጡ ከሆነ አምላካዊ ፍርድና ቅጣት ያገኛቸዋል፡፡ ቀስ በቀስና ደስ በሚል





ቅጽበታዊ የደስታ ስሜት ተውጠው ፍጻሜው ግን እንደ እሬት ወደ መረረና ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍ ወደተሳለ ሞትና ሲኦል በመውረድ የሕይወትን መንገድ እንደማያገኙት መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። *"ከጋለሞታ ሴት ከንፈር ማር ይንጠባጠባልና፥ አፍዋም ከቅቤ የለሰለሰ ነውና፤ ፍጻሜዋ ግን እንደ እሬት የመረረ ነው፥ ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍም የተሳለ ነው። እግሮችዋ ወደ ሞት ይወርዳሉ፥ እርምጃዎችዋም ወደ ሲኦል ነው፡፡ የቀና የሕይወትን መንገድ አታገኝም በአካሄድዋ የተቅበዘበዘች ናት፥ የሚታወቅም አይደለም።"* /**ምሳሌ** 5፡ 3-6/ ይህን የእግዚአብሔር ፈቃድ በመረዳት በልምምዱ ውስጥ የገቡና በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ፈጥነው በንስሃ ሊመለሱ ይገባል፡፡ *"ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤"* /**ራዕ** 2፡ 21-23/ የሚለውን አምላካዊ የንስሃ ጥሪ በመስማት ንስሃ ለመግባት ለሚፈልጉ ሰዎች ደግሞ አሁንም የመመለስ ጊዜው ገና አልመሸባቸውም፡፡ የፖርኖግራፊ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችንና ፎቶግራፎችን... ወደማየትና ወደዚህ ርኩሰት የተሞላ ሱስ ልምምድ ያልገቡ ክርስቲያኖች ደግሞ ከእንዲህ ዓይነቱ ክቡሩን ሰው የሚያዋርድ ልምምድ ሕይወታቸውንና ቤተሰባቸውን እንዲጠብቁ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምራል።

# V. ባለትዳሮችን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ የሚያደርጉ ምክንያቶች

## 1. አጋጣሚ

ሰዎች መጀመሪያ በተለያየ መንገድ ከፓርኖግራፊ ልምምድ ጋር ይተዋወቃሉ ከዚያም ለፖርኖግራፊ ሱስ አልፈው ይሰጣሉ። ይህ ከሚከናወንባቸው የተለያዩ መንገዶች መካከል አንዱ እንደ አጋጣሚ ሌሎች እያዩአቸው ከነበሩ ከፖርኖግርፊ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ፊልሞች፣ የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራምና በኢሜል አድራሻቸው ወደሚጠቀሙበት ኮምፒዩተር ከሚመጡ ፖርኖግራፊ አዘል መልእክቶች ጋር በመገናኘት ምክንያት የሚጀመር በፖርኖግራፊ ሱስ የመጠመድ አጋጣሚ ነው። እነዚህ ሰዎች መጀመሪያ ላይ በድንገት ከፖርኖግራፊ ልምምድ ጋር የተዋወቁ ቢሆንም ከዚያ በኋላ ግን ራሳቸው እያሰቡና ምክንያት እየፈለጉ የፖርኖግራፊ ተጠቂዎችና ከትዳር ውጭ የፍትዎት ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚደረግ ርኩሰት የሞላበትን የአመንዝራነት ኃጢአት መለማመድ ይጀምራሉ።

## 2. ጓደኞች (በወዳጆች)

ክፉ ባልጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል አንዳንዶች በፖርኖግራፊ ሱስ ወደ መያዝ የሚገቡት በዚህ የወሲብ ሱስ በተጠመዱ ጓደኞቻቸው ምክንያት ነው። በተለያየ ምክንያተ ቅርብ ጓደኝነት መሥርተው አብረው የሚጓዙ ሰዎች እርስ በርስና አንዱ በሌላው ላይ በተለያየ መንገድ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ማምጣቸው አይቀሬ ነው። አንዳንዶች በቀናነት ሌሎችን ነገሮች እንደሚከፋፈሉ ይህንም ልምምድ አንዱ ለሌላው ማካፈል ይጀምራሉ። ሌሎች ደግሞ

አመጽ መሆኑንና በሕይወታቸውም ሆነ በትዳራቸው ላይ እያመጣ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ እያወቁ በዓላማ ሌሎችን ጓደኞቻቸውን በክፉ ወጥመዳቸው በማስገባት የከፋታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። ስለዚህ ክርስቲያን ወገኖች መልካም አመል የሌላቸው ጓደኞቻቸው ክፉ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩባቸውና ወደ ቀውስ እንዳይመሯቸው ሕይወታቸውንና ቤተሰባቸውን መጠበቅ አለባቸው:: በተቃራኒው ግን በክፉ ተጽዕኖ ሥር ያሉና በኃጢያት ርኩሰት ባርነት የተያዙ ሰዎች ነፃ እንዲወጡ በእግዚአብሔር ቃል የእውነት መልዕክት፣ በጽድቅ ኑሯቸውና እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ መርዳትና የጽድቅ ተጽዕኖ ማሳደር የሚኖሩለት ዓላማ ሊሆን ይገባል::

## 3. የትዳር ጓደኞች

አንዳንዶች ደግሞ የትዳር አጋሮቻቸው ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊትም ሆነ በኋላ በዚህ የወሲብ ልምምድ ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት በፖርኖግራፊ ሱስ ይጠመዳሉ:: የትዳር ጓደኛቸውንም ወደዚህ ወጥመድ ይመራሉ። የፖርኖግራፊ ሱስ ተጠቂ የሆኑ የትዳር አጋሮቻቸው በሚያቀርቡላቸው ግብዣ፣ ማበረታታቸና አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት ከፖርኖግራፊ ምስሎች አቅራቢ ድረ-ገጾችና የሚዲያ ማሰራጫዎች ጋር ይተዋወቃሉ። አንዳንድ ባለ ትዳሮች ደግሞ በቀጥታ በትዳር ጓደኞቻቸው ባይጋበዙም እንኳን የትዳር አጋሮቻቸው ሲመለከቷቸው የነበሩ የፖርኖግራፊ ድረ-ገጾች ወይም የቪዲዮ ምስሎች ሳይዘጉ እንዲሁ ያገኟቸዋል:: ይህ ክስተት አንዳንድ የትዳር አጋሮችን ሊያስቆጣ ቢችልም አንዳንዶችን ግን የድርጊቱ ተባባሪ እንዲሆኑ ያደረጋቸዋል።

## 4. ማሕበራዊ ድረ-ገጾች

ማሕበራዊ ድረ ገጾች የሚባሉት እንደ ፌስ ቡክ፣ ቲውተር፣ ዩቲዩብና ሌሎች በመገናኛ መረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት ማሕብረሰቡን የሚያገናኙ ድረ-ገጾች ሁሉ ናቸው። እነዚህ ማሕበራዊ ድረ-ገጾች በብዙ መንገድ የሚጠቅሙንንና የምንጠቀምባቸውን ያክል በዚያው መጠን የተለያዩ ፖርኖግራፊ አዘል የሆኑ ማስታወቂያዎች፣ ለወሲብ የሚያነሳሱ የተለያዩ የተቀራኒ ጾታ ፎቶዎች፣ ጽሑፎች፣ ስዕሎችና ቪዲዮዎች ይቀርቡባቸዋል:: በዚህም ምክንያት ፖርኖግራፊ ከመቼውም በበለጠ እየተስፋፋ ብዙዎችን ተጠቂ እያደረገና የብዙዎችን የትዳር ግንኙነት እያሻከረ ያለ አመጻዊ ልምምድ ሆኗል። ለምሳሌ:- ፌስ ቡክ የሚጠቀሙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሳይቀር ባለትዳር እንዳልሆኑ በመናገርና ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተዋወቅ የፍቅር መሳሳብ የሚጀምሩበትና ከትዳር አጋሮቻቸው የተደበቀ ሌላ ኢሜል፣ የፌስ ቡክ አካውንትና የስልክ ቁጥር በማውጣት ግንኙነታቸውን በድብቅ የሚቀጥሉበት ድረ-ገጽ አድርገው ይጠቀሙበታል። አንዳንዶች አገልግሎት የሚፈልጉ ሰዎችን እያገለግልኩ ነው ወይም እየረዳሁ ነው.የሚሉ ምክንያቶችን በመስጠት በድፍረት ጤነኛ ያልሆነ አሳባቸውን እየቀጠሉ ወደተወሳሰበ ግንኙነት ይገባሉ።





## 5. የሌላን ሰው ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ መጠቀም

አንድ አንድ ጊዜ በጣም ወሳኝ ሥራ ሲያጋጥመን ወይም አስፈላጊ ጉዳይ ሲኖረን የሌላውን ሰው ማለትም የወዳጅ፣ የስራ ባልደረባ፣ የቅርብ ወይም የሩቅ ዘመድ የግልም ሆነ የመሥሪያ ቤት ላፕቶፕና ዴስክቶፕ ኮምፕዩተሮች ተጠቃሚዎች እንድንሆን እነገደዳለን። ይህ ዓይነት በጋራና በመዋዋስ አንድን ኮምፕዩተር በጋራ የመጠቀም ሁኔታ ሲፈጠር የችግሩ ተጠቂ ያልሆኑ ሰዎች የሚጠቀሙበት ኮምፕዩተር ላይ የተጫኑና ሌሎች ሰዎች ሲመለከቷቸው የነበሩ የፖርኖግራፊ ድረ-ገጾች እንደተከፈቱ ያገኛሉ:: እነዚህን ካሁን በፊት የማይታወቁና በሌላ አጋጣሚ ሊገኙ የማይችሉ ድረ-ገጾችን በቀላሉ ተዘጋጅተው ያገኙ ሰዎች የችግሩ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 6. የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት (የፍትዎት ፍላጎት)

አንዳንድ ምክር ፈላጊ የሆኑ ክርስቲያን ባለትዳሮች በማማከርበት ወቅት ትክክለኛውን ችግራቸውን ለማወቅ ጥያቄዎችን እጠይቃቸዋለሁ:: ከምጠይቃቸው የተለያዩ ጥያቄዎች መካከል አንዱ የግብረ ስጋ ግንኙነት በሚያደርጉበት ጊዜ ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር የሚጣጣሙ መሆኑንና አለመሆኑን የሚመለከት ጥያቄ ነው:: አንዳንዶቹም ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በግብረ ስጋ ግንኙነት እንደማይጣጣሙ ይገልጻሉ። በዚህ ወቅት ከመጀመሪያው ጥያቄ ወደ ሌላ ቀጣይ ጥያቄ በመሻገር አንዳንዶቹን በፖርኖግራፊ ላይ ያላቸውን አቋምና ልምምድ መረዳት እንድችል የሚረዳ ጥያቄ እጠይቃቸዋለሁ:: ለዚህ ጥያቄየ መልስ የሚሰጡ አንዳንዶች መላሾች የፖርኖ ግራፊ ቪዲዮዎችና ፊልሞች ተጠቃሚ እንደሆኑ በመግለጽ ሐቀኛ ምላሽ ይሰጡኛል። አንዳንዶቹ ልምምዳቸውን እንደ ትክክለኛ እርምጃ አድርገው በመውሰድ "ምን ምርጫ አለኝ?" ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች የበደለኝነት ስሜት ቢሰማቸውም "ከሌላ ሰው ጋር በዝሙት ከመውደቅ ይሻላል! ወይም ወደ ፍች ከመሄድ ይሻላል!" በማለት አእምሮቸውን በማሳመን በድርጊታቸው ለመቀጠል ይበረታታሉ:: ራሳቸውንም ያደፋፍራሉ።

በምክር አገልግሎት ካጋጠሙኝ አሳዛኝ ታሪኮች መካከል አንዱ ከኢትዮጵያ ውጭ በሚኖሩ ከተጋቡ ቅርብ ዓመት በሆናቸው ጥንዶች መካከል የተፈጠረ ክስተት ነው:: ባል ለአገሩ አዲስ የሆነ፣ ትምህርት ላይ የሚያተኩርና አብዛኛውን ጊዜ ቤት ውስጥ የሚያሳልፍ ሲሆን ሚስት ደግሞ አዲስ የትዳር ሕይወቷን ለማሳካትና የተለያዩ የቤት ወጭዎችን ለመሸፈን ሁለት ሥራ በመሥራት ብዙ ጊዜዋን ከባሏ ጋር ሳይሆን ሥራ ላይ ታሳልፍ ነበር። ሥራ ላይ ብቻ ያተኮረች ሚስት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ወደ ትዳሯ ዞወር በማለት ከባሏ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ስትፈልግ እርሱ በእነዚህ ዓመታት ቤት ውስጥ በዋለበትና ከሚስቱ ትኩረት በተነፈገው ጊዜ የተለማመደው የፖርኖግርፊ ልምምድ እንድታጣው ምክንያት ሆነባት። ልቤን በጣም የነካው **"በገዛ እጄ ባሌን አጣሁት"** በማለት የተናገረችው ንግግር ነው:: ባለትዳሮች እርስ በርሳቸው አብረው የሚቆዩበት

ጥሩ ኅብረትና የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርጉበት የጋራ ጊዜ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህንን የኅብረት ጊዜ መፍጠርና ሕይወትን መካፈል እንዲሁም መጣጣም ያለበት የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ካልቻሉና የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ባለማሟላት አንዱ ሌላውን መቅጣት ከጀመር የትዳር ጓደኛውን ለፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ እንዲሆን አሳልፎ እየሰጠ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነቱ ስህተት በትዳር ውስጥ ለግጭትና ለአለመግባባት ምክንያት ከመሆኑም በላይ ትዳርን የመበተን ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡

## 7. የክፉ መንፈስ አሠራርና ተጽዕኖ

ሰይጣን ከመቼውም ዘመን በበለጠ ሰዎች ወደ ትክክለኛ የትዳር ግንኙነት እንዳይደርሱ የጋብቻን ክቡርነት በማቃለል፣ እግዚአብሔር ከደነገገው ውጭ የሆነ ክፉ ልምምድ እንዲበዛ እና ለእግዚአብሔር ሰዎች የማይመችና የማይገባ ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ክፉ ስራውን በተለያየ መንገድ እያስፋፋ ይገኛል። እኛም እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ሃሳቡን ልንነቃበትና በጽድቅ ልናሸንፈው ይገባል። ዘመኑ ሰይጣን በራሱ ክፉ አሳብ የኢንተርኔት መርብን በመመጠቀም ክርስቲያኖችንና ክርስቲያን ባለትዳሮችን በፖርኖግራፊ እንዲጠመዱ በማነሳሳት፣ አጋጣሚዎችን በመፍጠር፣ ለፈተና እንዲጋለጡ በማድረግና በትዳራቸው ያጡትን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ማርኪያ አማራጭ እንዲጠቀሙ ሰበብ እየሰጠ በዚህ ክፉ ሱስ ተጠቂ፣ ተጋላጭና የወሲብ እስረኛ እንዲሆኑ እያደረገ ያለበት ጊዜ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

# VI. የፖሮኖግራፊ ሱስ አሉታዊ ተጽዕኖ

## 1. መደበቂያና ማምለጫ መንገድ አድርገው መጠቀማቸው

በፖርኖግራፊ የተጠመዱ ሰዎች ፖርኖግራፊን ከተለያዩ ነገሮች እንደ መደበቂያና ማምለጫ አድረገው ይጠቀሙበታል። ለጊዜው የሚሰጠውን ወቅታዊ የሆነ ወሲባዊ የስሜት እርካታና ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘት ሲሉም የወሲብ ሱስ እስረኛ ይሆናሉ። አንዳንዶች ራሳቸውን በአልኮል፣ በአደንዛዥ ዕፅ (ድራግ)፣ በትንባሆና በሌሎች ሱስ አመንጭ መንገዶች በመጠቀም በሕይወታቸው ከተፈጠረ ጊዜያዊ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ውጥረትና የሕመም ስሜት ለማስመለጥ ጥረት እንደሚያደረጉ ሁሉ የዚህ ሱስ ተጠቂዎች ደግሞ በፖርኖግራፊ ውስጥ ራሳቸውን በመደበቅ ጊዜያዊ ችግራቸውን ለመርሳት ይሞክራሉ።[46] ዘለቄታ ያለው መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ ጊዜያዊ የሆነ ደስታ ለመፍጠር ቅድሚያ በመስጠት በሚወስዱት ያልታሰበበት እርምጃ ለዕድሜ ልክ እስራት አልፈው ይሰጣሉ።

[46] sexuality and relationship counseling p 158





## 2. ጥልቅ በሆነ የተጎዳ ስሜት ውስጥ መኖር

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎችን በጥልቀት ለማወቅ ጥረት ብናደርግ ስለራሳቸው ያላቸው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። ማሕበራዊ ግንኙነታቸው በጣም ደካማ ነው፡፡ ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከቤተሰብና ከሌሎች ወዳጆች ጋር ከሚደረግ ማሕበራዊ ግንኙነት ራሳቸውን ያርቃሉ፡፡ በብቸኝነት በጣም የተጠቁ ናቸው፡፡ በሰው ዘንድ ተቀባይነት የለኝም ብለው የሚያስቡና የማንነት ቀውስ ያለባቸው ናቸው። ባጋጠማቸው የማንነት ቀውስ ምክንያት ድብቆችና ገለልተኞች ለመሆን ይገደዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ ምናልባት ከአሁን በፊት ጾታዊ ጥቃት ያጋጠማቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በአስገድዶ መደፈር ወይም በሌላ በልጅነታቸው በደረሰባቸው ወሲባዊ ጥቃት ... ምክንያት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ከሚኖራቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ የፖርኖግራፊ ፊልሞችንና ምስሎችን ማየትን በማዘውተር ወይም ራሳቸው በራሳቸው በግለ-ወሲብ (ማስተርቤንሽን)ና በተለያየ መንገድ የወሲብ ስሜታቸውን ማርካትን የሕይወት አማራጭ አድርገው ይወስዳሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ ከዚህ ሱስ ለመውጣት ቢሚከሩ እንኳን ካደረባቸው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ በቋሚ የዚህ ሱስ እስራት ውስጥ ተጠምደው በባርነት ለመኖር ይገደዳሉ፡፡[47]

## 3. ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር ስሜታዊና ግብረ ስጋዊ ግንኙነትን ማቋረጥ ይጀምራሉ

በተለያየ መንገድ በፖርኖግራፊ ሱስ ተጠቂ የሆኑ ባለትዳሮች ልምምዳቸው በግብረ ስጋ ግንኙነት ሱስ ይበልጥ እንዲያዙ ይዳርጋቸዋል። ከመጠን ባለፈ በፍትዎት ፍላጎት ሱስ ከመያዛቸው የተነሳ በትዳራቸው ባለው የግብረ ስጋ ግንኙነት የማይረኩና ስሜታዊ በመሆን ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር በየጊዜው የሚጋጩ ይሆናሉ። ሌላው ችግራቸው ከትዳር አጋሮቻቸው ትክክለኛ ያልሆነ ግብረ ስጋዊ ግንኙነትን ይጠብቃሉ፣ ይጠይቃሉ ብሎም የፈለጉትን ለማግኘት የትዳር ጓደኛቸውን ሊያስገድዱ ይችላሉ። ድብቅ በሆነ የፖርኖግራፊ ሱስ በመጠመዳቸው ምክንያት ከትዳር የሚጠበቀውን በእውነተኛ ፍቅር ላይ የተመሠረተውን ጤናማ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሂደት በማቃለል ወደ ማይፈለግና እንግዳ የሆነ የወሲብ ግንኙነት የመግባት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ። በክርስቲያን የትዳር ሕይወት ውስጥ በትክክለኛው የግብረ ስጋ የሰውነት ክፍል የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም ተፈጥሯዊ፣ ተገቢና ንጹሕም ነው *"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።" /ዕብ 13፡ 4/፡፡*

[47] sexuality and relationship counseling p 158

### 4. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ለሌሎች ችግሮችም ተጋላጭ መሆን ይጀምራሉ

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች በተያዙበት ሱስ በቀላሉ የማይረኩ፣ ይበልጥ የሚፈልጉና በየጊዜው የሚጨምር የፍትዎት ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡ ሌሎች ሰዎች ሌላ ነገር እንደሚራቡና እንደሚጠሙ ብሎም ፍላጎታቸውን ለማርካት ዋጋ እንደሚከፍሉ ሁሉ እነዚህ ሰዎችም ብርቱ የሆነ የፍትዎት ፍላጎት ያላቸውና ፍላጎታቸውንም ለማርካት ማንኛውንም ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው። የፍትዎት ፍላጎታቸው በተፈለገው ጊዜ ባልተሟላ ወቅት በብርቱ ይቆጣሉ፣ ንዴት ያጠቃቸዋል፣ በከፍተኛ ጥላቻ ውስጥም ይገባሉ። በፖርኖግራፊ የተጠመዱ ባለትዳሮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከመሆን ብቻቸውን በራሳቸው ክፍል ውስጥ መሆንንና ቀድሞ የነበራቸውን የጓደኝነት ቅርበት በመቀነስ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር እንኳን የጊዜ ሰሌዳ በመምረጥ መገናኘት የሚፈልጉ ናቸው፡፡[48]

አንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት ስሰጥ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል አንዱ እንዲህ ይመስል ነበር፡- ብዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሁኔታዎችን ለማጣራት ስሞክር ባሏ በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደባት ሚስት ስለባሏ፡- "ራሱን የቻለ የራሱ ክፍል አለው፡፡ ኮምፒዩተሩን ከእርሱ ውጭ የቤተሰቡ አባል መንካትና መጠቀም አይችልም፡፡ ልጆቹ ወደ እርሱ ክፍል ሲመጡ ዳዲ እየመጣን ነው ወይም ልንመጣ ነው ብለው ድምጽ በማሰማት ማስጠንቀቂያ መስጠት አለባቸው፡፡ ሌሊት ያመሻል ቀን ደግሞ በጣም ይተኛል፡፡ ከሁሉ በላይ ብቻውን መሆን በለመደበት ሰዓት እርሱን ሌላ ስራ ማዘዝ እጅግ በጣም ያስቆጣዋል (ይናደዳል) ብሎም ከእኔ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ይጋጫል፡፡" እያለች ምልክቶቹን በመዘርዘር አጫወተችኝ። እነዚህ ሁሉ በቂ ማስረጃ ሊሆኑ አይችሉም ልትሉ እንደምትችሉ አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ይህች ሴት ብዙ ጊዜ እርሱ ሳያውቅ ሲመለከተው የነበረውን የፖርኖግራፊ ድረ ገጽ ሳይዘጋው አግኝታ ነበር፡፡ ጥያቄ በጠየቅሁ ጊዜ ምልክቶቹን በዝርዝር ልታስረዳኝ የሞከረችውም ለዚህ ነበር።

ሌላው የፖርኖግራፊ የቪዲዮ ምስሎችና ፎቶግራፎች አዘውትረው በማየት በወሲብ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የሚታይባቸው ጸባይ የአካል ድካም፣ የእንቅልፍ ብዛት፣ አለመንቃትና ለሥራ ተነሳሽነትና ኃይል ማጣት ነው፡፡[49] እነዚህ ምልክቶች የሚታዩባቸው ሰዎች ሁሉ በጅምላ የፖርኖግራፊ የቪዲዮ ምስሎችና ፎቶግራፎች በማየት ሱስ የጠመዱ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በሥራ ብዛት፣ በትምህርት ላይ ባሉ ሰዎች ላይ ጥናትና የወረቀት ሥራዎች በፈጠሩት እረፍት የለሽ ወከባ፣ በጤና መታወክ፣ የተለያዩ ችግሮች ባስከተሉት ድብርትና የተስፋ መቁረጥ ሁኔታ … ምክንያት የአካል

[48] sexuality and relationship counseling p 158

[49] sexuality and relationship counseling p 158



የግጭት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

ድካም፣ ንቃትና የሥራ ተነሳሽነት ማጣት እንዲሁም የእንቅልፍ ብዛት የመሳሰሉት ችግሮች በሰዎች ላይ ሊከሰቱ እንደሚችሉ እገነዘባለሁ፡፡ ነገር ግን እዚህ ላይ ማሳየት የፈለግሁት በፖርኖግራፊ ፍትወታዊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የራሳቸውን ማንነት ዝቅ አድርገው የሚያዩ በመሆናቸው በሚፈጠርባቸው የተስፋ መቁረጥ ምክንያትና በተለይ በለመዱት ሰአት የሚፈልጉትን ማግኘት ባልቻሉ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ድብርት የሚያጠቃቸው መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት ራሳቸውንና ማንኛውንም የሕይወት እንቅስቃሴ የሚያዩበት ተስፈኛ የሆነ እይታ ስለማይኖራቸው በጨለምተኛነት፣ በሌላ አካል አስገዳጅነት አንድ ነገር የማድረግ ግዴታ የተጣለባቸው በሚመስልና በጣም በተሰላቸ ስሜት ነገሮችን ሁሉ ያስተናግዳሉ፡፡ ወሲባዊ ፍላጎት አእምሮቸውንና ስሜታቸውን ስለሚቆጣጠራቸው ለሌላ ሃሳብና ድርጊት ክፍትና ንቁ አይሆኑም። በተደጋጋሚ ይህን አመጽ በድብቅ ከመለማመዳቸው የተነሳ ችግር ውስጥ እንዳሉ በተረዱ ጊዜ እንኳን ከችግሩ ለመውጣት እየፈለጉ ባለመቻላቸው በየጊዜው የበደለኝነት፣ የኃፍረትና የጭንቀት ስሜት ይፈራረቅባቸዋል።

## VII. በፖርኖግራፊ ሱስ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. በሱስ የተጠመደ አካል ሊወስደው የሚገባ እርምጃ

#### 1) መጀመር፡- ኃጢአት መሆኑን ማመንና እርዳታ ለማግኘት ፈቃደኛ ከመሆን መጀመር

ፖርኖግራፊ በተባለው አስከፊ ሱስ የተጠመዱ ሱሰኞች ከተያዙበት ሱስ ለመላቀቅ ከሁሉ አስቀድመው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን የወደቁበት ወጥመድ ኃጢአት መሆኑን ከመቀበል መጀምር ከችግሩ መውጣት የሚያስችል እርዳታ ለማግኘት ቀዳሚው ጉዳይ ነው። ስለፖርኖግራፊ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? የሚለውን ሃሳብ ለመዳሰስ የሞከርኩት አንዳንዶቹ ተጠቃሚዎች አመጽና ክፉ ልምምድን የሚያሰራጩት ምንም ችግር እንዴለለበት፣ ጽድቅና መልካም ሥራ እንደሆነ አድርገው በመናገር ስለሆነ ነው፡፡ ይህን አቋም የሚያራምዱና ጥቅስ በመጥቀስ ከፋታቸውን የሚያዘምቱ አማኝ ነን የሚሉ ሰዎች መኖራቸውን ይህ አቋም ካላቸው ክርስቲያን ነን ባይ ሰዎች ጋር ባደረግሁት ውይይት ለማወቅ ችያለሁ። መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነታ እነርሱ ከሚሉት በተቃራኒ ርኩሰታዊውን ልምምድ በግልጥ ኃጢአት፣ ርኩሰት፣ ፍትዎት፣ አመንዝራነት፣ ሴሰኝነት፣ ክፋት በማለት ይገልጸዋል። ከችግሩ ለመውጣት የመጀመሪያው እርምጃ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቅ በመረዳት አምኖ መቀበልና ከችግሩ ለመውጣት ፈቃደኝነትንና ፍላጎትን ማሳየት ነው /ቆላ 3: 5፣ 1ኛተሰ 4: 3-5፣ 1ኛቆሮ 6: 18/

#### 2) መግባት፡- ድካምን (ጥፋተኝነትን) አምኖ በመቀበል ንስሃ መግባት

በዚህ ችግር ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች በአጠቃላይም የዚህ ሱስ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ከችግሩ የመውጣት ፍላጎት ካላቸው በቅድሚያ ከቁጥጥር ውጭ የሆነው ወሲባዊ ባሕርያቸው ስህተትና ኃጢአት መሆኑን መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡ እግዚአብሔር

የሚያድስ፣ የሚለውጥና ነፃ የሚያወጣ ኃይል እንዳለው በማመን እና ለእግዚአብሔር፤ ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች በመናዘዝ ፈቃዳቸውንና ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ጥበቃና ቁጥጥር ስር እንዲሆን መወሰንና መፍቀድ መለኮታዊና ሰብአዊ ድጋፍ ማግኘት ያስችላቸዋል:: ሌሎች የሞራል ግድፈቶች ካሉባቸው ደግሞ በእርጋታ ራሳቸውን በመመርመር ለለውጥ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው:: እውነተኛ ንስሃ በመግባት ተግባራዊ የሕይወት ለውጥ ለማምጣት የውሳኔ ሰው፣ ቆራጥና ጽኑ መሆን ይገባቸዋል::

**3) *መለማመድ፡- በክርስቶስ ማንነት ላይ በተመሠረተ የክርስትና ሕይወት መኖርን መለማመድ***

የክርስትና ሕይወት መሠረት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ በመመሥረትና በእርሱ በመታመን የሕይወት ውድቀቶችን ለማሸነፍ ዝግጁ መሆን ተገቢ ነው። በክርስቶስ ማንነት ውስጥ ስንሆን እርሱ በእኛ ሁኖ ይረዳናል:: ሕይወታችንን ሊለውጥና የቅዱስ መንፈሱ መኖሪያ እንድንሆንና የእርሱን መልክ እንድንመስል በሚያስችል ጸጋው ነፃነትና አቅምም ይሰጠናል:: በዚህ የሕይወት መስመር በቋሚነት ለመኖር ደግሞ በክርስቶስ ሕይወት ላይ፣ በጽድቁ ላይ እና በትምህርቱ ላይ መመሥረት የግድ ነው /**1ኛቆሮ 3: 16-17፣ 1ኛቆሮ 6: 16-20፣ 1ኛቆሮ 15: 56-57**/።

በክርስቶስ ማንነት ላይ በመመሥረትና በመታነጽ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ መንፈሳዊ ሕይወትና እንቅስቃሴ ውስጥ መሆን ተገቢ ነው። በሂደት መንፈሳዊ ፍሬዎችን በሕይወት በመጨመርና በማብዛት፣ ከጌታ የተማርነውን፣ የተቀበልነውን፣ የሰማነውንና ያየነውን በማድረግ (በመታዘዝ) ሕይወትን ከተለያየ ሱስ መጠበቅና ማስመለጥ ይቻላል /**ፊል 4: 8-9**/። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረው በየቀኑ የልቦናን ወገብ በመታጠቅ፣ በመጠን በመኖር፣ ያለፈን ምኞት ባለመከተልና የተጠራንበትን ዓላማ በመገንዘብ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ራስን መግዛትን በመለማመድ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ትክክለኛው የነጻነት መንገድ ነው /**ኤፌ 2:1-3፣ 2ኛጴጥ 1: 3-4**/ ።

**4) *መገንዘብ፡- ኃይል በሚሰጠን በክርስቶስ እንደምንችል መገንዘብ***

መንፈሳዊ ንቃታችሁን በመጠበቅ ተመልሳችሁ በሱስ እንዳትጠመዱ መርሆዎችን መጠበቅና መለማመድ ሕይወትን በማያቋርጥና በተትረፈረፈ ሕይወት መኖር እንዲቻል ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። እግዚአብሔር ለሕይወት፣ ለመንፈሳዊ ብስለትና እድገት እንዲሁም ለቅድስና እንደጠራችሁ በማመን በቅድስና መመላለስን መለማመድ ቁልፍ መፍትሔ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው /**1ኛጴጥ 1: 13-16**/:: በሱስ የተያዘው ሰው ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የወሲብ ፍላጎትን ለማስወገድና በሱስ የተጠመደውን ሰው የሚረዳ (ደካሞችን ሊረዳ የሚችል) ሁሉን የሚችል አምላክ እንዳለ ማወቅ፣ ማመንና በአቅርቦቱ ለመረዳት እንደሚቻል መገንዘብ አስፈላጊ ነው /**ፊል. 4: 8-13 ኢሳ 40: 27**/።



የጥፋት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

**5) *መጠቀም፡- የተለያዩ የመፍትሔ ሃሳቦችን መጠቀም***

**i. በአሳብና በስሜት መጓዝን መቆጣጠር**

ከፖርኖግራፊ ሱስ ነፃ በመውጣት ጤነኛና ደስተኛ የሆነ ትዳርና ቤተሰብ እንዲኖራቸው ሁሉም አካላት የየበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል። የፖርኖግራፊ ሱስ ከፍተኛውና የመጀመሪያው አሉታዊ ተፅዕኖ አእምሮንና ስሜትን መቆጣጠር መቻሉ ነው። ስለዚህ የፍትዎት ስሜት አእምሯቸውን በመቆጣጠሩ የተለያዩ ከክርስትና ጋር የሚቃረኑ መንገዶችን ተጠቅመው የፍትዎት ፍላጎታቸውን የማርካት ባሪያ ከሆኑበት ለመላቀቅ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል:: ይህ ፍላጎት ካላቸው ፍላጎታቸውን በተግባራዊ ጥረት ለማገዝ ቆራጥነትና አቋም ያስፈልጋቸዋል:: የጥረታቸው የመጀመሪያው እርምጃ ደግሞ በሃሳባቸው የሚመጣ የፍትዎት ፍላጎት በሌላ አሳብ እንዲለወጥ አእምሯቸውንና ስሜታቸውን መቆጣጠር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር መሆን አለበት። *"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።"* /**ሮሜ 12፡ 2**/ የእግዚአብሔር ቃልም *"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።"* /**ምሳሌ 4: 24**/ በማለት አጥብቀን ልባችንን መጠበቅ እንዳለብን የሚያስተምረን አሳባችንን በጤንነት ከጠበቅን ተግባራችንና ኑሯችንም ጤነኛ እንደሚሆን ለማስረዳት ነው።

**ii. የሚፈትኑ ነገሮችን ማራቅና ከእነርሱ መሸሽ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች ከተያዙበት እስራት ነፃ መውጣት ፍላጎታቸውና አቋማቸው ከሆነ ለፖርኖግራፊ ልምምድ ከሚያነሳሱና ከሚያበረታቱ የተለያዩ መጽሔቶች፣ ጽሑፎችና የቪዲዮ ፊልሞች በመራቅና እነዚህን ነገሮች ከአካባቢያቸው በማራቅ ራስን ከፈተና መጠበቅ ጠቃሚ ነው። በዙሪያ ያሉ ተፈታታኝ የሆኑ ጹፎችን ብቻ ሳይሆን ኮምፒዩተር ላይ የተቀመጡ የተለያዩ ቪዲዮችን መደምሰስ ተገቢ ነው። *"ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።"* /**1ኛቆሮ 6፡ 18**/። ብቻቸውን በሚሆኑበት ወቅት ለፍትዎት አሳብ ፈተና የሚጋለጡ ከሆነ የቤተሰብ አባል ወይም ሌሎች ሰዎች ባሉበት ወቅት ኮምፑተር መጠቀም ራስን ከፈተና የመጠበቂያ ጥሩ አማራጭ ነው:: በተጨማሪ ለሌላ ሰው ተጠያቂ በመሆን ያሉበትን ደረጃ የሚጠይቅ፣ የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ መንፈሳዊ፣ ታማኝና ብቃት ያለው አማካሪ ወይም መጋቢ ማግኘት በእግዚአብሔር ቃል እውነት እየተቀረጹና እየታደሱ በአስተሳሰብና በተግባራዊ የለውጥ መንገድ ለመጓዝ እጅግ በጣም አስፈላጊ እርምጃ ሊሆን ይችላል። *"ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ"* /**ኤፌ 4: 22-23**/

**iii. ጠንካራ ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባርና መንፈሳዊ ልምምድ ላይ ስር መሰደድ**

ሕይወትን ለክርስቶስ መስጠትና ማስገዛት እንዲቻል የሚረዱና መንፈሳዊ አቅጣጫ የሚያሳዩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ሕብረት መፍጠር አስፈላጊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለማወቅ፣ ለመለማመድና ሥር በመስደድ መለወጥ እንዲቻል ከሚያስተምሩና ከሚከታተሉ አገልጋዮች እርዳታ የሚያገኙበትን እድል መፈለግ አለባቸው። የፖርኖግራፊ ልምምድ ኃጢአት እንደሆነ መረዳት፣ በእውነተኛ ንስሃ መመለስና ይበልጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ትኩረት በማድረግ ለእውነተኛ ለውጥ የመዘጋጀት ውሳኔ መወሰን ያስፈልጋል። *"አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል። መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።* /1ኛጢሞ 6፡ 11-12/

መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።"* /2ኛቆሮ 5፡ 17/ በማለት እንደሚመሰክረው በክርስቶስ አዲስ ሕይወት እንዳለው አማኝ አሮጌውን ነገር በመተው አዲስ ሕይወትን በትጋት ወደ መለማመመድ መግባት በችግሩ የተያዙ ሰዎች ከተጠመዱበት ሱስ ነፃ ለመውጣት የሚችሉበት ቁልፍ ነው:: ይህን ትጋት የተሳካ ለማድረግ በቅዱሳን መንፈሳዊ ሕብረት በመሳተፍ በኅብረቱ ተጠያቂነትና በረከት ተጠቃሚ መሆን አስፈላጊ ነው። አንዱ ሌላውን ማገልገል እንዲችሉና በማሕበራዊ ግንኙነት የተሳሰረ ሕብረት እንዲኖራቸው ራሳቸውን በጤናማ ኅብረት ህብረት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ከፖርኖግራፊ ሱስ ለመውጣት ባለው ሂደት የሚሰጠው እገዛ ከፍተኛ ነው። አገልጋዮችም ሆኑ የትዳር አጋር በፖርኖግራፊ ልምምድ ውስጥ ያለውን ሰው በመርዳት ሂደት ውስጥ ማረጋገጥ ካለባቸው ነገር መካከል አንዱ እርዳታ ፈላጊዎቹ በመልካም ሰዎች መከበባቸውን ነው። *"አትሳቱ፤ ክፉ ባልጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል"* /1ኛቆሮ 15፡ 33/

ቀጣይነት ያለው እርዳታ ለመስጠት ትዳራቸው እንዴት እንደሆነ ማረጋገጥ፣ ነፃ በመውጣቱ ሂደት የተፈጠረባቸውን ስሜት መረዳትና በተለይ የፖርኖግራፊ ልምምድ ውስጥ እንዲሆኑ ያደረጓቸውን ሁኔታዎች በጥንቃቄ መመዘን የመሳሰሉ መልካም እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው:: ከልምምዱ ለመውጣት ጥረት በሚያደርጉ ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው በመጠየቅ መረዳት ተገቢ ነው። ሊሰማቸው የሚችለውን ስሜትና ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ለማገዝ፣ በጸሎትና በምክር ለመርዳት መትጋት ብሎም በተለያዩ ሥራዎች እንዲጠመዱ ማድረግ ጠቃሚ ነው:: አብሮነትን በማጠናከርም ከፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ እየወጡ እንዲመጡ በጤነኛው የሕይወት መስመር ስር እንዲሰድዱ ለችግሩ ሰለባዎች ያላሰለሰ ድጋፍና ጥረት ማድረግ ትርጉም ያለው ውጤት ያመጣል።

**iv. ቤጋብቻ አማካሪዎች አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን**

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ሊጀምሩትና ሊያጠናክሩት ከሚገባው አገልግሎት አንዱ የጋብቻና የቤተሰብ የማማከር አገልግሎት ነው:: ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በትዳርና በቤተሰብ ዙሪያ እየደረሱ ያሉ የተለያዩ ቀውሶችን ለመቀነስና ለማስወገድ አንዱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች ኃላፊነት የማማከር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማኞችን መለየት፣ ማሰልጠንና ኃላፊነት በመስጠት የምክክር አገልግሎትን አጠናክሮ መጀመር ነው:: ያን ጊዜ ብቻ ምክርና እርዳታ ፈላጊ ሰዎች በፈለጉት ጊዜና ቦታ የምክር አገልግሎትን መጠቀም የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል:: ይህን ማድረግም ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ሊሆን ይገባል። የችግሩን በፍጥነትና አደገኛ በሆነ መንገድ የመስፋፋት ሂደት ለመቆጣጠርና ለመቀነስ እንዲሁም የብዙ ክርስቲያኖችን ትዳር ከቀውስና ከፍርሰት ለማዳን ቤተ ክርስቲያን የጸጋ ስጦታ፣ ሌሎችን የማገልገል ልብ፣ ጊዜ፣ ስልጠናና ልምድ ያላቸውን ሰዎች በማሰለፍ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ልትንቀሳቀስ ይገባታል።

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደው የትዳር አጋርም በቤተ ክርስቲያን ባለው የጋብቻና የቤተሰብ የማማከር አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን በለውጡ ሂደት አማካሪዎች አብረው እንዲሆኑ መፍቀድ፣ መተባበርና እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። የትዳር አማካሪዎች በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮችን በሚረዱበት ወቅት ግለሰቡን እንደ አማኝና እንደ ባለትዳር በማነጋገር ችግሩን ለመፍታት ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ መሪዎችና አማካሪዎች እርዳታ የማድረጉ ሂደት ከአቅም በላይ በሚሆንባቸው ወቅት ከምክር ፈላጊው ጋር በመነጋገርና ፈቃደኝነቱን በመረዳት ክርስቲያን ፕሮፌሽናል አማካሪ ወደ ሆኑ ሰዎች ተመካሪውን በመምራት ተገቢውን እርዳታ እንዲያገኝ ማገዝ አስፈላጊ ነው።

**v. ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ግልጥነትና ተጠያቂነትን መፍጠር**

ራስን ከተለያዩ ወሲባዊ ፈተና ለመጠበቅና የትዳር የፍቅር ግንኙነት ለማጠናከር አንዱ ለሌላው ግልጥ የሆነ ተግባቦትና ተጠያቂነት መፍጠር ተገቢ ነው። ባልና ሚስት በቁጥጥር መንፈስ ሳይሆን ነፃነት፣ መተማመመን በተሞላው ግንኙነትና በፈቃደኝነት በተመሠረተ ተጠያቂነት መፍጠር በጥንዶች ላይ ይበልጥ መተማመንና አንዱ ሌላውን መጠበቅ፣ መርዳትና መሸፈን እንዲኖር ያግዛል። በቤት ውስጥ ያሉ ኮምፒዩተር፣ ላፕ ቶፕ፣ ተንቀሳቃሽ የእጅ ስልኮች፣ በኢንተርኔት መርብ የሚላኩና ገብተን የምንመለከታቸው ድረ ገጾችን፣ የሚታዩ የተለያዩ ቪዲዮዎችና ፊልሞችን አንዱ የትዳር አጋር የሌላውን ማየትና መጠቀም ቢችል ስጋትና ጥል የማይፈጥር ሁኔታ በተገነባ ግልጥነትና ተግባቦት ግንኙነትን መጠበቅ ተገቢ ነው።

**vi. የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመግዛት ከኮምፒዩተር ውስጥ የማይፈለጉ ድረ ገጾችን በማጣራትና በመቆጣጠር ማስቆም**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች ከዚህ ችግር ለመውጣት ሲሞክሩ የሚፈትኑ ነገሮችን ማራቅ አንዱ ወሳኝ የመፍትሔ መንገድ ነው:: ራስን መግዛት ችግሩን መቋቋም ካልተቻለ ደግሞ ኮምፒዩተርን ለማጽዳት የሚያግዙ ሶፍትዌሮችን በመግዛት በኢንተርኔት የሚላኩ የተለያዩ ለፍትዎት የሚያነሳሱ ድረ ገጾችን ማጣራትና ማስቆም የሚቻልበትን መንገድ መጠቀም ብልህነት ነው። እዚህ ላይ ይህንን ለማድረግ

የሚያስችሉ የታወቁ ሶፍትዌሮችን በመጥቀስ ማሳወቅ ግንዛቤ ለማስጨበጥና አንዳንድ ወገኖችን ለመርዳት ጠቃሚ ነው። በአገራችን የታወቁ እንዲህ ዓይነቱን ድረ ገጽ የሚከላከሉ ሶፍትዌሮች ስላልተዘጋጁ በአማርኛ ቋንቋ ስማቸውን የመጥቀሱ ጉዳይ ያስቸግራል። ከዚህም ባለፈ የሶፍትዌሮችን ስም በአማርኛ ቋንቋ መጥቀስ ስለሶፍትዌሮች ግልጥ መረጃ ከማስተላለፍ ይልቅ መደናገር ሊፈጥር ይችላልና በቀጥታ በእንግሊዘኛ በሚጠሩበት የታወቀ ስማቸው ዝርዝራቸውን ላስቀምጥ እወዳለሁ። እናንተም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሶፍትዌሮች በመግዛት እንድትጠቀሙባቸውና ለእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ቃል መርህ መሰረት ራሳችሁንና ትዳራችሁን ለተመሠረተው የትዳር ሕይወት መርህ የማስገዛት ትጋታችሁን እንድትቀጥሉ አደራ እላለሁ።

- Net Nanny parental control
- McAfee safe eyes
- McAfee family protection
- PureSight PC
- CYBERSitter
- Cyber patrol
- Profile parental filter
- im view... የመሳሰሉ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ብልህነት እንጅ ሽንፈት አይደለም።

**vii. ከክፉ መናፍስት ተጽዕኖ ነፃ መውጣት**

ሰይጣን በተለያየ መንገድ ሊዋጋ ይችላል። አንዳንዶችን በቁጥጥሩ ሥር በማድረግና የራሱን ፈቃድ እንዲፈጽሙና እንዲያገለግሉት ባሪያ በማድረግ የሚገዛቸው ሲሆን ሌላው ክፉ አሠራሩ ደግሞ በውጭ በመሆን አሳብን በመላክ፣ አማኞችን በመጫን፣ ከሩቅ ሁኖ በመዋጋትና የተለያዩ ክፉ አሳቦችንና የፈተና ወጥመዶችን በመዘርጋት የክፉ ስራው ሰለባ እንዲሆኑ ያደርጋል። በእውነት ክርስቶስ ጌታና አዳኝ ነው ብሎ በሚያምን ዳግም በተወለደ አማኝ ሕይወት ውስጥ ኢጋንንት ይኖራል እያልኩ ሳይሆን በየጊዜው በንስሃና በንስሃ ፍሬ መንፈሳዊ ሕይወትን በጽድቅ መንገድ መምራት ካልተቻለ ሰይጣን በአማኞች ሕይወት ላይ እንኳን በክፉ ሥራው ተጽእኖውን በማሳረፍ ባሪያና ተገዥ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንደነዚህ ዓይነት በመናፍስት ክፉ ሥራ እስራት ውስጥ ያሉ በጌታ መንፈስ ነፃ ሊወጡ ይገባል። በእርግጥ ሁሉንም ነገር የመንፈስ አሠራር ተጽእኖ ብቻ ማድረግ የለብንም:: ነገር ግን የሰይጣንን አሠራር አሳንሶ በማየት እንደሌለ መቁጠርና ሁሉንም ነገር ተፈጥሯዊና ሰብአዊ ብቻ በማድረግ በሕክምናና በሌሎች መንገዶች ብቻ ለመፍታት በመሞከር በዲያብሎስ ሥራ እንዳንታለል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ችግሮችን በመለየት ተገቢውን አገልግሎት የማግኘት አስፈላጊ ነው:: አገልጋዮችም እንደጸጋቸው ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው::



የጥቃት መንስኤዎችና መፍትሔዎቻቸው በጋብቻ ውስጥ!

## 2. በሱስ የተጠመደን አካል (ግለሰብ) ለመርዳት ሊወሰድ የሚገባ እርምጃ

**1) *መጣር:- ችግሩን ይበልጥ ለመረዳት ጥረት ማድረግ***

**i. በፍቅርና በርህራኄ መቅረብ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደን ሰው ለመርዳት ኃላፊነትና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ሊወስዱት የሚገባው የመጀመሪያው የመነሻ እርምጃ ችግሩን ይበልጥ ለመረዳት እንዲችሉ በችግሩ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በርህራኄና በፍቅር መቀበልና መቅረብ ነው። በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደ የትዳር አጋርን ከዚህ ውድቀት ለማትረፍ የመጀመሪያው እርምጃ በፍቅር ለመርዳት መዘጋጀት እንጅ መፍረድ መሆን የለበትም። በፍቅርና በርህራኄ መቅረብ የችግሩ ተጠቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር እርዳታ እየሰጡ ብዙ መንገድ አብሮ ለመዝለቅ ይረዳል። ጌታ ኢየሱስ ደካማ የሆኑ ሰዎችን ለመርዳት *"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።"* /ማቴ 11፡ 28/ ብሎ ወደ ራሱ በፍቅር በመጋበዝ ከእነርሱ ጋር በአስገራሚ ፍቅርና ርህራሄ አብሯቸው እንደነበር ወንጌላት ያስረዱናል። ስታመነዝር የተገኘችውን ሴት በአመንዝራነቷ ሰዎች እንደ ሙሴ ሕግ ሊፈረድባት የሚገባት እንደሆነች በማስረዳት ከሰዋት ነበር:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ሳይፈርድባት ድጋሚ ተመሳሳይ ኃጢአት እንዳትሰራ በማስጠንቀቅ ምህረት ሲያደርግላትና በነፃ ሲለቃት ማየት የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለመርዳት ሊከተሉት የሚገባ ትልቅ ምሳሌ ነው። *"ኢየሱስም:- እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።"* /ዮሐ 8፡ 11/

**ii. እያለፉበት ያለውን ሁኔታ ይበልጥ ለመረዳት የሚያስችሉንን የሚከተሉትን ተገቢ ጥያቄዎች መጠየቅ**

- *የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ማየት ከጀመሩ ስንት ጊዜ ሆናቸው? በስንት አመታቸው (እድሜአቸው) ማየት ጀመሩ? የሚያዩት በምን ያህል የጊዜ ርቀት ነው?*
- *የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ለማየት ያነሳሳቸው ምንድን ነው?*
- *የፖርኖግራፊ ፊልሞችን፣ የቪዲዮ ምስሎችንና ፎቶግራፎችን ማየት የሚያዘወትሩት መቼ ነው? የሚመለከቱበት የጊዜ ሁኔታ ቀን፣ ማታ ወይንስ በየትኛው ሰዓት?*

✓ ብቸኛ በሚሆኑበት (ሰው በሌለበት) ጊዜ?
✓ ምን ዓይነት ስሜት ሲፈጠርባቸው ነው ወደ ማየት የሚሄዱት (በሚጨናነቁበት፣ በሚያዝኑበት... ጊዜ)?
✓ ምን ዓይነት የአየር ሁኔታ ባለበት ወቅት (በብርድ፣ በሙቀት...ጊዜ)?
✓ ከሥራ እረፍት በሚሆኑበት ወይንስ ሥራ ላይ ባሉበት ሰዓት? ወዘተ...

- እያመጣ ያለውን ክፉ ተጽዕኖ አምነው ይቀበላሉ? ስለጉዳዩ ግልጽ ጥያቄ ቢቀርብላቸው ምን ይላሉ?
  - ✓ በሕይወታቸው
  - ✓ በትዳራቸው
  - ✓ በቤተሰባቸው
  - ✓ በማሕበራዊ ግንኙነታቸው...
- ልምምዱን ለማቆም ሞክረው ያውቃሉ? ከሆነስ እንዴት? ለምን ያክል ጊዜ አቋርጠው ቆዩ? እንደገና እንዲቀጥሉ ያነሳሳቸውስ ምን ነበር?
- ከዚህ ሱስ ለመውጣት ምን ያክል ፈቃደኛ ናቸው? መውጣት የሚቻልበት ተስፋ አለ ብለው ያስባሉ?
- ስለእግዚአብሔር ረዳትነትና ሕይወታቸውን ሊለውጥ እንደሚችል ምን ያክል ያምናሉ?[50]

**2) መግለጥ፡- የሚፈጥርባቸውን ስሜት በመረዳት በተለያየ መንገድ አብሮነትን መግለጥ**

በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ሰዎች የሚፈጠርባቸውን እንግዳና መጥፎ ስሜት በመረዳት በተለያየ መንገድ አብሮነትን ለማሳየት ምን ዓይነት ሁኔታ ወደ ፖርኖግራፊ ስሜትና ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምን ዓይነት ሁኔታ ወደ ፖርኖግራፊ ስሜትና ልምምድ ውስጥ እንዲገቡ እንደሚያደርጋቸው ለመረዳት ደግሞ፡- ከሥራ ጋር የተያያዘ መሆን አለመሆኑን? በቀኑ ውስጥ በትኛው ሰዓት ላይ ፈተናው እንደሚበዛባቸው? በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ማለትም፡ በሚጨናነቁበት ወቅት፣ በሚቆጡ ጊዜ፣ ጥልቅ ሃዘን ውስጥና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሲሆኑ፣ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ግንኙነታቸው ሲበላሽ ወ.ዘ.ተ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መወያየት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች ልንረዳቸው ፈቃደኛ መሆናችንን በግልጥ በማሳየት ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ በዓላማና በእቅድ አብሮ መሆን ተገቢ ነው። በፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሚሰሟቸውና ከሚፈጠሩባቸው የተለያዩ ጥልቅ ስሜቶች መካከል ከፍተኛ የሆነ የፍትዎት ፍላጎት፣ ከፍተኛ የሆነ ቁጣና ንዴት እንዲሁም የብቸኝነት ስሜት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ልንረዳው የምንፈልገው ሰው መሠረታዊ የስሜት ችግር የትኛው እንደሆነ መገንዘብም ይህንን ስሜት በሌላ ስሜት መቀየር የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

በፖርኖግራፊ ሱስ ልምምድ ውስጥ ያሉ ሰዎችን መርዳት የሚወስደው ጊዜ ቀላል አይደለም። ከሱስ ነፃ የመውጣት ሂደት የእርዳታ ፈላጊውን ፈቃደኝነት መሠረት

[50] sexuality and relationship counseling p 159





በማድረግ የሌሎች የታመኑ ሰዎች እርዳታ የግድ ያስፈልገዋል፡፡ ስለዚህ እርዳታ መስጠት የሚችሉ ሰዎችን በመጠየቅና በመተጋገዝ አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠት፣ የሚፈጠሩ የተለያዩ መጥፎ ስሜቶችን ለመቀነስ፣ የታመኑ ወዳጆችን (ጓደኞችን) በመጋበዝ በጸሎት፣ በምክርና አብሮነትን በመግለጽ ማገዝ መንፈሳዊነትና ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችን ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ስናደርግ ራሳችንን በመጠበቅና በጥንቃቄ መሆን አለበት/ገላ 6፡ 1-2/።

**3) መምራት፡- ትክክለኛና ሙያዊ ድጋፍ ሊሰጡ ወደሚችሉ ክርስቲያን አማካሪዎች መምራት**

እንደ ትዳር ጓደኛነታችሁና ክርስቲያንነታችሁ በፖርኖግራፊ ሱስ ውስጥ ለወደቁ የትዳር አጋሮች ወይም ወዳጆች አቅማችሁና እውቀታችሁ የሚፈቅድላችሁን ያህል ድጋፍና እርዳታ ካበረከታችሁ በኋላ የሰጣችሁት ድጋፍ በቂና ለውጥ አምጭ መስሎ ካልታያችሁ ሌሎች አማራጮችን ስለማቅረብ ማሰብ አለባችሁ፡፡ የእኛን ጥረቶች ማድረጋችን እንደተጠበቀ ሆኖ የችግሩ ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችን ከሌሎች በመንፈሳዊ ሕይወትና በማማከር አገልግሎት ባለሙያ ከሆኑ ሰዎች ድጋፍ ማግኘት ያለባቸው መሆኑን በማስረዳት ማሳመንና ሊረዷቸው ወደሚችሉ ሰዎች መምራት አለብን፡፡

የተሻለ ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎች የሚባሉት በሳልና የታመኑ ክርስቲያን ወንድሞችና እህቶች ሆነው በተለይ በማማከር አገልግሎት በሚገባ የሰለጠኑ ፕሮፌሽናል አማካሪዎች ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ የሰለጠኑ ክርስቲያን የማማከር አገልግሎት ባለሙያዎች የሌሉ ከሆነ ደግሞ ችግር ውስጥ ያለው ሰው ድጋፍ እንዲያገኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ መሪዎች፣ ክርስቲያናዊ ድረጅቶችና አገልግሎቶች መምራት አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ መንፈሳዊ አቅጣጫ በማሳየት፣ አመለካከቱን በእግዚአብሔር ቃል መርህ በማስተካከልና በመቅረጽ የሞራልን ከቡርነት እንዲረዳ እያገዙት ቀጣይነት ባለው ክትትል እርዳታ ሊያደርጉለትና ትክክለኛ እርዳታ በመስጠት ወደ ትክክለኛው መንገድ ሊመሩት እንዲሁም ሊያበረታቱት ይገባል።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አስራ ሁለት (12)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ፖርኖግራፊ የሚለውን ቃልና ሃሳብ ምንነት በመግለጥ ተወያዩበት፡፡
2. የፖርኖግራፊ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ያሏቸው የተለያዩ አመለካከቶች ምንድን ናቸው? እናንተስ እንዴት ታዩታላቹህ?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለፖርኖግራፊ ምን እንደሚል በመጽሐፉ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማውጣትና በማንበብ በሰፊው ተነጋገሩበት፡፡
4. በዚህ ዘመን ባለትዳሮችን አስከፊ ለሆነው የፍትዎት ሱስ (ለፖርኖግራፊ) ተጋላጭ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ምክንያት በመዘርዘር በፍጹም ግልጥነት ውይይት አድርጉ፡፡
5. ለፖርኖግራፊ እይታ ተጋላጭ ሁናቹህ ታውቃላቹህን? እንዴት? ከዚያስ ምን እርምጃ ወሰዳችሁ?
6. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመዱ ባለትዳሮች ላይ ሊፈጠር የሚችል አስከፊ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖና ግጭት ምን እንደሆነ በዝርዝርና በግለጥ ተወያዩ፡፡
7. በፖርኖግራፊ ሱስ የተጠመደ የትዳር አጋር ምን የመፍትሔ እርምጃ ሊወስድ ይገባል? አንድ የትዳር ጓደኛ በዚህ ሱስ የተያዘውን አጋሩን ሊረዳ የሚችልባቸው የመፍትሔ እርምጃዎችን በጥንቃቄ፣ በስፋትና በነፃነት በማንሳት ውይይት አድርጉ።
8. ወደ ፊት አስከፊ ለሆነው የፖርኖግራፊ ሱስ ተጋላጭ ላለመሆን እንደ ባለትዳር ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?





# ክፍል ሶስት፡- ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ